በፍቅር፤ በሰላም፤ በአንድነት፤
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ!
መቻቻል!

ኢትዮጵያዊ
የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት
በአማርኛ

$2.75

# ላንዳፍታ






ሰኔ/ሐምሌ
፲፱፻፹፱
፭ኛ ዓመት
ቁጥር 6



# LANDAFTA

An Ethiopian Cultural Magazine In Amharic
(Amharic is the Official Language of Ethiopia)

JUNE/JULY 1997 Vol. V - No.6

**Patrick A. Harton**
*Partner*

**Teketel Wegayehu**
*Legal Asst.*

# Harton & Henry

Attorneys At Law

**Samuel C. Henry**
*Partner*

**G. Angela Harton**
*Office Mgr.*

## "A Law Firm Proudly Serving the Ethiopian Community"

በየትም ቦታና ጊዜ ለሚያጋጥምዎ አጠቃላይ የሕግ ችግሮች
ምንም ነገር ከማድረግዎ በፊት በሕግ ምክርና የጥብቅና አገልግሎት
የታወቀውን የሐርትንና ሔነሪ የጥብቅና ድርጅት
በማነጋገር ለችግርዎችዎ በሙሉ አስቸኳይ መፍትሔ ያግኙ ·

- Auto Accident
- Immigration Law
- Personal Injury
- Business Law
- Divorce
- Criminal Law

- Ethiopian National with extensive knowledge of Ethiopian history, laws, language and culture on staff

## Free Consultation

**70 Fairlie Street Suite 260, Atlanta, Georgia**

**40 ◆681◆1 00**

# ኤክስፕሬስ
## የገበያ አዳራሽ መዝናኛና የባህል ምግብ ቤት
# EXPRESS FOOD MART

በቅርቡ ሥራውን የጀመረው ድርጅታችን የደንበኞቹን ፍላጎት ለማርካት በልዩ ዝግጅትና መስተንግዶ ተቀናብሮ ቀርቧል። የምግብ ማጣፈጫ ቅመማ ቅመም ከማቅረብ ሌላ ትዝታ ቀስቃሽ የባህል ምግቦችን ተወዳዳሪ በማይገኝላቸውና የረጅም ጊዜ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች እያዘጋጀ ያቀርባል። በተጨማሪም የመዝናኛ ክፍላችን ሌሎች አገልግሎቶችንም ለመስጠት በዝግጅት ላይ መሆኑን በደስታ እንገልጻለን።




For your Pleasure
we also carry:
- *Video sales & rentals*
- *Audeo cassettes*
- *Compact Discs*
- *Ethiopian Magazines*

**የአገራችንን ምግብ ለመሥራት**
**የሚያስፈልጉ ነገሮች ሁሉ ቀርበዋል፤**

1. በርበሬ
2. ምጥን ሽሮ
3. ሽሮ
4. አዋዜ
5. የቅቤ ቅመም
6. ጤፍ
7. መከለሻ
8. ምስር ክክ
9. አተር ክክ
10. ቅንጨ
11. የገንፎ ዱቄት
12. የአጥሚት ዱቄት
13. በሶ
14. እንጀራ
15. ጠላ
16. ጠጅ

በተጨማሪ ለክትፎ፤ ለጥብስና ለጥሬ
የሚሆን ወደር የማይገኝለት ሥጋ

Recreation Room Services Include:
- *Table Tennis*
- *Billiard*
- *Pin Balls*
- *Video Games*
- *Other Indoor Games*
- *Coffee & Tea*

መጥተው ይጎብኙን!!
በመስተንግዶአችን ይኮራሉ።
ሰፊ የመኪና ማቆሚያ
ስላለን አይቸገሩም።

**EXPRESS FOOD MART**
4959 - C Memorial Drive
Stone Mountain, GA 30083
Phone: (404)299-6800
Fax: (404)325-7344

# ማ ው ጫ CONTENTS


3 ከአዘጋጁ

4 ሰላምታ ከወደ አገር ቤት (ወርቃየሁ)

5 ሰላምታ ከባህር ማዶ (ገብርዬ)

13 ከአንባብያን

15 የወያኔ አፓርታይድ አገዛዝ በመቃወም ...
(ዓለም አቀፍ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ)

20 እንዲህ ሆነ (ከዜና ማህደር)

25 የኢትዮጵያ አንድነት ግንባር ሠራዊት መግለጫ

27 የሲቪክስ ድርጅቶች ሚና
(ዶ/ር ጌታቸው መታፈሪያ)

32 ልብ ወለድ – ያዳፈኑት እሳት
(ሰይፉ ብሻው)

40 የግጥም ጉባኤ

44 ዜና ቤተ ክርስቲያናት

45 እንደው ለምክር ያህል

46 ከአበው (መጋቢ አእላፍ መክብብ አጥናው)

47 የሰንጠረዥ ጨዋታ




ዓለም አቀፍ የተቃውሞ
ሰላማዊ ሰልፍ





የኢትዮጵያ አንድነት
ግንባር ሠራዊት (25)


ላንዳፍታ የግል መፅሔት ናት። የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ የአዘጋጁን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሑፎቹን በሬዲዮ፤ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የፀሐፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የፈጠራ ድርሰቶች መብታቸው በሕግ የተጠበቀ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1997

ላንዳፍታ
ሰኔ/ሐምሌ ፲፱፻፹፱
5ኛ ዓመት ቁጥር 6
LANDAFTA
June/July 1997 Vol. V - No.6

አዘጋጅና አሳታሚ
መኮንን ገሠሠ

**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*

**Assistant Editor:**
*Genet Wolde*

**Contributors:**
*Workayehu (pen name)*
*Gebrie (Pen Name)*
*Girma Zegeye*
*Seifu Mekuria*
*Saefu Bishaw*
*Wuhib Tiruneh*
*Eyayu Belelgne (pen name)*
*Rev. Mekbib Atnaw*

**Editorial Advisors**
*Lisanu Simret*
*Dr. Abera Molla*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Solomon Melesse*
*Dawit Deres*

**Distribution**
Atlanta, GA
California Mart
Sweet Auburn Grocery
H & B Shop
Nazareth Restaurant
Express Food Mart
Merkato Market
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
Dallas, TX
Maru Grocery
Abeba Grocery
Durham, NC
Blue Nile Eth. Cusine
Denver, CO
Emebet Worku
Houston
Queen of Sheba Rest.
Maru Grocery
L.A., CA
Merkato
Coffee Damera
Oak Land, CA
Albo-African Shop
San Diego, CA
Axum Market
San Jose, CA
St. Claire News Stand
Seatle, WA
Arat Kilo Deli Grocery
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN
Merkato
Washington D.C. area
Addisu Gebeya
Nini Market (Alex.)
Tana (Silver Spring)
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu
London

# ከአዘጋጁ

እንደምን ከርማችኋል። ይኸው ብቅ ብለናል ደግሞ።

የኢትዮጵያ ጉዳይ በጣም አሳሳቢ ደረጃ በደረሰበት በአሁኑ ወቅት ኢህአዴግ/ወያኔ ሥልጣን የያዘበትን 6ኛ ዓመት ተቋውሞና ብሶትን ለማሰማት የተዘጋጀው ዓለም አቀፍ ሰላማዊ ሰልፍ በተሳካ ሁኔታ መካሄዱን (ከአዲስ አበባ በስተቀር) የሚገልጽ ሰፋ ያለ ዜና ይዘን ቀርበናል። የላንዳፍታ መጽሔት ይህን የተቃውሞ ሰልፍ ለማዘጋጀት በተቋቋመው ዓለም አቀፍ ጊዜያዊ ኮሚቴ አባል በመሆን ከሌሎች የፓለቲካ፤ የሲቭክና የሚዲያ ድርጅቶች ጋር ሆና አስተዋጽዖ በማድረጓ ከፍተኛ ኩራት ይሰማታል። መጠነኛ ልዩነትን በማቻቻል አገርን ከጥፋት ለማዳን በሚደረጉ የጋራ ጥረቶች ላይ ሁሉ ያልተቆጠበ አስተዋጽዖዋን ታደርጋለች። የአገር አጥፊዎችንም ደባ ከማጋለጥ ወደ ኋላ እንደማትል ታረጋግጣለች።

በዛሬው እትማችን የአገራችንን ጉዳይ በተመለከተ ሌሎችም የተለያዩ ሰፋ ያሉ ዘገባዎች ይዘን ቀርበናል። ቀደም ሲል ባሉት እትሞቻችን ስለሲቪክ (ብዙሃን) ማህበራት ወቅታዊነትና አስፈላጊነት ገብርዬ በጀመረው ሃሣብ ላይ ጌታቸው በጋሻው አክሎበት በብዙዎቻችን ዘንድ ትልቅ የውይይት መድረክ መክፈቱ ተሰምቶናል። ይኸው ውይይት ጠለቅ ባለ መልኩ እንዲካሄድ በማሰብ የፖለቲካ ሣይንስ ምሁር የሆኑትን ዶክተር ጌታቸው መታፈሪያን ቃለ መጠይቅ አቅርበንላቸው ያገኘነውን ግንዛቤ አያይዘናል። በቅርቡ ተጋድሎ የጀመረው የኢትዮጵያ አንድነት ግምባር (ኢአግ) የሰጠውን መግለጫ ከተላከልን ፎቶግራፍ ጋር አቅርበናል።

ስለ መጽሔታችን መስጠት የምትፈልጉት
አስተያየት ወይም በመጽሔቱ እንዲወጣ
የምትፈልጉት ጽሑፍ ካለ በአድራሻችን ይላኩልን።

የላንዳፍታ መፅሔት ዝግጅት ክፍል
LANDAFTA
P.O Box 49301, Atlanta, GA 30359
Phone: (404) 508-4657 Fax: (404) 508-2447
E-MAIL- mgessesse@aol.com
HOME PAGE:
http://www.ethiopic.com/landafta.htm

*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic. Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት
# ከወርቃየሁ

ሰላም አጋሮቼ እንደምን አላችሁልኝ? ኑሮና ብልሃቱስ እንዴት ያደርጋችኋል? እኔ ፈጥሮ የማይረሳው አምላክ ምስጋና ይግባውና እስካሁን አለሁ፣ ደህና ነኝ እላለሁ።

ገብርዬ! እናንተ በዓለም ዙሪያ ያላችሁት ሁሉ በኢትዮጵያዊ ወገኖቻችሁ ላይ እየደረሰ ያለው ችግርና ሰቆቃ፣ ስቃይና መከራ ... ተሰምቷችሁ በመቃወም ያደረጋችሁትን የተቃውሞ ሰልፍ ስሰማ እጅግ በጣም ኮራሁ! እሰየው ወገኖቼ ለካ አሉልን፣ አልረሱንም ብዬ በጣም ተደሰትኩ። ገብርዬ ምንም ቢሆን አለሁልህ የሚል አጋር በዚህ በቀውጢ ጊዜ ማግኘት ቀላል አይምሰልህ። ደግሞ ዘረኛው የወያኔ መንግስት ከውጪ አገር እየመጡ ንግድ በሚከፍቱ ሰዎች እያመካኘ ይኸው ሰዉ ሁሉ አገሩ እየገባ ነው እያለ አገር ውስጥ ሰላም እንዳለ የሚያስመስለውን በማጋለጥ እናንተው እዛው ሆናችሁ ሰላም እንደሌለና አሁንም ኢትዮጵያ ትልቅ የችግር አዘቅት ውስጥ እንዳለች ለአለቆቹና ለአይዞህ ባዮቹ ጩኸታችሁን በማሰማታችሁ እሰየው ወገኖቼ አበጃችሁ አልኩ! ከአንጀት ካለቀሱ እምባ አይገድም ነውና ሰው ያለውን ባለበት ካደረገም አንድ ነውና ይህ ለእኛ ትልቅ የመንፈስ ሞራል ነው የሰጠን።

ገብርዬ! ምንም እንኳ አንዳንድ በውጪ የሚኖረው አበሻ ድሮ በደርግ ጊዜ ታግያለሁ የሚል ፈሊጥ ቢኖረውም፣ በድሮ በሬ ያረሰ የለምና ከዛሬ ሃያ ዓመት በፊት ስለታገለ ብቻ ዝንተ ዓለም ያ ታሪክ ሲዘከርለት እንዲኖር አይፈልግ፣ ይልቁንስ አሁን ከዛን ጊዜው በዕድሜው አድጉ፣ በዕውቀቱም በስሏልና ለእናት ሀገሩ የሚበጀውንና ሀገሩ ከዚህ አስከፊና መሪር ኑሮ የምትታደግበትን መንገድ ከወገኑ ጋር ቢመክር ይበጃል ባይ ነኝ። ደግሞስ ይኼ በየኬላው ስደተኛ ሆኖ የገባው ወገን በኢትዮጵያ ችግር ስም ያገኘውን ግሪን ካርድ በእጁ ካስገባ በኋላ ስለኢትዮጵያ አታውሩኝ፣ ፖለቲካ ሰለቸኝ ይብቃኝ ማለቱና አንተ እንዳልከው እንደግመል ሽንት ሁሌ ወደ ኋላ መጉተቱ የወያኔን ሰጥ ለጥ ብላችሁ ተገዙልኝ የሚለውን መርሆ የሚያራምድ መሆኑን አልተገነዘበውምን? ይህስ ከታሪክ ተወቃሽነት የሚያድነው ይመስለዋልን? ብቻ ኢትዮጵያ የወላድ መሐን አልሆነችምና ይኸው እንደዚህ ከጉን ደግሞ አለንልሽ የሚል ኃይል እየተነሳ ነው።

ለመሆኑ ገብርዬ ከተቃውሞ ሰልፍ መልስ በኋላስ ምን አስባችኋል? ምንስ ተነጋግራችኋል? ወይስ በአንድ ቀን ተቃውሞ ብቻ ወያኔ ስልጣኑን እንካችሁ የሚል መስሏችኋል? ምከሩበት ባይ ነኝ። ደግሞ ወያኔ በዚህ በተቃውሞው በጣም እየተደናገጠ እንደሆነ ልነግርህ እወዳለሁ። እና አሁንም በሁሉም ነገር እንደዚሁ በርቱልኝ እላለሁ። የተጫረው ካልነደደ በኋላ ረመጥ ሆኖ የበለጠ እንደሚፋጅ መገንዘብ ይኖርብናል።

ወዳጄ ገብርዬ! እኛ ግን «ተከለከለ አሉ፣ ቤትሽ እንዳመሉ» ሆነና ተከለከልን። ለ6 ዓመታት የተዳፈነ ስሜታችንን በኡኡታም ቢሆን ዘንድሮ ይወጣልናል ብለን የተዘጋጀን ብዙ ነበርን። ግን ምን ያደርጋል ወያኔ ከዚህ የበለጠ ነፃነትና ሰላም፣ ከዚህ የበለጠ ዲሞክራሲ ምን ለመሆን ነው ብሎ የታሰበውን ሰላማዊ ሰልፍ በስልጣኑ አገደ። የሚገርምህ ግን ኢህአዴግ ራሱ በቀረፀው ህገ መንግስት አንቀጽ 30(1) ላይ «ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው» በማለት የደነገገ ቢሆንም የወረቀት ላይ ዴሞክራሲ ብቻ ሆነና ፈቃድ ሊሰጥ አልፈለገም። ታዲያ የሆነው ይሁን ብለን ገፍተን እንዳንወጣ «አባብ ያየ በልጥ በረየ» ነውና ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ የደረሱትን አስከፊ ነገሮች ወደኋላ አሰብንና በጥይት ከማለቅ ብለን ለጊዜው ተውነው። ግን በወረቀቱም ሆነ በምኑ የተቻለንን ያህል ዕለቱን ተቃውመናል፣ ቀስቅሰናል።

ገብርዬ! የአገራችን ሁኔታ ከምንጊዜውም በላይ እየከፋ ሄዷል። ይባስ ብሎ እንደ ቀይ ሽብር ጊዜ ሰው በአደባባይ ይገደል ጀምሯል። ባለፈው በመምህራኑ ማህበር ም/ሊቀመንበር ላይ የደረሰውን ግድያ ሳትሰማ አልቀረህም። ከዚያም በኋላ 2 ሰዎች በፓስታ ቤት አካባቢ በጠራራ ፀሐይ ተገድለዋል። በተለያዩ ሶስት የንግድ ማዕከሎች (ጨርቆስ፣ በአዋሬ፣ በመርካቶ) ማን እንደለኮሰው ባልታወቀ ሁኔታ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ንብረቶች ጋይተዋል። የእሳት አደጋ መከላከያው የሚረጨው ቤንዚን ይመስል አንድም ሱቅ እንኳ ሊያድን አልቻለም። በዚህ ቃጠሎ ሳቢያ ስንቱ ቤተሰብ ባዶ እጁን ቀርቷል። ነጋዴዎች ባለፈው የንግድ ቤት ኪራይ ጭማሪን በመቃወም ባደረጉት የሱቅ መዝጋት አድማ በርካታ ነጋዴዎች የንግድ ፈቃዳቸውንና ሱቃቸውን ሲነጠቁ የተቀሩት ደግሞ ሁለተኛ የዚህ አይነት አድማ ቢያደርጉ የእነሱም ፈቃድና ሱቅ እንደሚወሰድ ፈርመው «የውሾን ነገር ያነሳ ውሾ ይሁን» ብለው ወደስራቸው ተመልሰዋል። የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችም ገበሬውን ለምን ደገፋችሁ በማለት ታስረዋል፣ ተደብድበዋል፣ ... ሌላም፣ ሌላም ሆነዋል። ሌሎችም እንዲሁ ... እና ይኸውልህ የእኛ ኑሮ ይህን እየመሰለ ነው። ወያኔ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ እምባገነንነቱን በሁሉም ዘርፍ እያሳየ ነው። እና ምን ይበጃል ትላላችሁ? «ቻለው፣ ቻለው» እንደማትለኝ ተስፋ አለኝ።

ገብርዬ! በመጨረሻ ስለደብዳቤ ልውውጣችን በማንሳት በዚያውም ትልቅ ትምህርት የሰጡንን አቶ ጌታቸው በጋሻው ለማመስገን ነው። እንዲያው አንዳንዴ ከአንተ ሌላ የሚጭር ሳጣ ይሄ ሁሉ ጥሁፍ የውኃ ላይ ኩበት ሆኖ ቀርቶ ይሆን እያልኩ አስብ ነበርና አጋር በማግኘትህ ደስ ብሎኛል። እንግዲህ እስቲ ሌሎቻችሁም እንዲሁ አለን በሉና!

በቸር ይግጠመን
ወርቃየሁ ነኝ ከሸገር

# ሠላምታ ከባህር ማዶ
# ከገብርዬ — ለወርቃየሁ

ወዳጄ ወርቃየሁ፤ ቸርነት የማያልቅበት አምላካችን ጠብቆህ ለበርካታ የደብዳቤ ልውውጥ በመብቃትህ ክብሩ ይስፋውና የምትኖረው በአንተ ትግል ብቻ እንዳልሆነ እረዳለሁ፤ ያባቶቻችንና የናቶቻችን አምላክ ይርዳህ፤ ለመሆኑ እንዴት ሰነበትክ?

ስለብዙኃን ድርጅቶች ከዚህ በፊት በገለፅኳቸው ዐበይት ጉዳዮች ላይ ጌታቸው በጋሻው ትምህርታዊ ቁምነገሮችን አስፍሯል። የፀረፍተ ነገሩን ክራር ቅኝት በቅኝት እየመታ በአንቀፆችም እየተከዘ ለአሁንም ሆነ ለመጭው ትውልድ እንደድምፀ መልካም አረሆና ክራርተኛ የብዙኃንን ስብስብ አወድሶታል፣ የትግልና የግምባር አጋዥነቱንም በማይጨበጥ ንድፈ ሐሳብ ብቻ ሳይሆን በገቢራዊነት አቀንቅኖታል። ጽሑፉ በግልፅነቱ፣ በአስተማሪነቱና በማመሳከሪያ ዋቢነቱ እጅግ ጠቃሚ በመሆኑ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሊወያይበት ይገባል። በተመክሮ፣ በፖለቲካዊ ክስተቶችና በተጓዳኝ ነባራዊ ሁኔታዎች ተመስርቶ የቀረበልን የጌታቸው በጋሻው መጣጥፍ ለሰብዓዊ መረዳጃና ለግምባር ምሥረታ ፍናቱን እንደላምባዲና (ባትሪ) ወለል አድርጉ የሚያሳይ ነው። ሳይከርና ሳይጉረብጥ በሚገባ ቋንቋና በሀገር መቆርቆር አንባቢን ስለሚኮረኩር ከራስ ጋር ያነጋግራል፤ ያነዛንዛል፤ እዚያው በዚያው መልሱን ሰጥቶ ካለ ሊቀመንበር ይዳኛል። የውይይቱንም አድማስ በማስፋት በታሪካችን ለፍትሕ አስተዋፅኦ ያደረጉትን በኢትዮጵያ የሠራተኛና የመምህራን ማህበራት በአርአያነታቸው ስለሚያነሳቸው በምዕራቡ ዓለም በስደት ለምናደርገው ትግል መነሻና መንደርደሪያን ይለግሰናል። ጌታቸው አንቂ የፍትሕ ብዕሩን ለሚወደው የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁንም ማሳየት አለበት። ወርቃየሁም ሳትመረምረው አልቀረኽምና ፀሐፊው እንደታሪክ ተመራማሪ ብቻ ሳይሆን እንደተሳታፊም ምሑራዊ መስተንግዶውን ከተመክሮው እያመሳከረ በስክነ አንደበት አደብ የገዛና ቁምነገራዊ ትንተናን (Serious analysis) አቅርቦልናል። በእውነትም በሥልተ—ተሞክሮ (PRAXIS) እና በአንክሮአዊ—ማሰላሰል (Critical Reflection) ያጌጠ መጣጥፍ ነው።

ወዳጄ ወርቃየሁ፤ ሰሞኑን የሞቡቱን መፈርጠጥና የሎሬንት ካቢላን ድል ሰማን። «ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም»ና ነው ነገሩ በጠመንጃ ኃይል የሞቡቱን ስልጣን የነጠቁት ካቢላ አንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሌሎችን ፓርቲዎችና ድርጅቶች እንዳይቀርቧቸው ገላምጠዋቸዋል። ዛየር እንደአብዛኛው የአፍሪቃ ሀገሮች (ኢትዮጵያንም ይጨምራል) የግፍና የስቃይ ሲኦል ናት። አውሮጳውያንና ዐረቦች የኮንጉን ወንዝ ካቋረጡ ጀምሮ የዛየር ስቃይና በሽታ ፀንቷል። የመብት መረገጥ አይሏል። ከአፍሪቃ ቅርምት በኋላ የአካይስት ሀገር ስለሆነችው ዛየር በርካታ ፀሐፊዎች ብዙ ገጥመዋል። ከተፃፉት ውስጥ እነዚህን ሁለት ግጥሞች መርጫለሁ። ግጥሞቹ በውርስነት የተተረጐሙት በልሳኑ ሥምረት ነው።

የሊዮፓልድ ውቃቢ

ኧረ ምነው ሳምላክ ብላችሁ፥ ውቃቢውን እንኳ አዳምጡት
የሊዮፓልድን አስፈሪ መንበር፥ ጊዜ ሠርቃችሁ ባይሆን ቃኙት
አጥፍቶ እርሱም ለጠፋው፥ ለሚጮኸው በገሀነመ እሳት
እንግዳ ተቀባይ አሽከሩን፥ እጁን ቆርጦ ለጣለበት፤
አካይስቱም በምላሽ፥ ባጠፋው ፈርደውበታል
እየጮሁ በአስረሽ ምቺው፥ እጁን ሁሉ ጉማምደውታል
እየገዘገዙ ቅልጥሙን፥ በገሃነም ያሽካኩበታል
— ቫሼል ሊንድሲይ፣ «ኮንጉ»

አቤት ጥርስ ማፋጨት
አቤት የሲኦል ጩኸት።
— ጆሴፍ ኮንሬድ፣ «የጭለማ ልብ»

እንደሌሎች የአፍሪቃ ሀገሮች የዛሬዋ ዛየር የድሮዋ ኮንጉ ከገሃነመ እሳትነት ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ፍንክች አላለችም። ከአፍሪቃ ባሕል፣ ወግና አስተዳደር በመለስ የሲቪየት ኀብረገነን መንግሥት (Totalitarianism) ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያምን በምስላቸው እንደሰሩት ሞቡቱንም እንደጭቃ ጠፍጥፈው የበየዱት ምዕራባውያን ናቸው። በጠበንጃ ኃይል፣ በሀገር—በቀል ምሁራን መሣሪያነትና በባዕዳን የበላይ አስተባባሪነት አፍሪቃ በርካታ መሪዎችን በአብዮትና በለውጥ ስም መልሳ መላልሳ በልታቸዋለች። ከወደሙም በኋላ ታሪካቸውን በተገኘነት በአምሳሏ ቀርፃቸው ተርካለች። ለዚህም ነበር የአሜሪካው ፖለቲከኛና «ቀኝ ቀመስ» ምሑር ዢብግኒው ብሬዥኒስኪ (Zbigniew K. Brezinski) "ታሪክ የእንቅስቃሴ ደቀ—መዝሙሮችን በነፍሳቸው ተጫውታበታለች" ያሉት። በእርግጥም የሚስተር ብሬዥኒስኪ ወገናዊ «እውነተኛ» መሰል አባባል ለማርክሲስት ቀመስ ግራ ኃይሎች ቢሆንም ለሦስተኛ ዓለም ለውጦችና እንቅስቃሴዎችም በደፈናው የተነገረ ይመስላል። ወደእርሳቸው የምዕራባውያን መንግሥታት የበላይነት ትንተና ቤት ጭልጥ ብለን ባንገባም ሀሳባቸው በተቃራኒነት በሕዝቦች እንቅስቃሴ ላይ ቢያተኩርም መሠረታዊ እውነትነት አለው። ለምን ማለት ደግ ነው። አብዮት በእንቅስቃሴ መሪዎች ነፍስ ተጫውታለች። እነመንግሥቱን፣ እነዚያድባሬን፣ እነሞቡቱን…ወዘተ አሳፍራና አዋርዳ መቀመቅ ከታለች። ጊዜው ሲደርስ ሰው አቃጥለው እነርሱም ከስመዋል። የገነቡት መዋቅርና የጦር ሠራዊት ወድሟል። ዛሬም በአፍሪቃና በሌሎችም ሦስተኛ ዓለም ሀገሮች በጠበንጃና በመፈክር ስልጣን ላይ የተቆናጠጡ መሪዎች ይወድማሉ። መለስ ዜናዊም ኢሳያስ አፈወርቂም ይወድማሉ። የጊዜ ጉዳይ ነው። እንደመድኃኒት የመደርደሪያ ሕይወት (Shelf life) ዲክቴተሮች በኃያላን መንግሥታት መደርደሪያ የማብቂያ የጊዜ ሕይወት (Expiration Date) አላቸው። በተመክሮ እንደታየው ይህ የማብቂያ ጊዜ ግፋ ቢል በማዕከላዊ ደረጃ ሲታይ ከ20 ዓመት አያልፍም። ኃያላን መንግሥታት በእጅ አዙር ሕዝቡን በጦር መሣሪያና በገንዘብ ኃይል ቢገዙትም ልቡንና ማንነቱን አያጠፉትም። ለዚህም ነው የዲክቴተሮች የመደርደሪያ ሕይወት (Shelf life) ዘለዓለማዊ የማይሆነው።

ወዳጄ ወርቃየሁ፣ የመንግሥቱ ኃይለማርያምን፣ የሞቡቱንና የመለስ ዜናዊን አነሳስና አካሔድ ስንመረምር ያለፈውን ከወደፊቱ በማያያዝ ትንቢትን ለመናገር አያዳግተንም። መንግሥቱ ኃይለሥላሴን ገሎ 20 ዓመት ከገዛ በኋላ ዕልቂት አድርሶ፣ እርሱም በኃያላን መንግሥታትና በወያኔ ሸር ተሸርቦበት ወደ ዚምባብዌ ሸሸ። በጫማው የተተካው የጎሳ እኩይ መሠሪ መንግሥት በሌላ ፍርጥም አምባገነን ተደርምሶ እንደሚሸሽ ወይም እንደሚሞት የሁኔታው አረማመድ ራሱን እየከሰተ ነው። ታሪኩ የተፃፈ ነው። የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ እስካለ ድረስ የሦስተኛ ዓለም መንግሥታት ቋሚ አይሆኑም። በሦስተኛው ዓለም የሕዝብ ፍላጉት፣ ኢኮኖሚያዊና

ፖለቲካዊ ጥያቄ የሚያበቃ አይደለም። የሕዝብ ልብ ከኃያላን መንግሥታት ቁጥጥር ውጪ ነው። ይህ ሂርዮሽ በሦስተኛው ዓለም ሊቆም የሚችለው በኃያላን መንግሥታት ሀገሮች የሚኖሩ ሕዝቦች ሲነቁና በአንድነት በሦስተኛው ዓለም የሚካሄደውን ፖሊሲ ሲቃወሙ ነው። ሰብዓዊ መሪዎችን ስልጣን ላይ ሲያወጡ ነው። ይህ አስተሳሰብ ከማርክስም ይለያል። የአሜሪካንን መራሽ የመከሊት ፖሊሲ ሰንኮፉን የሚነቅለው ሕዝቡ ነው። ይህ ማለት ግን በሦስተኛ ዓለም (በኢትዮጵያ ለምሳሌ) የሚደረገው ትግል አይፋፋም ማለት አይደለም። በብሔራዊነትና በፍትሕ ላይ የተመሰረተ የሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ትግል (Pan Ethiopianist) መጧጧፍ አለበት። ነገሩ በአጠቃላይ የሦስተኛ ዓለም የመንግሥታትን ሁኔታ ለማሳየት የቀረበ ነው።

ወደ መንግሥቱ፣ ሞቡቱና መለስ የታሪክ ትንተና እንመለስ። ጆሴፍ ካሣ ቩቡና ሞቡቱ ሴሴኮም፣ ፓትሪስ ሉሙምባን ከሲአይኤ ጋር በመተባበር ገድለው የእርዛትና የአፋኝ መንግሥት አቋቋሙ፤ ብዙ ንብረት ከበዘበዙ በኋላ አገር አውድመው ሞቡቱም ፈርጥጠዋል። ኢዲአሚን፣ ዚያድባሬ፣ ፈርዲናንድ ማርቆስ እና እንደዚሁም በምዕራቡም የጥቁር ሀገሮች እነ ቤቢ ዶክ ዱቫልዬ (ሔይቲ) የሀገራቸውን ሕዝብ አስበልተውና ግጠው ጠፍተዋል። ዛሬም በናይጄሪያ፣ በሴራሊዮን፣ በላይቤሪያና በሌሎችም ሦስተኛ ዓለም ሀገሮች አየሩ በደም እንፋሎት ጉምና በህፃናት እምባ ተሸፍኗል። ኃያላን መንግሥታት ሀገራቸው የፈጠሩትን ቀውስ በድኃው ወንጀለኝነትና በግብረሠናይ (welfare) መርኃግብሮች እንደሚያሳብቡ ሁሉ በፈጠሩት የከፋፍለህ ግዛው መቅሰፍት ራሳቸውን ሳይወቅሱ የአፍሪካ ሕዝቦችን የሶሺያልና የፖለቲካ ቀውስ በደፈናው በጉሳ መለያየት ላይ ያሳብባሉ።

ወዳጄ ወርቃየሁ፣ የአፍሪቃ መሪዎች አሸሻሸት ዘይቤ ራሱን የቻለ የታሪክ ስልትና «ተለምዶአዊ» ሂደት አለው። የአፍሪቃ ዲክቴተሮች መግዛት ሲያቅታቸው እንዲሸሹ መንገዱን የሚያመቻችላቸው የምዕራቡ ዓለም የስለላ መዋቅር ነው። በእኛም ሀገር ኮሎኔል መንግሥቱን እንዲኮበልሉ ግፊት ያደረጉት ምዕራባውያን ናቸው በማለት የሚያብራሩ ጠበብቶች አሉ። ኮሎኔል መንግሥቱ የመሰረቱት የቦላዔ–ሰብ መንግሥት አረመኔና ጨካኝ ቢሆንም እርሳቸውን ከሀገር ለማስወጣት ተሸረበ ስለተባለው የምዕራባውያን ደባ ከሀገር ጣልቃ ገብነት አንፃር ሲመረመር በርካታ አገር ወዳዶችንና ብሔራውያንን (Nationalist) አሳዝኗል። የነሔርማን ኮሽን ተንኮል ለዘለዓለሙ በኢትዮጵያ ታሪክ የማይረሳ ጥቁር ነጥብን ጥሎ አልፏል።

በተደጋጋሚ እንደገለፅኩት የሞቡቱ ክሌብቶክራሲ (ሌኩይ መደብ) እና የመለስ ዜናዊ የጎሳ መደብ የሚመሳሰሉበት መንገድ ለመናሩ በርካታ ዋቢዎችን መጥቀስ ይቻላል። የዲክቴተሮች ጥንካሬ ለተወሰነ ጊዜ ነፍሱን ዘርቶ የሚቆመው በውጭ የዕርዳታ ኃይል ነው። ብድር፣ የገንዘብ ችሮታና የጦር መሣሪያ የአምባገነኖች መመኪያዎች ናቸው። አይኤምኤፍና የዓለም ባንክ በብድር ችሮታ ትርፋቸውን የሚያካብቱ፣ በሦስተኛው ዓለም ሕዝብ ብሶትና ላብ በተሰበሰበ ግብር ኃብታቸውን የሚያዳብሩ የአራጣ ድርጅቶች ናቸው። «ወይ አበዳሪ ይሞታል፣ ወይ ተበዳሪ ይሞታል» የሚለውን የደግ ዘመን የልምድ ጥቅስ ዋጋ ቢስ ያደረጉት እነዚህ ድርጅቶች ሳንካቸውና የወለድ አገድ ጠሳቸው ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍና ሀገርን የሚጉዳ ነው። ከዋጋ ግሽበት በላይ (Inflation) በርካታውን እጅ ወይም የሀገሪቷን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ምርት (GNP-General National Product) ለባዕዳን በማስበላትና የህዝባቸውን ወገብ በማጉበጥ የብድሩን ወለድ ለመክፈል የሚንገዳገዱ ድኃ ሀገሮች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። አይኤምኤፍና የዓለም ባንክ ብድር ሲሰጡ ድሃ ሀገሮች ማሟላት የሚገባቸውን ተግባራት አብረው ከ«ዕርዳታው» ጋር ግዳዊ ያደርጉታል። በመዋቅራዊ ማስተካከል (Structural Adjustment) ስም ሠራተኞች በግፍ ማንቁርታቸው ታንቆ ከሥራ ይባረራሉ። የሀገር የማዕድናት መጠባበቂያ ኃብትና ንብረት (Reserve) በአራጣ መልክ እንዲከፈል ውል ይደነገጋል። አንዲት ሀገር ለውጭ ገበያ የምታቀርበው ጥሬ ሀብት (Commodity) ካለ እርሱም ጌቶቹ (አበዳሪዎቹ) በፈለጉት ዋጋ እንዲገዙ ስምምነት ይደረጋል። ስምምነቱ ከኒውዮርክ፣ ሉንዶንና ቶኪዮ ከሚለወጡት የብር ለውጥ መስፈርቶች (Stock Exchanges) በተለየ መንገድ ይዋቀራል። በተለይም የአንዲት ሀገር የውጭ ምንዛሪ በአንድ ጥሬ ሀብት ላይ የተመሠረተ ከሆነ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በጥቂት አመታት ውስጥ ይንኮታኮታል፤ ለወደፊቱም ለማገገም አይችልም። ይህም ገዳይ የኢኮኖሚ ውል («የኢኮኖሚ ተራድዖ» ይሉታል)፣ በስራ እንዲውልና ዓለም አቀፍ ተደጋጋፊ ባለመከሊቶችና አልሚዎች (Investors) ስራቸውን በተመቻቸ (በተረጋጋ) ሁኔታ እንዲያከናውኑ ተቃዋሚ ሀገር ወዳድ አመፅ እንዳይነሳ የጦር ቃልኪዳንና የፖሊስ ተራድዖ በስምምነቱ ውስጥ ይታከላል። በመድኃኒት ምትክ ቦምብ፣ የእምባ ጢስና ታንክ ይታደላል። በእርሻ ልማት ማስልጠኛ ተቋም ምትክ «የወንጀል» ምርመራ ማዕከል ይቋቋማል። ነፃ የሕዝብ ማኅበሮችን ለማዋቀር ከሚረዳ ጥናትና ምርምር ክፍል ምትክ የምዕራቡን ዓለም የበላይነት የሚያረጋግጡ መጽሐፍት ቤቶች፣ ትያትሮችና የሲኒማ ቤቶች ይታነፃሉ። ሕዝቡ ለፍትሕ እንዳይነሳሳ በውጭም ሆነ በሀገር ቤት የምዕራቡ የስለላ ድርጅቶች ከመሰሎቻቸው ጋር ስማበር የታዮችንና የጋዜጠኞችን መብት ያፍናሉ። እንግዲህ በዚህ የደም ገንዘብ ምሁሩ ይታነቃል፣ ካስፈለገም በረቀቀ ሳይኮሎጂያዊ ዘዴ የሊቆች የአንቂነት መብራት ይደበዝዛል፣ ሞራላቸው በግላንግስ ላሽቆ የተፋላሚነት ስለታቸው ይደንዛል፣ ሕዝብ ይጨፋጨፋል፣ ነባር ባህልና ኃይማናት ይጣጣላል። የኢኮኖሚም ጥቅም ለመከላከያ ኃይሉና ኮትኩተው ላሳደጉት ውሱን የጉሳ ወይም በጥቅም ለተወሳሰቡ ክፍሎች መበልፀጊያ ይውላል። የኢትዮጵያ እኩይ የጉሳ መደብ ይህንን ንብረትና ገንዘብ እንዴት ይጠቅማል? በኢትዮጵያ ሬጂስተር በማስረጃዊ ሰነዶች እንደቀረበው የኢትዮጵያ ሐብትና ገንዘብ ለሕዝብ ጥቅም ሳይሆን ለወያኔና ለሻቢያ ኮንትራቶች፣ ኮንሴስንስ፣ ኢንቬስትሜንት፣ የግል ንብረትና የኪራይ ልማት ይውላል። ለፖለቲካ ደጋፊዎች መጉራረስ በተራቀቀ መንገድ እንደቅርጫ ስጋ ይታደላል። በዚህ የብድርና የ«ተራድዖ» ገንዘብ የሚበለፅጉት የወያኔ ትግሬዎች፣ የሻቢያ ካድሬዎችና ለስልጣኑ ያጉበደዱ ሌሎችም የመደቡ አባላት ናቸው። የዚህ ዓይነት አዲስ መደብ ከ1960ዎቹ አመታት በኋላ በአፍሪቃ የተከሰተና ከዓለም መከሊተኞች ብድርና የገንዘብ ዕርዳታ ለማግኘት በመደራደር ስልቱ ያደገና የሰለጠነ፣ ልዩ ልዩ ዓለም አቀፋዊ የብድርና የዕርዳታ ጥቅሞችን ለመዋዋል ከኃያላን መንግሥታት ጋር ችኮና ነዝናዥ የድርድር ታክቲኮችን (Shrewd Negotiating Tactics) የሚጠቅም የኅብረተሰብ ስብስብ

ነው። ታዋቂ የላቲን አሜሪካ የኢኮኖሚ ሊቃውንት ይህንን ስብስብ እኩይ መደብ (Cleptocracy) ብለው ሰይመውታል። በሀገራችንም ሁኔታ ጉሳን ስለሚጨመር የጎሳ እኩይ መደብ በማለት አቻ ቃል ለማግኘት ሞክሬያለሁ። የነዚያድ ባሬ፤ የነዳንኤል አራፕሞይ፣ የነሞቡቱ፤ የነካቢላ (በሁቱና ቱትሲ ነገር አመለካከታቸው)፤ የሳሙኤል ዶ...ወዘተ መንግሥታት ከነዚህ ተለይተው የሚታዩ አይደለም።

አንጀቴ ወርቃየሁ! ምንም እንኳን በሕዝብ ድምፅ ሳይሆን ርዕሰ ብሔርነታቸውን በጠበንጃ አፈሙዝ የተቀዳጁት ሎሬንት ካቢላ «በዛየር ጉዳይ የውጭ ጣልቃ ገብነትን እንቃወማለን» በማለት በቅርቡ ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጡበት ወቅት ብዙ የአፍሪቃ የፖለቲካ ትዕይንት ታዛቢዎች ተገርመዋል። ካቢላ እንደሞቡቱ ብድርና የውጭ ዕርዳታ ካላገኙ ስልጣን ላይ አይቆዩም። ለሦስተኛ ዓለም መሪዎች ይህ ግዳዊ ነው። ነገሩ «በማን ላይ ቆመሽ እግዚአብሔርን ታሚያለሽ» ነውና እንኳን አሁንና፤ አዲሱ የዓለም አቀፍ ሥርዓት (New World Order) የሦስተኛ ዓለምን አፍንጫ ሰንጉ በጡንቻውና በገንዘቡ በተቆጣጠረበት ወቅት ይቅርና በምዕራቡና በምስራቁ አፍላ የቀዝቃዛው ጦርነት ሽኩቻ ጊዜ እንኳ ዛየር ነፃነቷን ጠብቃ አልኖረችም። እንዲያውም የዛየር እኩይ መደብ (Cleptocracy) የአይኤምኤፍንና የዓለም ባንክን ገንዘብ አበዳሪዎቹ በሚፈልጉት መንገድ ስላልከፈለ የሀገሪቷን ነፃነት በግልፅ በአደባባይ አደጋ ላይ በመጣል በዓለም መክሊተኞች የተሾመ (የሀገሪቷ ተወላጅ ያልሆነ) የፋይናንስ ከፍተኛ ባለስልጣን እንደነበረ ታሪክ ዘግቦት አልፏል።

የሎሬንት ካቢላ ጋሻ ጃግሬና ጠቅላይ ፀሐፊ ዲዮ ቡጌራ በተለመደው ስልጣን ቋመጥ የአፍሪቃ በረሽኞች ቅጥፈት «ሁሉንም የሕዝብ ክፍሎች የሚያቅፍ አዲስ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋማል፤ የተሳካ ምርጫ ግን ሀገር እስከሚረጋጋ መጠበቅ አለበት፤ ከምርጫ በፊት ዝግጅትና ስነልቦናዊ መሰናዶ ያስፈልጋል፤ ለምዕራባውያን የዕርዳታና የምርጫ ፕላን ፍንክች አንልም» ብለዋል። መንግሥቱም፣ መለስ ዜናዊም፣ ኢሳያስ አፈወርቂና ሌሎችም አምባገነኖች ሺህ ጊዜ የመላለሱት የማደናገሪያ ቃል ነው። «የተሳካ ምርጫ ግን ሀገር እስከሚረጋጋ መጠበቅ አለበት» የሚለው የፖለቲካ ሽሙጥ ስልጣን ቋማጭ በረሽኞችን ለስልጣን መደላደል ቅድመ-ዝግጅት የሚረዳ ነው። ከሀገር ወዳድ መፈክር ጋር ተደባልቆ ይህ ፕሮፓጋንዳ (ቡጋንዳ) ይረጫል። ወታደራዊ የደርግ መንግሥት ስልጣን ላይ ሲወጣ «ካለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም»፣ ወታደሩ ሀገር ሲረጋጋ ስልጣኑን በህዝብ ለተመረጠ መንግሥት በማስረከብ ወደጦር ካምፑ ይመለሳል» ብሎ ነበር። በሂደቱ ግን እያደር እየዋለ ተጠናከረ። ህዝብን አፈነ። ካለምንም ደም ባለበት አፉ ቀይ ሽብርን አወጀ ብዙ ደም አፈሰሰ። በግዳጅ ምርጫ በራሱ አምሳል በቀረፃቸው የገበሬ፣ የሠራተኞችና የቀበሌ ማኅበራት በሥልጣን ተቆናጠጠ። መለስ ዜናዊም ከለንደኑ ስብሰባ በኋላ ኤርትራን በውሸት ሪፌረንደም አስገንጥሎ ጥቂት ከቆየ በኋላ በክልል ክፍፍል፣ በጉሳ ቅስቀሳ፣ በጠበንጃና በተቆጣጠራቸው የመገናኛ አውታሮች አጋዥነት የይስሙላ ምርጫ (SHAM ELECTION) አካሂዶ ራሱን አደላደለ። እንደሞቡቱ ክሌብቶክራሲ ገና ከጅምሩ «ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ» እንዲሉ የዓለም መክሊተኞችን የገንዘብ ዕርዳታ፣ በጉሳዊ ሙዳዩ (Ethnic Depository) ከቶ እንደውኃ ቧምቧ እየከፈተና እየዘጋ እንደአመቺነቱ በብልጠቱ ለደጋፊዎቹ አዳረሰ፤ በህዝብ ፕሮጀክት (ስራ) ስም የጉሳ ካድሬዎች በብር ናጠጡ፤ ኩባንያዎች በተለጣፊነትና በፊት ለፊት አደናጋሪ ስም (Front Names) በአዲስ አበባ፣ በመቀሌ፣ በአስመራና በድሬዳዋ እንደአሸን ፈሉ። በአንፃሩም በተበጣጠሰ ላስቲክና በክርታስ በተሰሩ ቤቶች ገበናኛው ጦም አዳሪ ህዝባችን በውርጭና በበሽታ ተሰቃየ፤ ጃንሜዳ በቦላዔስብ ደርግ ጊዜ የሚሊሺያ ማሰልጠኛ ያልሆነችውን ያህል በዚህ የጉሳ ነፍሰ በላ መንግሥት፥ የረሀብተኞችና የአካለ ስንኩላን መሰብሰቢያ ሆነች።

ወዳጄ ወርቃየሁ!

እኩይ የጉሳ መደብና እኩይ መደብ በባዕዳን የመክሊትና ወታደራዊ ዕርዳታ ድሐውን ህዝብ መውጪያና መግቢያ አሳጥተውታል። በታዳጊ ሀገሮች ይእነዚህ መንግሥታት አነሳስና ተግባር ሲመረመር ለህዝባቸው የቆሙ «ብሔራዊ» መንግሥታት ናቸው የሚለው ሐሳብ ተቀባይነት የለውም። የዓለም አቀፍ አዲሱ ሥርዓት (New World Order) ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በብሬተንውድስ ከተጠነሰሰ ጀምሮ ነፃ ኢኮኖሚን የገነባ የሦስተኛ ዓለም ሀገር የለም። ሊቢያ፣ ብሩናይ፤ ኩዌትና ሳውዲ አረቢያ ከሌሎቹ ሻል የሚሉት ዘይት ስላላቸው ብቻ እንጂ የኃያላን መንግሥታት ብድር ረድኤታቸው አይደለም። ነፃ ኢኮኖሚንስ መገንባት ይቻላልን? እነዚህስ ክስተቶች በዓለም አቀፍ ገበያ (International Market) በግዳዊነት የሚመጡ አይቀሬ ጉጂ ሁኔታዎች ብቻ ናቸው ወይስ ነፃነትን ለማይሸጥ ኢኮኖሚ አማራጭ በር አለ? አበዳሪዎችን አታሎ ብድራቸውን እየከፈሉ ነፃ ኢኮኖሚ መገንባት ይቻላልን? በመሠረታዊ የንድፈ ሐሳብ ጥያቄ ለምሳሌ ከኃይማኖት ትምህርት አኳያ ሲታይ ዲያብሎስን ማታለል ይቻላልን? መልሱ እጅግ አስቸጋሪ ነው። በርካታ ኢኮኖሚስቶች (አጠቃላይ ማለት ይቻላል) አዛዥ ኢኮኖሚ (Command Economy) እርባና ስለሌውና ስለወደቀ ቅልቅል ኢኮኖሚ (Mixed Economy) አማራጭ ነው ይላሉ። እዚህ ላይ እነዚህ ኢኮኖሚስቶች ያልተረዱት አዛዥ ኢኮኖሚ በዓለም አቀፍም ሆነ በሀገር ውስጥ ደረጃ ሙትና በድን መሆኑን ነው። ስለሆነም በቅልቅል(ቅይጥ) ኢኮኖሚ ውስጥ የሰይጣን ነፍስ ዘርቶ የሚያይለው የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ነው። በዚህ ፅንሰ ሀሳብ መሠረት አዛዥ ኢኮኖሚ ባዶ ነውና ከግል ኢኮኖሚ ጋር ሲደመር የስሌቱ ውጤት የሚያጋድለው ወደ ግል ንብረትነት ነው። የግል ንብረት ዓለም አቀፍ ኃይሉ ዐቢይ ነው። የአዛዥ ኢኮኖሚ ኃይል እስከነአካቴው ባዶ ባይሆንም ባለው ዓለም አቀፍ ሁኔታ አስተዋጽኦው እጅግ የበነነና የማጨ በመሆኑ የሚጫወተው ሚና ከመጤፍ የማይቆጠር (insignificant) ስለሆነ ቅይጥ በሚባለው ኢኮኖሚ ውስጥ ሚና የለውም። ቅይጥና አዛዥ ወይም የግል ኢኮኖሚ ሲባል ቢሮክራሲውን፣ አስተዳደሩን፣ ትስስሩን፣ ባህሉን፣ የተያያዙ ተቋሞችን የሚያጠቃልል ነው። ስለሆነም የመደመር ስልቱ በቀላሉ ፅንሰ ሀሳቡን ለማሳየት እንጂ ከአዛዥና ቅይጥ ኢኮኖሚ ጋር የተያያዙ ውስብስብ መስተውሑዳን (variables) እንዳሉ ማንም መዘንጋት የለበትም። ስለሆነም የሚከተለውን ስሌት በአጠቃላይ መልኩ ተረዳልኝ፤ የቀናሽነት–አቀንቃኝ (Reductionist) አይደለሁም። እናም፦

ሀ + ለ = ሐ

ሀ = ማለት አዛዥ ኢኮኖሚ ይሁን።

ለ = ማለት የግል (Private) ኢኮኖሚ ይሁን።

ሐ = ማለት ቅይጥ ኢኮኖሚ ይሁን

«ሀ» (አዛዥ ኢኮኖሚ) ወደ ዜሮ በተጠጋ ቁጥር

ለስሌቱ ትልቁን ሚና የሚጫወተው «ለ» ነው። በገቢራዊ የዓለም አቀፍ ሁኔታ እንደሚታየው በአሜሪካ ዶላር፣ በጀርመን ማርክ፣ በእንግሊዝ ፓውንድና በጃፓን ዬን የተነሳ ዓለም አቀፍ የንግድ ልውውጥ የግል ንብረትን በማሳደጉ የግል ኢኮኖሚ ኃይልነቱንና ስልጣኑን ተቀዳጅቷል። አዛዥ ኢኮኖሚ ድምጥማጡ ጠፍቷል። ከሶቪየት ኅብረት መንኮታኮት በኋላ በአዛዥ ኢኮኖሚ ሁኔታዎች ምቹ አይደሉም። ለዚህም ነው የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሦስተኛ ዓለም ምሁራንና የጥናት ማዕከሉች የሚያነበንቡት የቅይጥ መፈክር ባዶ የሚሆነው። በአሁኑ የዓለማችን ሁኔታ በመፈክር ካልሆነ በስተቀር ያለውን የግል ንብረት ሁኔታ በፖሊሲ ለመቀየር አንችልም። እዚህ ላይ መቀበል ያለብን አንድ ሀቅ አለ። ቅይጥ ኢኮኖሚ ለጥቂት ጊዜ ዚምቧቤ እንደታየው ተዓምር ሊሰራ ይችላል። ትልቁ ዓለም አቀፍ የግል ንግድ መልሶ ስለሚውጠው እንደገለባ እሳት ይሆንና ቶሎውኑ ይጠፋል። እንደነስዊድን ሰብዓዊ የግብረሠናይ መንግሥታት (Welfare States) ማቋቋም ያለ ነገር ነው። ነገር ግን በስም ብቻ ያጌጠ ቅይጥ ኢኮኖሚ እገነባለሁ ማለት ራስን ማታለል ነው።

ታዲያስ ያገር ልጅ ወርቃየሁ የቱ ይበጃል? ቅማል የሚያስበላ አዛዥ ኢኮኖሚ ወይስ በሕዝብ ላይ ደንገላሳ የሚጋልብ ያልተሸበበ የግል ንብረት ኢኮኖሚ? ወይስ በመፈክር ያጌጠና በግብር የማይተረጉም ነገር ግን በውስጡ የግል ገበያን ኃያልነት የሚያስመሰክር ጥምር ኢኮኖሚ? በመፈክርና በገቢራዊ ሁኔታ ሲታይ የሦስተኛ ዓለም ሀገሮች ችግር ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው። የግል ንብረትን ኃጢአተኛ መዋቅር መስበር ካልተቻለ እንደለማዳ እንስሳ ማለማመድና ቤተሰባዊ ማድረግ ይቻላልን? ("Friendly Capitalism") እንዴት?

የሦስተኛ ዓለም ሀገሮች ቁጥጥር ካልተደረገበት ወደ ንቅዘትና ዝቅጠት የሚያመራውን የግል ኢኮኖሚ ለህዝብ ጥቅም ሲሉ መሸበብ አለባቸው። የተሸበበ የግል ኢኮኖሚ ከግብረሠናይ መንግሥታት ጋር ፅኑ ጓደኝነት አለው። ኃብታሙንና ባለፀጋውን ለህዝብ ጥቅም እንደችሎታው በግብር ይቆነድደዋል። እንደለማዳ የዱር አራዊት አደብ ይገዛል። ሲናከስና ሲያቆስልም እግሩ በሰንሰለት ታስሮ አፉ ይሸበባል። ስካሩና ቁጡነቱ ይበርድለታል። ባህልን እንዳያጠፋ በህግ ይሰከላል። ስዊድን ያደረገችው ይህንኑ ነው። ኖሮዌይ ጊልደኗን አበርክታ ለራሷ ተርፋ ለዓለም አቀፍ ተራድዖ የበቃችው በዚሁ ነው። የውሸት የቅይጥ ኢኮኖሚንና የአውርጳን ሶሺያል ዴሞክራሲ አሁንም የሚያምታቱ ኢኮኖሚስቶች አሉ። ሁለቱ ግን ልዩ ናቸው። ቅይጥ ኢኮኖሚን በተግባር ለመተርጐም የመንግሥት የፖሊስ ባህርይ (Police State Character) ጉልህ (dominant) መሆን አለበት። በሶሺያል ዴሞክራሲ ግን ፓርላማዊ ኃይሉ ነው ጉልህ የሚሆነው። የኢኮኖሚ ትምህርት ራሱ መነሻው ከብርና ከንቅዘት ነው። ሦስተኛው ዓለም ራሱን የቻለ አማራጭ (Alternative) የኢኮኖሚ የጥናት ማዕከል መመስረት አለበት። ግን እኮ ኖሮዌይ ኢትዮጵያ አይደለችም ትለኝ ይሆናል። ትክክል። የኢትዮጵያ ህዝብ ባህሉን ሳይጥል፣ ሳይከፋፈልና በጎሳ የእርስ በርስ መርዝ ሳይበከል ከተባበረ የግል ንብረትን ሸብቦና ሰንኮፉን ከስክሶ እንደለማዳ አውሬ ከህጉና ከባህሉ ጋር አለማምዶ ህዝባችንን ከድኅነት ሊያላቅቅ ይችላል። ለዚህ መሳካት በህዝብ ፍላጐት ላይ የተመሰረተ አሰባሳቢና በጐሳ መርዝ ያልተበከለ አርቆ አሳቢ ፌዴራላዊ መንግሥት መቆም አለበት። ሌላው መነሳት ያለበት ጥያቄ የሚከተለው ነው። የካፒታሊዝምን በብሔራዊ ትግል መሸበብ የዓለም መከሊቶች ይደግፋሉን? አይደግፉም። ስለሆነም ብሔራዊ ፕሮግራሞች በረቀቀና በነጠረ' ታክቲክ ደረጃ በደረጃ መነደፍና በግብር መተርጐም አለባቸው። የ«ኮሚኒስት ባሪያ» ሆኖ አለም አቀፍ ህብረገነናዊነትን (Totalitarianism) ማታለል እንዳልተቻለ ሁሉ የ«ምዕራቡ ባሪያ» ሆኖ ነጮችን ማታለል አይቻልም። ሁለቱንም ግን በበሰለ ታክቲክና ስትራቴጂ መታገል ይቻል ነበር። ምናልባትም ከኮሚኒስት ባሪያ የካፒታሊስት ባሪያ ፈንጋይና አቀባባይ መሆን ይሻላል የሚል ሳይጠፋ ይችላል። ይህ አባባል በገቢራዊ ሁኔታ የሚማርከው «የካፒታሊስት ባሪያ ቢያንስ በልቶ ያድራል፣ ደምወዙ አዲስ ልብስ ባያስገዛ ማለፊያ ውራጅ ልብስና ግሳንግስ ያመጣል» ወደሚለው በማጋደል ነው። በአመለካከት ደረጃ እስካልተለያየን ድረስ የዝንጀሮ ቆንጆ እንደሌለ ሁሉ የባርነት መልካምነት ለሦስተኛ ዓለም የለም። ጥንት አባቶቻችን የፓርቹጋልንና የጣልያን ጣልቃ ገብነት የታገሉት ሳይመርጡ ነው። የአደዋውና የማይጨው የአልገዛም መንፈስ ከዚህ ስሜት የመነጨ ነው። ስለሆነም አንድ ሕዝብ ብሔራዊነቱን እስካገነና ግብ አድራሽ አረማመዱን ለከቶ እስከተራመደ ድረስ ከባለ ጉልበቱ ጋር በአላስፈላጊ ሁኔታ ሳይጋጭ በጥበብ ጥቅሙን ሊያስጠብቅ ይችላል። ይህ በረቀቀ ዲፕሎማሲያዊ ቀመር፣ በጋራ ጥቅም መርሆ፣ በምርት ማሳደግ፣ የግል ንብረትን ከባህልና ከወግ ጋር ለማዳ በማድረግ፣ ብድርን በጊዜው በመክፈልና ለሕዝብና ለሀገር ጥቅም ነፃነትን ሳይሸጡ ድርድር በማድረግ ሊመጣ የሚችል ነው። የእምዬ ምንሊክ የዲፕሎማሲ ችሎታ ለዚህ ቁምነገር ምሳሌ የሚሆን ነው። እንደካስትሮም ሳይገተሩ እንደቴርሀንም አያቶላ ሳይቆጡ ሁሉንም የኃይል አሰላለፍ በመረዳት በጥበብ የሚካሄድ ግኑኝነት ነው። ከላይ እንደጠቀስኩት አንዳንድ ኢኮኖሚስቶች ሰይጣንን ማታለል እንደማይቻል ሁሉ ካፒታሊዝምን በኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ ለማዳ ማድረግ ይከብዳል ይሉ ይሆናል። አመጣጣቸውና አባባላቸው ትክክል ነው። ጥናቱ በጥልቀት ከተደረገ የማይቻል ነገር የለም። እንኳን ለበጐ ነገር መደራደር ቀርቶ ሞቡቱ ሴሴኮ እንኳ በአንድ ታሪካዊ ወቅት በእኩይ ምሁራኑ ድርድር አይኤምኤፍን ተጋፍቶ ነበር። አይኤምኤፍን በእርሱ የድርድር አጀንዳ ውስጥ አስገብቶት ነበር። ጋፍኛ አይኤምኤፍ ግፉዕ ሆኖ በመበደሉ የሞቡቱን መንግሥት መማጠን ጀምሮ ነበር።

ዛሬ ጥምር ወይም ቅይጥ ኢኮኖሚ በአንዳንድ ሀርቫርድና ኦክስፎርድ ታዋቂ የምዕራቡ ምሑራን በሥርዓተ–ትምህርት ውስጥ ይስተናገዳል። እንደነ ኬኔት ጋልብሬይዝ ያሉት ዕውቅና የኖቤል ሽልማት ያገኙት ምሑራን በ«ተራማጅ» ኢኮኖሚ ስንክሳር ስም የጥምር ኢኮኖሚን ጠቃሚነት በጽሁፎቻቸው ማቀንቀናቸው አልቀረም። አውቀውም ሆነ ሳያውቁት ለዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት አቸናፊነት ምሑራዊ ሽፋን ይሰጣሉ። የኢኮኖሚ መፈክር ሕዝባዊ ድምፁን ሳይለቅ በነርሱ ጥገናዊ ለውጥ ውስጥ ይገባል። በብድርና በዕርዳታ ስም የሚጉለብቱት የዓለም መከሊተኞች ቀስቃሽ ቡድንም (Lobby Group) መስርተዋል። አንዳንዶቹ ዓለማዊ ተራድዖን፣ የሦስተኛ ዓለም መበልፀግንና ለአሜሪካ ሠራተኞች የጠበቃ ቋሚነትን ስለሚያቀነቅኑ በሰብዓዊነት ስም ዓላማቸውን ያስጠብቃሉ። ከእነዚህ ውስጥ እንደምሳሌ መጠቀስ የሚገባው «የአሜሪካን ዓለምአቀፋዊ መሪነት ለማረጋገጥ የተዋቀረ ዘመቻ» በሚል የተደራጀው ስብስብ ነው። [CAMPAIGN TO PRESERVE US GLOBAL LEAD-

ERSHIP ይባላል]። ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው።

ሀ) በአሜሪካ የስራ መስክ ለመክፈት (ለማስፋፋት)

ለ) በዓለም የድኅረ-ቀዝቃዛ ጦርነት (Post Cold War) ሊያስፈልግ የሚችለውን ደኅንነት (Security) ማረጋገጥ

ሐ) ሰብዓዊ ዕርዳታዎችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስተባበርና የዓለም ሕዝብን በሰብዓዊ መንገድ ለመርዳት፣

መ) ቤተሰብን ለማጠናከርና ሕፃናትን ለማዳን

ሠ) የዓለም አቀፍ የምግብ ዕርዳታንና ችሮታን ለማዳበር

ረ) በጋራና የእርስ በእርስ ተራድዖ አለም አቀፍ ኢኮኖሚን መገንባት፣

ሰ) ወዳጆቻችንን በኢኮኖሚና በወታደራዊ ቋልኪዳን መሠረት መርዳት፣

ሸ) የንጥረ ኃይል ግዝፈ-መሳሪያዎች (Nuclear Weap ons) እንዳይሳፋፉ ማገድ

ቀ) የአሜሪካንን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መደገፍ፣

ረ) የዓለምን የተፈጥሮ ክልልን ሀብት መንከባከብ (Protecting the Global Environment)

ወንድሜ ወርቃየሁ! በርግጥም እነዚህ በደፈናው ላይ ላዩን ሲታዩ ጠቃሚ ቢሆኑም ሐሳቦቹን ያቀነቀነው ስብስብ (Coalition) ቀዳማይ መርኁ የአሜሪካንን የበላይነት ማረጋገጥ ነው። የአንዱ ኃይል በጉለበተ ቁጥር ደካማው ይረገጣል። እርሱ ሲገዝፍ ንዑሱ የበለጠ ይማማል። ይደፈጠጣልም። ለዓለም ድኃ ሕዝብ ከኃያላን መንግሥታት እርግጫ ለመከላከል ሕጋዊ መፍትሔ አልተወጠነም። ለዓለም የድኃ ሕዝቦች ፍትሐዊ ሥርዓትና ዴሞክራሲ የሚታገል አመዛዛኝ ድርጅት በአሁኑ ጊዜ የለም። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም ቢሆን መተዳደሪያ በጀቱን በይበልጥ የሚያገኘው ከአሜሪካና ከሌሎች የአውሮጳ ሀገሮች ስለሆነ የእነርሱን ዓላማ ከማስጠበቅ አይቆጠብም። ትልቁ ምሳሌ ቡጥሮስ ጋሊ ለመለስ ዜናዊና ለኢሳያስ አፈወርቂ የሰጡት ድጋፍ ነው። ሰብዓዊ የዓለም ድርጅት አለ ከተባለ ይኸ ተቋም በአመለካከቱ ሚዛናዊ ነው። በመሳሪያ እሽቅድምድም ንግድ ሊኖረው የሚገባ አመለካከት ፍትሐዊ መሆን አለበት። እግዚአብሔር ኃያላን መንግሥታት ብቻ የንጥረ ግዝፈ ኃይላት መሣሪያዎች እንዲሰሩ ከሰው ልጆች በላይ የሞራል የበላይነቱን አልሰጣቸውም። እነርሱም በኃይላቸው ዛሬ ከሚለፍፉት የሁቱና የቱትሲ መጫረስ በበለጠ በነጩ ወገናቸው ላይ እንኳ ከአፍሪቃ የ500 ዓመት መተላለቅ በሚያስከነዳ መንገድ ሕዝባቸውን አውድመዋል። በአሽዊትዝ፣ በቢርከናው፣ በባይለሩስ፣ በሒሮሽማ፣ በናጋሳኪ፣ በቬዬትናምና በሌሎችም ስፍራዎች የሰው ስጋን ጠብሰዋል። የተባበሩት መንግሥታት ጥረት የረቂቅ-ግዝፈ ኃይላትን መሣሪያዎች ከዓለም ለማጥፋት ከሆነ ትክክል ነው። እኛ ብቻ ኃይል ይኑረን ለሚሉን ግን ለእናንተስ ከምናያችሁና ከምንታዘባችሁ ሁኔታ አንፃር የቱ ጌታ ነው የሞራል የበላይነትን የሰጣችሁ እንላቸዋለን። በባሪያ ንግድ፣ በቀጥተኛ ቅኝ አገዛዝና በእጅ አዙር አስተዳደር ዓለምን በማራኮት ብዙ ግፍና ስቃይ ስላደረሳችሁ የእናንተ የበላይነት በጉልበታችሁ ካልሆነ በሞራላችሁ አይደለም እንላቸዋለን። የኢትዮጵያ፣ የዛየር፣ የብሩንዲ፣ የላይቤሪያ፣ የደቡብ አፍሪቃ፣ የሩዋንዳና የሌሎችም ሀገሮች ፍጅት ውስጥ የእናንተም የአውርጳውያን እጅና ተንኮል አለበት እንላቸዋለን።

ወዳጄ ወርቃየሁ! ወደነሞቡቱና መለስ ዜናዊ ታሪካዊ ማመሳከር ልመለስ። በአደዋው የአልገዛም መንፈስ (Spirit of Adwa) ላይ የተዋቀረው ትግላችን የቀጥተኛና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ላይ የተመሰረተ ነው። ትግላችንና ፍልሚያችን ለአርነት ከሚፍጨረጨሩት የአፍሪቃ ጥቁር ሕዝቦች ተለይቶ የሚታይ አይደለም። ሞቡቱ ሞቡቱ ስለሆኑ ብቻ ከአፍሪቃ መሪዎች ልዩ አይደሉም። እርሳቸውም ስልጣን ይጥማቸው ነበር። ዛሬ ወንበራቸው እንኳ በሕዝብ ከመመዝበሩ በፊት የተሰራው ፈረንሳይ ሀገር ነበር። ባህላቸውና የቦጠሊቅ አገባባቸው የባሕር ማዶ ዘዴ ነበረው። የሀገራቸውን ህዝብ ንቀው ቋንቋቸውን በመርሳት በነቻርላማይን ቋንቋ ነበር ሆሄ እየዋጡ በላንቃቸው የሚነጋገሩት። ሱፋቸው፣ ካፖርታቸውና ምንጣፋቸው ከውጭ ነበር በዕውቅ ሠራተኞች ተሰርቶ የተላከላቸው። የእኩይ መደባቸው የቀለም ሰዎች የተካኑት በውጪ ዩኒቨርስቲዎች ነበር። «እውነት አላቸው» ለምን አፍሪቃን ይውደዱ። የዛሬዎቹም መለስና ካቢላ፣ የነገዎቹ ሞቡቱዎች ከአድማስ ባሻገር እንደመንግሥቱና ዚያድባሬ መጭውን ቀን እየተጠየፉ ለዛሬ ብቻ እየኖሩ ነው። የሌዮፓልድ፣ የዚያድባሬና የመንግሥቱ ጣረሞቶች ለነመለስና ካቢላ ከእኛ ተማሩ እያሉ እረፍት ነሽ ጩኸት እንደሚያሰሙ አልጠራጠርም።

ወዳጄ ወርቃየሁ! አንድ ኢ.ኤፍ.ፖርተር (E.F Porter) የሚባሉ ጋዜጠኛ የአሁኗን ዛየር የጥንቷን ኮንጉ ቅኝ ግዛት ከለገሳቸው ጠባያት አኳያ በመመርመር በቅርቡ በኒውዮርክ ታይምስና በሴንትሉዊስ ፖስት ዲስፖች ላይ ዘግበው ነበር። ጽሑፋቸው ከአውሮጳዊ አስተሳሰብ ውጪ እምብዛም ታሪካዊ ፍርድን ለመስጠት ባይችልም ደረቅ ታሪኩ ከሞላ ጉደል ተገቢ ስለሆነ አስተያየታቸውን አደብዝዤ የታሪክ ገጠምተኝነትን በቅደም ተከተል ከእርሳቸው በመጥቀስ ለማብራራት እሞክራለሁ።

አፍሪቃ በርግጥም ከአረቦችና ከአውሮጳውያን ዘመቻ በኋላ የምድር ሲኦል መሆኗ የሚያከራክር አይደለም። ምንም እንኳ ኢትዮጵያችን በየጊዜው የተነሳባትን የውጪ ወራሪ ኃይል በታሪኳ ድባቅ ብትመታም በዘመናችን የውጭ ኃያላን መንግሥታት የእጅ አዙር ጣልቃ ገብነት በሕዝቦቿ ኑሮ ላይ ተፅዕኖ አድርጓል። የመለስ ዜናዊንና የመንግሥቱን ሁኔታ ስንመረምር የዛየሩ የሞቡቱ ታሪክ በምሳሌያዊነቱና በተመክሮአዊ ስልቱ ከእነዚህ ድውይ መሪዎች ጋር በማመሳከር በርካታ ቁምነገሮችን ሊያስተምረን ይችላል። እነሆ የቀድሞዋን ኮንጉ የዛሬዪቱን ዛየር ከጋዜጠኛው ኢ.ኤፍ.ፓርተር (E.F Porter) በመጠቃቀስ እናውጋ። ምስጋናውንም እንለግሳቸው። ስለዛየር የዘገቡትን በውርስነት (ከሴንትሉዊስ ፖስት ዲስፖት ሜይ 25, 1997) በመተርጉም ለአንባቢ አቀርባለሁ።

ወንድም ወርቃየሁ! «ከአንድ መቶ ዓመታት በፊት የኮንጉ ነዋሪዎች እርስ በርሳቸው ይተላለቁና ይዘራረፉ ነበር። እስከዛሬም ድረስ ቢሆን መተራረዱና መጫረሱ ካቢላ ስልጣን እስከያዙበት ጊዜ ቀጥሏል። የኮንጉ ቀዳማይ ቅኝ ግዛት ታሪክ የተጀመረው ከ3000 ዓመት በፊት ነበር። በዚህም የታሪክ ዘመን ባንቱ የሚባል የአፍሪቃ ነገድ ከደቡብ ሰሐራ በረሐ አካባቢ በመፍለስ የአሁኗን ዛየር አካባቢ ሰፈረበት። አንዳንድ ታሪክ ተመራማሪዎች ከባንቱ ነገድ በፊት በዱር የሚኖሩ አጫጭር ሕዝቦች (ፒጊሚስ-Pygimies) በአካባቢው እንደኖሩ ይናገራሉ። ሌሎችም ፀሐፊዎች ቀዳማይ ሰፋሪዎች የትኞቹ እንደሆኑ እንደሚያስቸግራቸው ዘግበዋል። እነዚህ ሁለት የህዝብ ክፍሎች ጉሳዊ ዝምድና ወይም ሐረጋዊ የደም ትስስር አልነበራቸውም። ምንም

እንኳ ታሪክ ተመራማሪዎች የባንቱ ነገድ ከደቡብ ሰሀራ አካባቢ መጣ ቢሉም ለዚህ በቂ ማረጋገጫ የለም። ከአፍሪቃ ቀንድና ከሰሜን አፍሪቃ ሕዝቦች በመልክና በአካላዊ ቁመና ይለያያሉ። የኖርዌይ ነሞች ከግሪክ ህዝቦች እንደሚለዩ ከሰሜን የዋትቱሲ ሕዝቦች (Watusi People) ከቁጥቋጦ ጫካ ሕዝቦች (Bush men) የባንቱ ሕዝቦች ይለያሉ።

የኮንጐ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ በሚባለው አካባቢ የባንቱ ፍልሰ–ስደት ራሱን እየከፋፈለ በቤተሰብና በቀላዳዊ ስፍር የቄቃና የሳር ቤት በመስራት ሰፈረ። በአንዳንድ የዘር ታሪክ አጥኚዎች አባባል በኮንጐ አካባቢ የታየው ታሪካዊው የባንቱ ፍልሰ–ስደት እስያውያን ወደ አሜሪካ እንደጐረፉት ዓይነት ሥነ–ሥርዌት (Wave) አድርገው ያቀርባሉ። አውሮጳውያን ገና ደቡብ አፍሪቃ ሳይገቡ ነበር ባንቱዎች ሌላ አካባቢ ይኖሩ የነበሩት። ይህም ለአፓርታይድ (ለዘር መድሏዊ ገደብ) የነጩን መጀመሪያነት (አብሪነት) በማሳየት ደቡብ አፍሪቃን ለመቆጣጠር በቂ መነሻዊ ምክንያት (pretext) ሆነ።

በኮንጐ የሚኖሩ ባንቱዎች ብዙ የሚነገርለት የአውሮጳውያን ስልጣኔ አላጥለቀለቃቸውም። በአፍሪቃ ሞቃታማና ቆላማ የመሬት መቀነት አካባቢ ስለሚኖሩ እንደአውሮጳውያን ከከባድ አየር ጋር በመፋለም በስልጣኔ አልገፉም።»

እየሀ ወርቃየሁ! እንደፀሐፊው አባባል እነዚህ ባንቱዎች ለም ሀገር በመኖራቸው በአደንና የዱር ፍራፍሬ በመልቀም ይኖሩ ነበር። ሙዝና የስኳር ድንች የመሳሰሉትን የምግብ ዓይነቶች ከድንግል የአፍሪቃ መሬታቸው ይሰበስባሉ። የጽሑፍ ቋንቋ ወይም ፊደል ስለሌላቸው የአቆጣጠር ስልት፣ በዕቅድ የተለካና የተዋቀረ መንገድ፣ የሒርቃ ጨርቅ ዕውቀት፣ የተሽከርካሪ ዕደ ጥበብና የበለፀጉ ከተማዎች አልነበራቸውም፤ የጊዜን ማለፊያ የሚለኩበት የጊዜ መቁጠሪያ አልሰሩም። ከውሻና ከአሳማ በስተቀር ሌሎች ለማዳ እንስሳትን አያውቁም ነበር። ለእርሻና ለመጓጓዣ የቤት እንስሳትን የመጠቀም ልምድ አልነበራቸውም። ሆኖም አንዳንድ የባንቱ ወገኖች ብረትን፣ ነሐስንና ወርቅን በማቅለጥ ጦር መሣሪያንና ጌጣ ጌጥን መስራት ለምደው ነበር። እነዚህ መሣሪያዎችና ጌጣጌጦች ያተኮሩት በአምልኮትና በበዓሎቻቸው ላይ ነበር። እምነታቸው በጣዖት፣ በአስማት፣ በአባቶቻቸውና እናቶቻቸው ውቃቢ ላይ የተመሰረተ ነው። በቃል ደረጃም የግጥሞችንና የዘፈኖችን ቃናም አሻሽለው ነበር። ይህም የጽሁፍ ሳይሆን የቃል ስንኝ ከልጅ ልጅ ሲወራረድ የመጣ የኪነት ባህል መሆኑን ኢ.ኤፍ. ፖርተር (E.F Porter) ያትታሉ። ምንም እንኳ የበርካታ መቶ ዓመታት የክርስቲያን ኃይማኖት ተፅዕኖ በኮንጐ ቢኖርም አምልኮተ ጣኦትና የሀገሩ እምነቶች ከዛር፣ ከቆሌና ልማዳዊ እምነቶች ህዝቡን አልነጠሉትም።

ዘመንም በገፋ ቁጥር ባህል እያደገና እየተለወጠ በመምጣቱ የጥንት ባንቱዎች ከእንጨትና ከዝሆን ጥርስ የመድብለ–ድምፅ (Polyphonic) መሣሪያዎችን ሠርተዋል። የከበሮና የታምቡር አመታታቸው ራሱ በላንቃ የሚናገር ይመስል ነበር።

ወንድሜ ወርቃየሁ!

ስለ አፍሪቃ ህዝቦች ታሪክና ባህል እንደዚሁም በየታሪካቸው ስላጋጠማቸው የአውሮጳውያን እንቅፋት ኢትዮጵያውያን በውል መረዳት ይኖርብናል። እኛም አፍሪቃውያን ነንና የእነርሱ በሽታና ሕመም ከእኛ የተለየ አይደለም። ከባዕዳንና ከዲክቴተሮች ደባ እኛም እንደነርሱ አልተላቀቅንም። ምናልባትም እያንዳንዱ የአፍሪቃ አህጉር ህዝብ የተጓዘበት ታሪካዊ መንገድ ከእኛ ተመክሮ ለየት ያለ ቢመስልም ከአፍሪቃ ቅርምት (Scramble for Africa, 1850's) በኋላ ታሪካችንን የጋራ የሚያደርጉ ክስተቶች ተከስተዋል። የአደዋና የማይጨው ጦርነቶች፣ እንደዚሁም የቀዝቃዛው ጦርነትና አዲሱ የዓለም አገዛዝ ስልት (The New World Order) ወደድንም ጠላንም ትግላችንን የጋራ ያደርጉታል። ከዚህ በፊት እነክዋሜ ንክሩማኅ፣ እነ አፄ ኃይለስላሴ፣ እነ ጆሞ ኬኒያታና አሁንም እነማንዴላ የሚያስተምሩን ይህን ሐቅ ነው። የዛሬውን አያድርገውና የአፍሪቃ አንድነት ጉባዔ (OAU) ሲመሰረት እነዚህን መርሆዎች በማካተት ነበር። ለዚህም ነው የባዕዳንን ጣልቃ ገብነት ለመምታት ኢትዮጵያ አገር ወዳድነትንና አፍሪቃዊ አህጉራዊነትን ይዞ የሚነሳ ሐገራዊ መሪና ድርጅት አስፈላጊ ነው የሚባለው። እንደልማዳቸው ኢትዮጵያውያን አርበኞችና ሀገር ወዳድ ምሁራን ይህንን ለዓለም ህዝብ ማሳወቅ አለባቸው። ከሌሎች ግፉዓን ሕዝቦች ጋር ትግሉን ካቀናጀን እንደዚሁም ጐሰኝነትንና ዘረኝነትን ሳናሰልስ ከተዋጋን ድጋፍ እናገኛለን። ስለሆነም የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል ብሔራዊና አፍሪቃዊ መሆን አለበት። (Pan Ethiopianist & Africanist)

ውድ ወርቃየሁ፣ ወደ ኮንጐ ታሪክ እንግባ። የባንቱ ህብረተሰብ በመንደሮችና በቤተሰብ ስፍሮች ላይ ጥንት የተመሰረተ ቢሆንም የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ በሄደበት ወቅት ጉልበተኛው ሌላውን እያስገበረ፣ ራቅ ያሉትም ከቅርቡ በመደባለቅ ነገዳቸውን አስፍተዋል። በሌላም በኩል ባንቱዎች ባህላቸውን የሚያከብሩና የአለቃና ምንዝርን ትስስር የሚቀበሉ በተለምዶ በተረጋጋ መንገድ የሚተዳደሩ ህዝቦች ነበሩ።

አንጀቴ ወርቃየሁ፣ ከአውሮጳውያን ጋር የነበራቸው የታሪክ ገጠመኝ እንደዚህ ነበር። «በ1483 የመጀመሪያዎቹ የፖርቱጋል ዱከኞችና መርማሪዎች ወደ ኮንጐ ወንዝ አካባቢ ደረሱ። እዚያም እንዳሉ የመጀመሪያ ፍላጐታቸው ውሱን ነበርና የንግድ ማዕከሎችን አቋቋሙ። በዚያን ጊዜም ፍላጐታቸው የዝሆን ጥርስ፣ መዳብንና ጥቂት ባሪያዎችን ማግኘት ነበር። የኮንጐም ንጉሥ በጣም በመደሰቱ ከአውሮጳውያን ጋር የተሳካ ግንኙነት መሰረተ። ደካማዎችን በጦርነት በማጥቃትና በማስገበር የተረፉትን የጐረቤት ህዝቦች ለፖርቱጋሎች በባርነት መልከ ሸጠ።» (* እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብህ ከዚህ በፊትም እንደገለፅኩት የወያኔና የሻቢያ አባላት ግምባር በመፍጠር በአሜሪካ የአንድነት ወገኖችን ለማስጠላት በተለይም የኤርትራ ሬፈሬንደም ሊቃረብ ሲል የእኛ ትግል ከባርነት ለመላቀቅ ነው፤ ኢትዮጵያውያን ባርያ ይሸጡ ነበር እያሉ፣ በጥቁር አሜሪካውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ለማስጠላት የተጠቀሙበትን የፕሮፓጋንዳ ስልት ነው። በታሪክ ውስጥ ደካማውን ያላስገበረ፣ ወሰንና ድንበር ያልጣሰ ህዝብ ይገኛልን? ዴሞክራሲያዊ አሜሪካና ካናዳስ በማን ሀገር ነው የሚኖሩት? የጥንት የኤርትራ መሪዎችስ የብሌንና የኩናማን ሕዝብ አላሰቃዩምን? የኦሮሞውስ ህዝብ ከዚህ ነፃ ነውን? በኩሉኮንታ፣ በጊሚራ፣ በወረሒመኒ በ16ኛውና–18ኛው መቶ አመት ድረስ ቋንዣ እየሰበረ ባሪያ ሲሸጥ አልነበረምን?)

የሆኖ ሆኖ ወደ ዋናው ቁምነገር እንመለስ። ፓርቱጋሎች የኮንጐን ወንዝ በመከተል እንዳበደ ውሻ ሲክለፈለፉ በሌላ ወገን ደግሞ ማዕከላቸውን ዛንዚባር (ምስራቅ የአፍሪቃ ጠረፍ) ያደረጉት አረቦች ወደ ውስጥ

በመስረግ የባሪያን ንግድ አጧጧፉት። አንዱን ነገድ በመደገፍና በመግዛት እንደዚሁም በማጣላት ግባቸውን በመወጣታቸው አረቦችና አውሮጳውያን ያመጡት የከፋፍለህ ግዛው ዘይቤ ከትውልድ ትውልድ በመተላለፉ ህዝቦች የጐሪጥ እንዲተያዩና ይህም ቁስል ለዘመናት እንዲቆይ ሆኗል። የሁቱና የቱትሲ ጠብ፣ የባንቱ ዜጐች መለያየት የኢንካታና ኤኤንሲ መከፋፈል፣ የኤርትራውያንና የኢትዮጵያውያን የጐሪጥ መተያየት፣ የኦሮሞ፣ የትግሬና የአማራ ህዝብ መጠራጠር ለዚህ ዓይነተኛ ማስረጃ ነው።

«በ1887 ሄነሪ ሞርቶን ስታንሊ የኒውዮርክ ሄራልድ ጋዜጠኛ ከጭፍሮቹ ጋር በማበር የኮንጐን ህዝቦች እየገደለ ልክ አሜሪካ እንደተፈጸመው የስፓኒሽ ዘመቻ ወደ ባንቱ ህዝቦች ዘልቆ ገባ። በእንግሊዝ (ዌልስ) የተወለደው ሞርቶንስታንሊ በኒው ኦርሊንስ ይኖር ነበር። በአሜሪካ የእርስ በእርስ ጦርነት (Civil war) ጊዜ በኮንፌደሬት ሠራዊት ያገለገለ በመጨረሻም ተማርኮ ከዩኒየን ሠራዊት ጐን የተዋጋ ጋዜጠኛ ነበር። ከጦርነቱ በኋላ የኒውዮርክ ሔራልድ የውጭ ጉዳይ ዘጋቢ ሆኖ በኢትዮጵያ፣ በትቤትና በሩሲያ ሠርቷል። አለቃው ዶክተር ዴቪድ ሊቪንግስተንን (የስኮትላንድ ዶክተርና ሰባኪ) እንዲገናኝ ወደ አፍሪቃ ላከው። ስታንሊና ዶክተር ዴቪድ ሊቪንግስተን በታንጋኒካ ሐይቅ አካባቢ ተገናኙ። የቤልጂየሙ ንጉሥ ሊዮፓልድ ከስታንሊ፣ ከዶክተር ሊቪንግስተንና ከአሜሪካ ጋር ውስጥ ውስጡን በመመሳጠር ኮንጐን ነፃ ሐገር አስብሎ በቁጥጥር ስር አስገባ። ንጉስ ሊዮፓልድም ኮንጐን ልክ እንደራሱ ቀላድ በመቁጠር የዝሆን ጥርስና የጐማ ምርት ለሌሎች ባዕዳን ሀገሮች ለመሸጥ ተዋዋለ። ሊዮፖልድም «ስራዬ እነዚህን የአፍሪቃ የጫካ ህዝቦች ማሰልጠን» ነው በማለት የኮንጐን ህዝብ ጉልበትና ማዕድን በዘበዘ። በዝሆን ጥርስና በጐማ የቀረጥ ተመን ለሊዮፖልድ እንዲከፍል የኮንጐ ህዝብ ተገደደ። ግብሩን ያልከፈሉ ይረሸኑ ነበር። በዚህ ምክንያት በርካታ ባንቱዎች ወደ ጫካና ደኖች ሸሹ። የባንቱን ሰላዮችና አስካሪዎች በመቅጠር በአሜሪካኖችና በቤልጂያኖች መሪነት ህዝቡ ተሰደደ ተጨፈጨፈ። እንደአረቦች ዘዴ አውሮጳውያኑም የከፋፍለህ ግዛን ዘይቤ አስፋፉት። ሕፃናት፣ ሽማግሌዎች፣ ወጣቶችና አመፀኞች ተጨፈጨፉ። ለማረጋገጥም አስካሪ ሰላዮች የአመፀኞችን ሬሳ አቃጥለውና ጠብሰው ለአለቆቻቸው በማቅረብ ተሾሙ። ሬሳም የሚጠበስበት ትልቁ ምክንያት እንዳይሸትና እንዳይከብድ ነበር። አንዳንድ የህዝብ ወገኖችም ከዚህ መዓት ለመዳን እጃቸውን ቆርጠው አቃጥለውና አቀርንተው ከግብር ጋር ወደ አለቆቻቸው መጡ። ይህ ነበር እንግዲህ የአውሮጳውያን ስልጣኔ። ይህንን በመቃወም ለመመርመር የእንግሊዝ የቆንስል ተወካይ በ1903 ወደ ኮንጐ ተላከ። ስሙም ሮጀርስ ኬስሜንት ይባል ነበር። በርካታ ዘግናኝና እንደዚሁም አሳዛኝ የኮንጐ ትዕይንትን ይህ ወኪል ስለመዘገበ ይህንን በማንበብ በርካታ የእንግሊዝ ዜጐች ታመሙ። ሚስተር ሮጀርስ ኬስሜንትም ትልቅ ዝናንና ታዋቂነትን አገኘ። በዚህም ምክንያት የቤልጂየም ፓሪሊያመንት የኬስሜንትን ሪፖርት ካዳመጠ በኋላ ንጉሥ ሊዮፖልድ ኮንጐን በግሉ እንዳይቆጣጠር አገደው። ስለሆነም የቤልጂየም መንግሥት በመጠኑም ቢሆን ሰብዓዊነት ተሰማው።

አንደኛው የዓለም ጦርነት ሊገባ ሲል ጀርመንም ምሥራቅና ምዕራብ አፍሪቃን ተቆጣጠረች። ይህ በዚህ እንዳለ ኔቪል ቻምበርሊን በ1930 ለጀርመን ቺኮዝላቫኪያ ለመስጠት ተመሳጠረ። የራሱ ያልሆነውን ሀገር ቺኮዝላቫኪያን ለጀርመኖች በዲፕሎማሲያዊ አሻጥር ሸጠ። ኮንጐ ግን በዚያ ውጣ ውረድ አሁንም በቤልጅጐች እጅ ነበረች።»

ወንድሜ ወርቃየሁ፣ በ1960 ቤልጅየም ለኮንጐ በነበረው የፀረ ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ የተነሳ ነፃነቷን ሰጠች። ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ህዝባዊ ኃይል (Force Publique) በሚባለው የሐገሬው ድርጅት አመፅ በማስነሳት በማዕድን የበለፀገችውን ካንታንጋን ለመገንጠል መፈክር አሰማ። የእርስ በእርስ ጦርነት ተነስቶ ብዙ ደም መፋሰስ ሆነ። በፓትሪስ ሉቡምባ (ኮሚኒስትና ብሔራዊ) በጆሴፍ ካሳቩቡ መካከል ጦርነት ተቀሰቀሰ። ፓትሪስ ሉቡምባ የሲቪዬትን ድጋፍ አገኘ። ከዚህም በተባበሩት መንግሥታት ጣልቃ ገብነትና በአሜሪካ የሲአይኤ አሻጥር ፓትሪስ ሉቡምባ ተገደሉ። እኛም እንደአቅማችን ከምዕራቡ መንግሥታት በተለይም ከአሜሪካ ጋር በመሆን በኰንጐ ዘመቻ ተሳትፈናል። ኮሪያም እንደዚሁ የምዕራቡን ዓለም ጥቅም ለማስጠበቅ ዘምተናል። ለታሪኩና ለትዝብቱ ኮሪያና ኮንጐ የሰጠን ጥቅም ቢኖር የጥላሁን ገሠሠን ሙዚቃ ነው። ሁለቱም ሀገሮች በመዝመታችን ያገኘነው የኢኮኖሚ ብልፅግና ወይም ቋሚ የምዕራቡ ዓለም ወዳጅነት የለም። ኑሮ ኑሮ አሜሪካም የኤርትራን መገንጠልና የጐሰኛ መንግሥትን ከመደገፍ አላለፈም። የጥንት ወዳጅነትን ጠቅሶ ከባህላችንና ከሀገራዊ ልዑላዊነታችን ጋር አልተሰለፈም። ለደጋፊው ለኃይለሥላሴ ብሎ እንኳ ከአንድነት ኃይሉች ጋር አላበረም።

ወዳጄ ወርቃየሁ!

የሞቡቱስ ስርወ መንግስት እንዴት ነበር? «ፓትሪስ ሉቡምባና ጆሴፍ ካሳቩቡ የተዋጉት በጁላይ 1960 በኪንሻሳ ድሮ ሊዮፓልድቪል በምትባል ከተማ ነበር። የካታንጋ አመፅ በ1963 በተባበሩት መንግስታት ጣልቃ ገብነት ተፈፀመ። ከዚያ በኋላ ከአንድ ዓመት በኋላ ጄኔራል ዲዜሪ ጆሴፍ ሞቡቱ በወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ካሳቩቡን ገልብጠው ስልጣን ያዙ። ስማቸውንም የአውሮጳውያንን መጠሪያ አልፈልግም በማለት ሞቡቱ ሴ.ሴ.ሴኮ ብለው ሰየሙት። ሴሴሴኮ «ከድል ወደ ድል» ማለት ነው። ሀገሪቷንም ዛየር ብለው ሰየሟት። ዛየርም ወንዝ ማለት ነው።

ሞቡቱም እንደ አስራ ሁለተኛው ክፍለ ዘመን ታሪክ በአሰቃቂነትና በፈላጭ ቆራጭነት እስካሁን ገዙ። ከአይኤምኤፍ የሚያገኙትን ብድርና የሀገሪቷን ንብረት ለራሳቸው በመጠቀም እንደዚሁም የሀገሪቷን ሠራዊት እንደራሳቸው ጋሻ ጃግሬ በማድረግ በስልጣን ባለጉ። በባህላቸው መሰረት ከአነር ቆዳ የተሰራ የማዕረግ ልብስ በመልበስ ለባዕዳን መንግሥታትና ለራሳቸው ጥቅም በቀጥታ ሀገራቸውን ቸበቸቡ። በገንዘብ ኃይልና በማስፈራራት ተቀናቃኝ ፓርቲዎችን አጠፉ። እንደማንኛውም የሶስተኛ ዓለም አምባገነኖች በቀዝቃዛው ጦርነት አማካኝነት የዋሽንግተንን ዓለም አቀፍ ደፍጣጭ የፖሊስ ልብ ማረኩ። ለዚህም ነው ርዕሰ ብሔር ጆርጅ ቡሽ «ሞቡቱ የአሜሪካ አንጋፋና ከቡር ጓደኛ ናቸው» ያሉት። ሌላው ለሞቡቱ ድጋፍን ያስገኘላቸው ነገር አሜሪካ ለግዝፈ ኃያላት መሣሪያ (Nuclear Weapons) የምትጠቀምበት ማዕድን በብዛት የሚገኘው ዛየር ስለሆነ ነው።»

ውድ ወርቃየሁ! እስቲ አንዳንድ የሂሳብ ገዖችን እንመልከት። የዛየር ህዝብ 44 ሚሊዮን ይጠጋል። ከ250

በላይ ጐሳዎች ወይም ብሔረሰቦች በዛየር አሉ። 50% የሕዝቡ እምነት ክርስቲያን ሲሆን 50% በጣኦትና በተለምዶ እምነት ያመልካል። ዛየር ከአፍሪቃ ትልቋ ሀገር ናት (900,000 ስኩዌር ማይልስ)። የአንድ ሰው የዓመት ገቢ $200 ነው። ዲያመንድ፣ መዳብና ኮባልት በገፍ ከሚያመርቱ ሀገሮች ጋር የምትታይ ናት። ሀገሪቷ 8,700 ማይሎች አቃዛፊ ጅረቶች አሏት። የዛየር የብድር ዕዳ በ1992 $10 ቢሊዮን ይደርስ ነበር። በ1980 250 የዛየር ብር አንድ የአሜሪካ ዶላር ነበር። በ1993 ግን አንድ የአሜሪካን ዶላር 110 ሚሊዮን የዛየር ብር ሆነ። ዛሬ 176,300 የዛየር ብር በአንድ ዶላር ይለወጣል። ከዋጋ ግሽበትም ሌላ ራሳቸውን በማበልፀግ፣ ውድ ቤተ መንግሥቶችን በመገንባትና ውድ መኪናዎችን በመግዛት ፕሬዚዳንት ሞቡቱ ዛየርን አራቁተዋል። በስዊስ ባንክም በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር አላቸው።

«በ1975 ሞቡቱ ኪዩባውያንና ሩሲያውያንን ለመታገል ወደ አንጐላ ወታደር ልከው ነበር። ሞቡቱ የቀዝቃዛው ጦርነት ውጤትና የአሜሪካ አሻንጉሊት ነበሩ። ከህዝባቸው ይልቅ ያስጠበቁት የራሳቸውንና የአሜሪካንን መንግሥት ጥቅም ነው። ሞቡቱ የአሜሪካ ወዳጅ ነበሩ። የካቢላና የህዝብ አመፅ ሲገለብጣቸውና ተዋርደው ሲሸሹ የአሜሪካ መንግሥት ለእኚህ አዛውንት ዲክቴተር አልደረሰላቸውም። አሜሪካም ያልቆመላቸው የቀዝቃዛው ጦርነት መጠቀሚያነታቸው ስላበቃ ይሆናል በማለት የሚያትቱ የታሪክ ታዛቢዎች አሉ።

ካቢላ የማርክስን ፈለግ የሚከተሉ የማካ አብዮታዊ ናቸው። ቼ ጉቬራ በ1960ዎቹ ዓመታት አፍሪቃ በሄደበት ወቅት ካቢላን «ረጋ ሠራሽ አብዮተኛ» ብሏቸው ነበር። የዩጋንዳና ሩዋንዳ የቱትሲ ኃይሎች ካቢላን ረድተዋል። ዛየርንም እንደመንደርደሪያ ተጠቅመው ሁቱዎችን ለማጥፋት ያቀዱ ይመስላል። ካቢላም በአካባቢው ሁቱዎችን እየጐዱና እየረሸኑ ነው።»

ሌላው የሚገርመው ነገር የአሜሪካ «የኃይማኖት መሪና ቀኝ አክራሪው ፓት ሮበርትስን የሞቡቱ ወዳጅ ነበሩ። ሮበርትስን የማዕድን ቁፈራ ንግድ በዛየር አላቸው። አሁን ደግሞ ካቢላን ጓደኛ ለማድረግ ብዙ ድርድር አካሂደዋል። እንግዲህ ይህ ሁሉ የምዕራባውያንን ደባ ቁልጭ አድርጐ ያሳያል ብዬ አምናለሁ።

ለእኛ የሌሎች የአፍሪቃ ሀገሮች ታሪክ ምን ያደርጋል የሚሉ ሊኖሩ ይችላሉ። በታሪኳ ኢትዮጵያ የጥቁር ህዝቦች አለኝታ ነበረች። የአደዋው መንፈስ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው። በኢትዮጵያ ለአንድነት ለፍትህና ለሀገራዊ ልዑላዊነት የሚነሳ አመራር ወይም እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ሀገር ወዳድነትንና አፍሪቃዊ ፍቅርን ይዞ መነሳት አለበት። ትግላችን የተበደሉ ግፉዐንን ሁሉ ማሰባሰብ አለበት። ትግላችን ወያኔና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ላይ ማለም ይኖርበታል። የነሚኒሊክ የነሉቡምባ፣ የነንክሩማህ መርህ ይኼው ነው።

እንጀቴ ወርቃየሁ! ሌላው በኢትዮጵያና በሌሎች የአፍሪቃ ሀገሮች ለጠላት መደላደል አመቺነትን የለገሰው የ«ተቃዋሚ» ወይም የ«ወገን» ኃይል ከልብ ታክቲካዊና ስትራቴጂያዊ ግምባር አለመመስረቱ ነው። እንደኔ ከሆነ ተቃዋሚ ኃይል ሁሉ ለጊዜው በአንድነት ጠላት ላይ መረባረብ አለበት። ጉነጣ፣ ንቀትና ፉክክር ተወግዶ ሁሉም በአንድ ላይ መሰለፍ አለበት። ግራውም፣ ቀኙም፣ መካከለኛውም ልዩነቱን አቻችሎ ከዘመተ የማይቻል ነገር የለም። አረጋዊው ወጣቱን ካንቋሸሸ፣ ወጣቱ ታላላቆቹን ካጣጣለና ልዩነት ከፈጠረ ተጠቃሚው ወያኔ ነው። በዚህ ስራችን ከቀጠልን ከወያኔ ባላነሰ መንገድ ወደፊት የኢትዮጵያ ታሪክና ህዝብ ይፋረደናል። ከግራም ሆነ ከቀኝ ሀገር ወዳድ ሁሉ ወገኔና ታጋይ ነው። ኢትዮጵያን እዚህ መቀመቅ የከተታት የመስመር ልዩነት ነው። ሁሉም ወገን መረዳት ያለበት ታሪክ ተቀባይነት የሚኖረው ቀኙ ወይም ግራው ስለጻፈው አይደለም። ህዝባችን ሁሉንም ይመለከታል። ስለሆነም እርስ በርሳችን በርቱ በመባባል ወደፊት እንግፋ። በእኔ በኩል «መንግሥቱ ኃይለማርያም መጥቶ ህዝቡን ከዘር ልዩነት አላቅቃለሁ ደግፉኝ» ቢል ካላንዳች ማመንታት እከተለዋለሁ። ነገር ግን መንግሥቱ ብዙ ወንድሞቼንና ጓደኞቼን ረሽኗል። ህዝብን ቢገድል እንኳ ሀገሬንና ባህሌን እንዳሁኑ የጐሳ መንግስት አላጠፋብኝም። የኢትዮጵያና የአፍሪቃ ህዝብ ነፃነትን ያያል! ግን ጊዜ እስኪያልፍ ያለፋል! ብቻ ተስፋችን እንዳይጨልም! እነሆ ትንሽ ግጥም፦

## የዕልቂት መከር

ሞቡቱም መንትያ ... የካቢላ ልጡ
መለስም ያው ናቸው ... አንጀት የሚመልጡ
ሕዝብን የሚረግጡ .. ዓይንን የሚያፈርጡ
ወለድ አገድ ንጠው .. ምሑር የሚድጡ፤
ዚያድ ባሬም ሆኑ ... በኃይል የረገጡ
«ለሕዝብ ቆሚያለሁ» ... ብለው ቃል ቢግጡ።
ቶምቦያም ያው ናቸው
አራፕሞይም እንዲያው
መንግሥቱም ኃይላቸው
ፈርጥሞ ጡንቻቸው
ካበቃቀላቸው፣ ከመፈክራቸው
ኢሳያስም ሆኑ ... ካስተያየታቸው፣ ካካይስት ግብራቸው
ከዲክቴተር መንበር ... ሕዝብ እስኪጥላቸው
መች የጥይት ናዳ ... ኃይል ሊመክታቸው
የትኛው ጠባቂ ... ዋቢ ሊሆናቸው
ሕዝብ ካለቀሰ ... ደም ደም ከሸተተው
ኑሮ ገበናውን ... አካቶ ከዘጋው
አሻፈረኝ ካለ ... ካልተገዛላቸው
የቱ የነጭ ቃፊር ... ቤዛ ሊሆናቸው
ይጠፉታል እንጂ ... እልፍ ነፍስ አጥፍተው
ባስካሪነት ታዘው ... ጋሻ ጃግሬ ሆነው
ዶላር ተጉራርሰው... መርዝ ለሕዝብ አብልተው
በሃብት ንረው አድገው ... ተጃጅለው ነቅዘው፤
ይጠፉታል እንጂ ... እልፍ ነፍስ አውድመው
ኢትዮጵያን «ከፋፍለው»...አፍሪቃን «አጥፍተው»
ታሪክ ላይሆናቸው ... ላይከተላቸው!!
መለኮትን ክደው ... ለሚያልፍ ዓለም ዋሽተው
ስብዕናን ሸጠው ... ተስፋን አጨልመው
ስንቱን አስለቅሰው ... ስንቱን ነገር ሰርተው
በሀገር ቀልደው ... በትውልድ አሹፈው
እነርሱም ላይኖሩ ... ሲብስ ካገር ሸሽተው፤
ግን ተስፋ አይሞትም ... የሀዝብ ዕውነት ነገር
ሰላምን መመኘት ... ማሻቀቡ አይቀር
ፍትሕን ለማምጣት ... አንገት ላለመስበር
በጭለማ ማየት ... በእንቅፋት መውተርተር
በወገን መሰደብ ... በወንድም ማማረር
ተመቶም መነሳት ... ተንቆም መከበር
አቤት የሕዝብ ፍዳ ...መዓት የእልቂት መከር።

ቸር ይግጠመን
ገብርዬ (አትላንታ ጆርጂያ)

# ከ አ ን ባ ብ ያ ን



ሰላም ላንዳፍታዎች፣ እንደምን አላችሁ? እኛ አምላክ ይመስገን ደህና ነን።

ባለፈው በሚያዝያ/ግንቦት ወር እትማችሁ ላይ ስለ ኢሚግሬሽን (በናንተ ቋንቋ ነፍስ በላው) አዋጅ ቁልጭ አድርጋችሁና አብራርታችሁ በመፃፋችሁ ለብዙዎቻችን ጥሩ ግንዛቤ በመስጠቱ ሳላመሰግን ብቀር የሕሊና ተወቃሽ እሆናለሁና እግዚር ይስጣችሁ። መጽሔቶች እንደዚህ ያሉትን ጉዳዮች በተለይ በራሳችን ቋንቋ ስትገልጹልን ከውኹንብር እንድናለንና ልምድ አድርጉ እላለሁ።

በተረፈ መፅሔታችሁ አስተማሪና ጠቃሚ ነው በርቱ — ደህና ሁኑልኝ።

አያልነህ—ከዳላስ

ይድረስ ለላንዳፍታ መጽሔት የዝግጅት ክፍል!!

በመጀመሪያ የከበረ ሰላምታዬን አቀርባለሁ። መጽሔቷን እዚህ ጣሊያን ሀገር ከሚኖር ጓደኛዬ ዘንድ አግኝቼ መልሼ መላልሼ አነበብኳት ሳይሆን አጠናኋት። መጽሔቷ ቁምነገራምና መምህር እውነትም ኢትዮጵያዊ የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት!!

ለወደፊቱ የመጽሔቷ ደንበኛ ከመሆን የሚከለክለኝ የለም። ለአሁኑ ግን የሰንጠረዡ መልስ በሚገባ ሰርቻለሁ ደንበኝነቴ ተጀመረ ማለት ነው።

የወንድወሰን ኃ/ስላሴ — ከጣሊያን(ሮም)

ሰላም እንደምን አላችሁ?

... ሰንጠረዡ አንድን ሰርቼ የተረፉኝ ፊደሎች ኢትዮጵያ ነው።

ለነገሩማ ሌላ ምን ትርፍ አለ? «ትርፋችን ሁሌም አገራችን ኢትዮጵያ ናት» ...

በርቱ — ሀሰን ዑመር ከቴክሳስ

ለላንዳፍታ ዝግጅት፣

በሰላምታ የምጀምርበት ምንም ምክንያት የለኝም። «ዘራፍ አካኪ ዘራፍ» በማለት እንጂ። ስለት ከመማዘዛችን በፊት ቦጭቃችሁ ያስቀራችሁትን የግጥሜን ግምዳይ መልሳችሁ በምትልኩበት ላኩልኝ። አለበለዚያ!...?

ለማንኛውም እኔ እንደእናንተ አይደለሁምና በቃሌ መሠረት ቀጥያለሁ። እነቦጭቁ! እንደ ልማዳችሁ ይሄንንም ቦጭቃችሁና ዕድሜውን አሳጥራችሁ አውጡ አሉ።

## ደብዳቤ ለእናቴ

እምይ የኔዋ እናት አገር ቤት ያለሽው
የኔን ኑሮ መጥተሽ ምናለ ባየሽው
ዶላር ብልክልሽ የደላኝ መስሎሻል
የኑሮ ችግሬን ማሰብ ተስኖሻል
ለመላቀቅ ብዬ ከችግር አረንቋ
ጠዋት ማታ እሰራለሁ ወገቤ እስኪንቋቋ
ስቋጥር ስፈታ እንዲሁ በተስፋ
ለነጭ እሰራለሁ ልቤ እስከሚጠፋ።
ባርነት መርጬ ይኸው ለጌቶቼ
ጉብ ቂጥ እላለሁ በውድ ተስማምቼ
እንዳጉበደድን ወገባችን ጉብጦ
በስልት ይገዛናል ነጣጥባ ረግጦ።
በአካፋ እየዛቁ ለእኛ ግን በማንኪያ
ጠብ ያረጉልናል አይሆን ለጥም ማርኪያ
ይገባ ይመስል ዶላሩ በኪሴ
ካንጀቴ እሰራለሁ እስክትወጣ ነፍሴ
እዚህ ሞላ ስለው እዚያ ጋር ሲጐድል
እንደባከንኩ አለሁ ራሴን ስበድል።
ዶላሩ አይጨበጥ አይገኝ ልባቸው
ምን ብዬ ልንገርሽ እነሱ ቆቅ ናቸው።
«ክሬዲት» እያሉ ካርቶን እየሰጡ (ክሬዲት ካርድ)
ዋዛ አርገኛቸዋል በሰው ሲያላግጡ
የደከምንበትን ዶላሩን ሳናየው
«ፔይ ቼክ» ብሎ ነገር ይሰጡናል ቀደው።
ባሜሪካ ኑሮ ምን ድሎት አለና
ልጅሽ ባዛኝ ነኝ ዛሬም እንደአምና፤
ራሲው አቡክቼ ራሴ ደፍቼ
ከማይሞላው ከርሴ አለሁ ተሟግቼ።
እንደ ቀበሮዋ ላት ይወድቅ መስሎኝ
አንቺን ሀገር ከዳሁ ዶላር አስኮብልሎኝ
እንዲያ እንደ ድመቷ ስወድቅ ስነሳ
ሥጋ አወርድ ብዬ ጉኔ ተበሳሳ።
መቾ እንዲህ ዋዛ የነሱ ስራቸው
«ሲስተም» ይሉት እዚም ይረጩት አላቸው
ቆልፎ ተብትቦ ከያዘ የማይለቅ
ጉትት ጋኔል ዓይነት አላቸው ረቂቅ
ሀገር የሚያይስከዳ ሀገር የሚያስለቅቅ
ይኸው ተደግሞብን በእነሱ ደብተራ
ከፍ አንል ዝቅ አንል አለን ሆነን ተራ።
ይህም ኑሮ ተብሎ መስዬ ለማደር
«ቴንኪዩ ማም» እላለሁ ደግሞም «ቴንኪዩ ሚስተር»
ሰጥተው ቀሚ ናቸው መቾ እነሱ የዋዛ
በጥበብ ዘዴ ነው ዓለም የተገዛ
እዚህ ምን ጠፋና ያውም ባሜሪካ
ቤትሽ ነው የሚመስል ወረቀት ፋብሪካ
መጥኔ ይስጠው አልኩኝ ለዚያ ለፖስተኛ
አይረቤ ወረቀት ለሚያሞቀው ለእኛ።
ይችም ገንዘብ ሆና የለፋንበትን
በስንቱ መሰለሽ መልሰው የሚነጥቁን
በማስታወቂያቸው ኮሜርሻል እያሉ
አጃጅለው አስቀው ከአፍ ይነጥቃሉ፤
ቁጭ አርጊያት ይሉሻል «ቢል» በሚባል ዕዳ
ቢል ጠላታችን ነው እኛን የሚጐዳ

ውጉዕዝ ከመአርዮስ ቢል ጠላታችን
እኛ እንደጠላነው አንቺም ጥይልን፤
ቢልን አውግዘሽው አምላክ ከሰማሽ
ያላንዳች ጥርጥር ቪላ ቤት አለሽ፤
ፀሎትሽን ሰምቶ ቢልን ካወደመ
መጣልሽ አበሻ ሀገሩ ከተመ።
ስንቱ ይመስልሻል የእኛ ባላጋራ
ደግሞ ሌላም አለ ታክስ ይሉት መከራ
ቢቻል እሱም ይውደም ተሳይ ለታቦት
እሱ ከጠፋልን አለሽ ጋሻ መሬት
ኸረ እሱ በሰማሽ አልከለከልሽም
እንደ አሜሪካኖች እኔስ አልነጥቅሽም።
በኪራይ በሆድሽ በሁሉ ይነጥቁሻል
በዕዳ ጉብጠሽ ኖረሽ ወደ የት ይሸሻል።
«ኮርት» ይባለው ችሎት በአንቺ ከበየነ
አለቀቀ ደቀቀ ኑሮሽ ተበተነ
ዕዳ ሳትከፍዪ እኮ የት ልትገቢ
«ጄል» ይሉት ወህኒ አላቸው ሰብሳቢ
እንዲህ እንኖራን ሆነ ዕዳ በዕዳ
ግብር ስንገብር ስንከፍል ስንጉዳ።
ስበው ይከቱሻል በአፍዝ አደንግዙ
ከቀን እስከ ማታ ብቻ ግዙ ግዙ!!
እንኪ ትባያለሽ ቤት አሻኝ ስትዪ
ውሰጅ ትባያለሽ መኪና ስትይ
ከዚያ ትኖሪያለሽ ዕዳ ስትከፍይ፤
ስንቱ አለ መሰለሽ የሚኖር ባላብ ባከኖ
ግራ የተጋባ ዕዳ በዕዳ ሆኖ።

እንዲህ እንዲያም ሆኖ ምግባቸው እንኳ አይጥም
ስታይው ይመስላል ጣት የሚያስቆረጥም
በላሁህ ስትይው ቀድሞ ይበላሻል
በየሁለት ሰዓቱ ክተቺ ይልሻል
ምግባቸው ሰላቢ ከሆድ አይቀመጥ
ስፖንጅ አለው አሉ ትበይውን ይመጥ።
ወንጀላቸው ብዙ ስራቸው አስከፊ
ስትሰሚ ስታይው ይላል ጥፊ ጥፊ።
እዚህ ቀይ ሽብር እዚያ ነጭ ሽብር
ሬዲዮ ቲቪያቸው ስሙ ነው አሸብር
ባህላቸው መጥፎ ልቅ ስልጣኔ
እዚህ ለመኖርሽ ያስብልሻል መጥኔ
በመንፈስ በአካል በሁሉ ፈዘን
እነሱን አደርጅተን እኛ ቆርቁዘን
ዕድሜያችንን ገፋን ስንገብር ለነጭ
ይህ ነው አሜሪካ ይሉት ውጭ–ውጭ።
እዚህ እንደፈጋነው አገር ቤት ብንሰራ
ዳግማዊ አሜሪካ ነበር የእኛ ተራ
ብቻ ምን ያደርጋል ታዲያ ምን ይደረግ
አገር ላይ ላንሰራ አለብን አጉል ወግ።
እንደዚህ እኖራለሁ እያልኩ ደፋ ቀና
የእሱን ይስጥህ በይው በእኔ ለሚቀና።
ካንገቴ እስቃለሁ ከነሶች ወርሼ
ትካዜ ቢገባኝ ስሄድ ሀሳብ ጥሼ
ይህን ኑሮ ካልሽው ይኸው እኖራለሁ
ቋቱ አይሞላ ነገር ስጭር እውላለሁ።

(መክብብ ከሲያትል)


**Allstate®**
**You are in good hands.**

4122 East Ponce DeLeon Ave. Suite 4
Clarkston, GA 30021
Phone: (404)508-8978
Fax: (404)299-6266

**AUTO**
**HOME OWNER'S**
**RENTERS**
**LIFE**
**BUSINESS**
**COMMERCIAL AUTO**

**CALL US FOR NEW & USED CARS LOAN**



Theodros Hailegiorgis
*Exclusive Agent*

Allstate Life Insurance Company, Northbrook, IL
Allstate Indeminity Company, Northbrook, IL
Allstate Commercial Companies
(subject to limitations and availability)

**You're in good hands.**

# የወያኔን አፓርታይድ አገዛዝ በመቃወም ኢትዮጵያውያን በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለያዩ የአሜሪካና የአውሮፓ ከተሞች ከፍተኛ የተቃውሞ ሰልፎች አካሄዱ።

ሜይ 27, 1997 የወያኔን የጐሣ መድልዖ አገዛዝ በመቃወም ከፍተኛ የተቃውሞ ሰልፎች በዋሺንግተን ዲሲ፣ በሚኒያፓልስ፣ በለንደን፣ በቦን (ጀርመን) በኦስሎ (ኖርዌይ)፣ በስቶኮልም (ስዊድን)፣ በቴላቪቭ (እሥራኤል)፣ በሜል ቦርን (አውስትራሊያ)፣ በአቴንስ (ግሪክ)፣ በአምስተርዳም(ሆላንድ)ና በኦቶዋ (ካናዳ) ተካሄደዋል። በአዲስ አበባ ከተማ ሊካሄድ የነበረው ተመሳሳይ የተቃውሞ ሰልፍ ፈቃድ ሊገኝ ባለመቻሉ ሳይደረግ ቀርቷል።

ይህ ዓለም አቀፍ የተቃውሞ ሰልፍ የተዘጋጀው ከተለያዩ የሲቪክ፣ የፖለቲካ፣ የሙያ፣ የሚዲያ፣ የሃይማኖት ድርጅቶች በተውጣጣ ጊዜያዊ ዓለም አቀፍ ኮሚቴ አማካይነት ነው።

ራሱን የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት (ሕወአት) ብሎ የሚጠራው ድርጅት የመንግሥት ሥልጣን በመያዝ በማካሄድ ላይ ያለውን የዘር መድልዖ፣ የጐጠኝነትና የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ በመቃወም የተደረገው ይህ ከፍተኛ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የዚህኑ የወያኔ መንግሥት ሰብዓዊ መብት ረገጣ በማጋለጥ ከፉኛ ተቃውሞ አሰምቷል።

## ዋሺንግተን ዲሲ

ሜይ 27, 1997 ከ2500–3000 የሚገመቱ ከተለያዩ የሰሜን አሜሪካ እስቴቶች የመጡ ኢትዮጵያውያን የተሳተፉበት የዋሽንግተኑ ሰልፍ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማንና የተለያዩ መፈክሮችን በመያዝ በካህናት አባቶች መሪነት ከጠዋቱ በ9፡00 am ከነጩ ቤተመንግስት አካባቢ ካለው ቦታ በመነሳት በእስቴት ዲፓርትሜንትና በዓለም ባንክ ህንፃ በር ረጅም ጊዜ በመቆም ተቃውሞውን በጩኸትና በመፈክር አሰምቷል። ይህ ታላቅ ቁጣና ተቃውሞ የታየበት ሰላማዊ ሰልፍ በእስቴት ዲፓርትሜንትና ዓለም ባንክ ሲደርስ ብፁዕ አቡነ መልከ ጸዴቅ በስደት የሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ተወካይ፣ ከሌሎች የሰልፉ ዝግጅት ኮሚቴ አባላት ጋር በመሆን ሰልፈኛውን በመወከል የተዘጋጀውን የተቃውሞ መግለጫ ደብዳቤ ለባለሥልጣናቱ አስረክበዋል። በተለይም በዓለም ባንክ የተቃውሞውን መግለጫውን ሊቀበሉ ለመጡ ባለስልጣናት እኚህ ታላቅ መንፈሳዊ አባት በጽሑፍ ከተገለጸው በተጨማሪ ምሬታቸውን በቃልም አስረድተዋል።

ሰልፈኛው «አትነሳም ወይ! አትነሳም ወይ! የወያኔ ግፍ አይበቃህም ወይ!» የሚል መዝሙር በመዘመርና «የዓለም ባንክ ለግፈኛው ወያኔ መንግሥት የሚሰጠውን የገንዘብ ብድር ያቁም፣ የወያኔ መንግስት ፋሺሽታዊና ዘረኛ መንግሥት ነው፣ የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ፣ ኢትዮጵያውያን ሰላምና አንድነትን እንፈልጋለን»፣ የሚሉ የተለያዩ የተቃውሞ መፈክሮችን በጩኸት በማሰማትና መፈክሮችን በመያዝ ከፍተኛ የሀገር ፍቅርና ወኔ የተመላበት ሰላማዊ ሰልፍ ያደረገ መሆኑ ታውቋል። ሰልፈኛው ለረዥም ጊዜ በዋሽንግተን ዲሲ ጐዳናዎች ላይ በዚህ መልክ ከተዘዋወረ በኋላ ቀደም ብሎ ሰልፉ ከተጀመረበት የነጩ ቤተመንግሥት አካባቢ በመመለስ ሕዝባዊ ስብሰባ በማድረግ ከተለያዩ ግለሰቦች የቀረቡትን ንግግሮች አዳምጧል። የተቃውሞ ሰልፉ አስተባባሪ ኮሚቴ ተወካይ ዶ/ር ፀሐይ ብርሃነ ሥላሴ ይህን ሕዝባዊ ስብሰባ የመሩ ሲሆን፤ የተለያዩ የኢትዮጵያውያን ማህበራትን በመወከል ግለሰቦች



ንግግር አድርገዋል። ከእነዚህም ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተወካይ ብፁዕ አቡነ መልከ ፀዴቅ፣ የኢትዮጵያ እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ተወካይ አቶ ሳአድ መሐመድ፣ ወጣቶችን በመወከል ንጉሴ መሸሻ፣ ኢትዮጵያውያን ሴቶችን በመወከል ወ/ሮ የሐረር ወርቅ ጋሻው፣ አርቲስት ታማኝ በየነና ሌሎችም ለሰልፈኛው ንግግር አሰምተው የዕለቱ ፕሮግራም ፍፃሜ ሆኗል።

በማግስቱ ማለትም ሜይ 28, 1997 ተቃውሞው በመቀጠል ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በር ላይ በመገኘት የኤምባሲው ሹማምንት ወያኔ ስልጣን የያዘበትን 6ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ የተለያዩ የአሜሪካ ባለስልጣናትና የሌሎች አገሮች አምባሳደሮችን ጠርቶ የእራት ዝግጅት በሚያደርግበት ወቅት ተቃዋሚው በቦታው በመገኘት የረበሻቸው ሲሆን በዝግጅቱ ላይ ለተገኙት እንግዶች የወያኔ መንግሥትን ማንነት የሚያጋልጡ በፅሑፍ የተዘጋጁ ወረቀቶችን የሰጠ መሆኑም ታውቋል።

ይህ ሰልፍ የተለያዩ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የተለያዩ የሙያ፣ የሚዲያ፣ የሃይማኖት፣ የወጣቶች፣ የሴቶች ድርጅቶች በአንድ ዓላማ ስር የኢትዮጵያን ጠላት በመቃወም የተሳተፉበት ሰልፍ እንደነበረ ለማወቅ ተችሏል።





"ኢትዮጵያን ዛሬ አይቶ የማያዝንላት ከቶ ማን ይኖራል፣"
አቡነ መልከጸደቅ በስደት ያለው የኢት. ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ. ክ. ሲኖዶስ ዲን



"ወያኔ በታላቁ መስጊድ ገብቶ ብዙ ሕዝብ ፈጅቷል።
. . .
የሃይማኖት ልዩነት ሳያግደን በአንድነት ኢትዮጵያችንን ለማዳን መታገል አለብን።"
አቶ ሳኢድ መሐመድ
የኢት. እስላሞች ማህበር



"የ5 ዓመት ልጄ የምትመጣው ከእግዚአብሔርና ከአገሬ በኋላ ነው። ወላጆቼ በልጅነት ዕድሜዬ ሲሞቱ ያሳደገችኝ ታፍራና ተከብራ የኖረችው አገሬና ወገኔ ናቸው..." ወ/ሮ የሐረር ወርቅ ጋሻው



"አባቶቻችን አንድነቷን ጠብቀው ያቆዩልን አገራችን እንዴት በእኛ ጊዜ ትፍረስ..."
ወጣት ንጉሤ መሸሻ



"የጋምቤላ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ እየኮራ በአንድነት በማመን ይህን ከፋፋይ መንግስት ለመጣል ዝግጁ ነው።"
አቶ ዮሐንስ አጆጙሉ





የኢትዮጵያ ወዳጅ ፕሮፍሰር ቬስታል

ብፁዕ አቡነ መልከጸዴቅ ለIMF ተወካይ
የኢትዮጵያውያንን ብሶት ሲያስረዱ






## አስሎ – ኖርዌይ

ሜይ 27, 1997 በኦስሎ ከተማ ኖርዌይ የተካሄደው የተቃውሞ ሰልፍ የተጀመረው ከጠዋቱ 11:30 am ሲሆን ያለቀው በ4:00 pm ነበር። ሰልፈኞቹ በመጀመሪያ በኖርዌይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በመገኘት በወያኔ መንግሥት ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ካሰሙ በኋላ የኖርዌይ መንግሥት ለዚህ ዘረኛ ለሆነው ለወያኔ መንግሥት የሚሰጠውን ድጋፍ እንዲያቆም በማምረር የገለፁበትን ማመልከቻ ለሚኒስቴሩ ሹማምንት ያቀረቡ ሲሆን እንደገና ኖርዌይ ፓርላማ በመሄድ ተመሳሳይ ተቃውሚቸውን አሰምተዋል። ከዚያም ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት በመሄድ ተመሳሳይ የተቃውሞ መግለጫ ደብዳቤያቸውን ለጠ/ሚኒስትሩ ተወካይ ሰጥተዋል። በኖርዌይ የሚገኙ ኢትዮጵያውያኖችን በመወከል አቶ ግርማ ዓለማየሁ ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡ ሲሆን ሰልፈኞቹ በዕለቱ የዘነበው ከባድ ዝናብ ሳይበግራቸው ሰልፉን እስከመጨረሻው ድረስ ማካሄዳቸው ቁርጠኝነታቸውን አስመስክሯል።

## ለንደን – እንግሊዝ

በለንደን ከተማ ሰልፉ የተካሄደው ሜይ 25, 1997 ነበር። እጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያኖች የተሳተፉበት ይህ ሰልፍ የጀመረው ሃድ ፓርክ ከተባለው አካባቢ ሲሆን የተቃዋሚ ሰልፈኛው የኢትዮጵያን ባንዲራ በመያዝና መፈክሮችን በማንገብ በለንደን ዋና ዋና ጐዳናዎች አቋርጦ የቆመው ትራፋልጋር አደባባይ ላይ ነበር። በዚህም ቦታ ሁለት የታወቁ አንጋፋ ኢትዮጵያውያን ንግግር አድርገዋል። ሥርዓቱን ለማስከበር የለንደን ፖሊሶች በብዛት ሆነው ሰልፈኞቹን በማጀብ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ያልተለዩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

## ኦታዋ – ካናዳ

በቶሮንቶ፣ በኦታዋና በሞንትሪል የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአንድ ላይ በመሰባሰብ የሜይ 27, 1997 የተቃውሞ ሰልፉን ያካሄዱት በኦታዋ ከተማ ነበር። ቀትር ላይ ካፒቶል ካለው ፓርላሜንት ሂል ከተባለው ስፍራ የተገናኘው ሰልፈኛ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮና የአሜሪካን ኤምባሲ በመሄድ የተቃውሞ መግለጫ ደብዳቤ ሰጥቷል። ኦታዋ የሚገኘው የወያኔ ተወካይ ጽ/ቤት የቀረበለትን የተቃውሞ ደብዳቤ ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑ ቢገለፅም ሰልፈኛው በተወካዩ ጽ/ቤት አካባቢ ጠንከር ያለ የተቃውሞ ድምፅ አሰምቷል። የኢትዮጵያንና የካናዳን ሰንደቅ ዓላማዎችና የተለያዩ ተቃውሞ መፈክሮችን ሳነገበው ሰልፈኛ ሁለት የቶሮንቶ ኢትዮጵያውያን ተወካዮችና አንድ የኦታዋ ኢትዮጵያውያን ተወካይ ንግግር አድርገዋል።

ከዚህ ሰልፍ አምስት ቀን ቀደም ብሎ የተቃውሞ ሰልፉ አዘጋጅ ኮሚቴ ለካናዳ ጠቅላይ ሚኒስቴር፣ ከሃምሳ ለሚበልጡ የዲፕሎማቲክ ኃላፊዎችና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች (NGO's) በላከው የተቃውሞ ደብዳቤ ላይ እነኚሁ የዲፕሎማቲክ ኃላፊዎችና የድርጅቶች ተወካዮች የወያኔ ተወካይ ለበዓሉ ባዘጋጀው ሪሲፕሽን ላይ እንዳይገኙ የሚያሳስብ ጽሑፍም አብሮ መላኩ ተገልጿል። በካናዳ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ድርጅቶች ለዚህ ሰልፍ መሳካት ትልቅ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ታውቋል። የኦታዋ ሰን ጋዜጣ ተቃውሞውን በተመለከተ ሰፋ ያለ መግለጫ ማውጣቱ ታውቋል።

## ቴልአቪቭ – እሥራኤል

ሰልፉ ሜይ 27, 1997 ከቀኑ 11:00 am የጀመረ ሲሆን ተቃዋሚ ሰልፈኛው ተቃውሞውን ለማሰማት የተጓዘው ወደ አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሣይና ስዊስ ኤምባሲዎች ሲሆን ሰልፈኞቹ በአማርኛ፣ በእንግሊዝኛና በእብራይስጥ ቋንቋ የተፃፉ የወያኔን ዘረኛ አገዛዝ የሚቃወሙና የሚያጋልጡ መፈክሮችን ይዘው ነበር። ለተለያዩ ኤምባሲ ኃላፊዎች የተቃውሞ ደብዳቤዎች ያቀረቡ ሲሆን በተለይ በአሜሪካ ኤምባሲ ፊት ለፊት የተካሄደው ሰልፍ ረዘም ያለ ጊዜ የወሰደ መሆኑ ሲታወቅ የስዊስ ኤምባሲ ካውንስለር ሰልፈኛውን በስርዓት ተቀብሎ እርሱም ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ በጋዜጠኞች ላይ እየደረሰ ያለው አፈና ያሳሰበው መሆኑን ገልጿል።

ከሰልፉ ቀን ቀደም ብሎ የተቃውሞ ሰልፍ አዘጋጅ ኮሚቴው የተቃውሞ ሰልፉን ዓላማ የሚገልፅ ለ25 ኤምባሲዎች መበተኑ ሲታወቅ ከሰልፉ ሶስት ቀን በፊት ይኸው ደብዳቤ ቴላቪቭ በሚገኘው የአማርኛ ሬዲዮ ሲነበብ በቴላቪቭ ያሉት የወያኔ ባለስልጣኖች ተቃዋሚ ሰልፈኛው የሚመጣው ከሌላ አገር እንጂ ከእስራኤል አይደለም በማለት ለማስተባበል ቢሞክሩም ሜይ 27, 1997 ደርሶ ሰልፈኛው ሲታይና በእስራኤል ያሉ ኢትዮጵያውያን መሆናቸው ሲታወቅ በጣም እንዳስደነገጣቸው ለማወቅ ተችሏል።

በእስራኤል አገር ወያኔን በመቃወም ኢትዮጵያውያን ሰልፍ ሲወጡ ይህ የመጀመሪያው በመሆኑ የወያኔ ባለስልጣኖች ክፉኛ መረበሻቸው ገሃድ ሆኗል። በቴላቪቭ የአማርኛ ሬዲዮ ፕሮግራም ዝግጅት ክፍል መግለጫ እንዲሰጥ የተጠየቀው የወያኔ ተወካይ በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለውን የሰብዓዊ መብት ረገጣና አፈና ሽምጥጥ አድርጐ መካዱ ተሰምቷል።

## ሜልቦርን – አውስትራሊያ

ሜይ 27, 1997 አውስትራሊያ ሜልቦርን ከተማ ብዙ ኢትዮጵያውያን የተሳተፉበት የተቃውሞ ሰልፍ ተካሂዷል። የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማና የተለያዩ የተቃውሞ መፈክሮችን የያዘው ሰልፈኛ በሜልቦርን ዋና ዋና ጐዳናዎች ላይ ከተጓዘ በኋላ ፓርላማው ፊት ለፊት ተሰባሰበ። ከዚያም ሁለት ተወካዮች ወደ ምክትል ፕሬሚየሩ ጽ/ቤት እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው በመግባት የሰልፉን ዓላማና እንዲሁም የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍ በዝርዝር አስረዱ። ምክትል ፕሬሚየሩም ይህንን አቤቱታ በአውስትራሊያ መንግሥት ለሚመለከተው ክፍሎች እንደሚያቀርቡ ቃል ገብተዋል።

የተቃውሞ ሰልፉ ዝግጅት ኮሚቴም የሰልፉን ዋና ዓላማ በተመለከተ የተዘጋጀውን ደብዳቤ ለኤምባሲዎችና የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የላከ መሆኑ ተረጋግጧል። በሰልፉ ማብቂያ ላይ ሰልፈኛው ተመሳሳይ የተቃውሞ ሰልፎችን ወደፊት ለማዘጋጀት ተስማምቷል።

## ቦን – ጀርመን

በቦን ጀርመን የሚገኘው የተለያዩ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶችን ያቀፈ የኢትዮጵያውያን ተግባር ኮሚቴ (Ethiopian Action Committee) አማካይነት ሜይ 27, 1997 በተደረገው የተቃውሞ ሰልፍ ላይ ከተለያዩ የጀርመን ከተሞች የመጡ እጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያን ተሳትፈዋል። ሰልፉ ከጠዋቱ 10:00 እስከ 3:00 ሙንስተር ፓላትዝ በተባለ ሰፊ የሕዝብ መሰብሰቢያ አደባባይ በተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የወያኔን ግፋዊ አገዛዝ የሚያጋልጡ መፈክሮች በብዛት መያዛቸው ሲታወቅ ይህንኑ ግፍ የሚገልጡ ጽሑፎች ተዘጋጅተው ለቦን ከተማ ነዋሪዎች የተበተኑ መሆኑ ታውቋል።

የሰላማዊ ሰልፍ አዘጋጅ ኮሚቴ የሰልፉን ዋና ዓላማና የወያኔን የዘር ፖለቲካ የሚያጋልጥ የምሬትና የተቃውሞ ደብዳቤ ለፕሮፌሰር ሪታ ሲስሙት የጀርመን ፓርላማ ፕሬዚዳንት፣ ለቻንስለር ሄልሙት ኮልና ለውጭ ጉዳይ ሚንስትር ዶ/ር ክላውስ ክሊንክል አቅርበዋል።

በዚሁ ከተማ ቀደም ሲል ማለትም ከአንድ ወር በፊት እጅግ በጣም ብዙ ኢትዮጵያውያን የተሳተፉበት ሰላማዊ ሰልፍ ተካሂዶ እንደነበርም ታውቋል።

## ጀኔቫ – ስዊዘርላንድ

ከተለያዩ የስዊዘርላንድ ከተሞች በመኪናና በባቡር ወደ ጄኔቫ በመምጣት ብዙ ኢትዮጵያውያን ሜይ 27, 1997 ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ አካሂደዋል። ይኸው ሰልፍ የተካሄደው ጄኔቭ በሚገኘው የተባበሩት መንግሥታት ጽ/ቤት ፊት ለፊት ሲሆን በእንግሊዝኛና በፈረንሣይኛ የተፃፉ የወያኔን ግፍ አገዛዝ የሚያጋልጡ ጽሑፎች ለተባበሩት መንግሥታት ዲፕሎማቶች መታደሉ ታውቋል።

## እስቶክሆልምና ጉተንበርግ ከተሞች (ስዊድን)

ሜይ 27, 1997 ስዊድን በሚገኙት ሁለት ከተሞች ማለትም እስቶክሆልምና ጉተንበርግ በተደረጉት ሰላማዊ ሰልፎች ቁጥራቸው እጅግ ብዙ የሆኑ ኢትዮጵያውያን መገኘታቸው ታውቋል። የአምኔስቲ ኢንተርናሽናል ተወካዮች በዚሁ ወቅት ንግግር ማድረጋቸው ሲታወቅ የቀይ መስቀል ማህበርም ተወካይ መላኩ ተረጋግጧል። በተጨማሪም ብዙ ስዊድናች በሰልፉ ላይ ተሳታፊ ነበሩ።

## ተቃውሞ ሰልፉን የማዘጋጀት ተግባር

የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶችን፣ የሲቪክ ማህበረሰቦችን፣ የሃይማኖት ድርጅቶችን፣ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ኃይሎችን፣ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንን እንዲሁም በሰሜን አሜሪካ ያሉ ኢትዮጵያዊ የሚዲያ አውታሮች አንድ ላይ ሆነው በመስራታቸው ይህ ታላቅ ዓለም አቀፍ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ሊሳካ ችሏል። ዓለም አቀፉ ጊዜያዊ ኮሚቴ ከተለያዩ አገሮች ያሉትን የአስተባባሪዎች ተወካዮች ያቀፈ ሲሆን በዚሁ ዓለም አቀፍ ጊዜያዊ ኮሚቴ ስር ደግሞ በየአገሩና አህጉሩ ሎካል አስተባባሪዎች ነበሩት።

በሰሜን አሜሪካ የተቋውሞ ሰልፉን ያዘጋጀው ኮሚቴ አባላት የሚከተሉትን ማህበረሰቦችና ድርጅቶችን ያቀፉ ነበሩ፡-

### የፖለቲካ ድርጅቶች

1) የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር
2) የመላው አማራ ሕዝቦች ድርጅት (መአህድ)
3) የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ኃይሎች ቅንጅት (ኢድኃቅ)
4) የኢትዮጵያ መድህን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድህን)
5) የአማራጭ ኃይሎች ለሰላም ለዴሞክራሲ ቅንጅት
6) የደቡብ ኦትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ቅንጅት
7) ሞዓ አንበሳ

### የሲቪክ ማህበረሰቦች

1) የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበር ለሰላም፣ ለዴሞክራሲና ለበጐ አድራጐት በዋሽንግተን
2) በምዕራቡ ዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ማህበር አንድነት
3) የኢትዮጵያ እስላሞች ማህበር
4) የሰላምና የዴሞክራሲ ፎረም
5) ማህደረ አንድነት የኢትዮጵያውያን ማህበር በአትላንታ
6) እኔ ለሀገሬ የኢትዮጵያውያን ማህበር በኒውዮርክ
7) የኢትዮጵያውያን ተቃውሞ ሰልፍ አዘጋጅ በቴክሳስ

### ሚዲያዎች

1. ኢትዮጵያ ሪቪው
2. ላንዳፍታ መጽሔት
3. ኢትዮጵያ ሬጂስተር
4. አንድ ኢትዮጵያ ሬዲዮ
5. ሕብረት ሬዲዮ



# ከዜና ማኅደር

# እንዲህ ሆነ!

## «ግንቦት 20»ን ለመቃወም የተጠራው ስብሰባ ታገደ

የኢህአዴግ አምባገነን አገዛዝ ስልጣን የያዘበትን «ግንቦት 20»ን በዓል በመቃወም አዲስ አበባ ውስጥ ግንቦት 24 ቀን ሊካሄድ የታቀደውን ህዝባዊ ስብሰባ ልዩ ልዩ ምክንያቶች በመፍጠር መከልከሉ ታውቋል።

ይህ የተቃውሞ ስብሰባ በአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት፣ በመላው ዐማራ ህዝብ ድርጅትና በደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ሕብረት በጋራ የተዘጋጀ ነበር።

የተቃውሞ ስብሰባውን ያዘጋጀው የሶስቱ ድርጅቶች የጋራ ኮሚቴ በሰጠው መግለጫ ስብሰባውን በመጀመሪያ ለግንቦት 17 ለማካሄድ የፈቃድ ጥያቄ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ቀርቦ የተለያየ ምክንያት በማቅረብ በመዘግየቱ እንደገና ለግንቦት 24 ቀን የፈቃድ ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም ግንቦት 20ን በመቃወም የተዘጋጁትን መፈክሮችና ንግግሮች በቅድሚያ ካልቀረቡልኝ ፈቃድ አልሰጥም በሚል ሰበብ መሰናክል መፍጠሩንና ስብሰባውን መከልከሉን አስታውቀዋል።

## የኢትዮጵያ ወጣቶች አንድነት ድርጅት ግንቦት 20 በሐዘን እንዲታሰብ አሳሰበ

የኢትዮጵያ ወጣቶች አንድነት ድርጅት «ወያኔ ኢህአዴግ መላው ኢትዮጵያን የተቆጣጠረበት ዕለት ግንቦት 20 ኢትዮጵያ አንድነቷና ሉዐላዊነቷ የተናደበት፣ ባንዲራችን የተናቀበትና የተጣለበት፣ ህዝቦች በሰላምና በፍቅር እንዳይኖሩ የተከፋፈሉበት፣ ሰራተኛው፣ ገበሬው፣ ነጋዴውና፣ ምሁሩ በሀገሩ የሥራ ዋስትና ያጣበት ዕለት በመሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ በሀዘን እንዲያስበው» ያሳሰበ ሲሆን በግንቦት 20 ዋዜማ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በበተነው በራሪ ወረቀት ደግሞ «ጀግናው የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ» በሚል ባቀረበው ጥሪ «በወያኔ ና በሻዕቢያ ስርዓት እየሞትክ ከመኖር ቢያንስ ጠላትን ይዞ መውደቅ የጀግና ሞት ነውና ለህልውናህ ለሚዋደቀው የኢትዮጵያ ወጣቶች አንድነት ድርጅት ድጋፍህን በመስጠት ተባበር» ሲል ጥያቄ ያቀረበ መሆኑ ታውቋል።

የዘንድሮው ስድስተኛ ዓመት የግንቦት 20 በዓል ከወትሮው ቀዝቀዝ ባለና ውጥረት በተሞላበት ሁኔታ ወያኔ/ኢህአዴግ ከአጫፋሪዎቹ ጋር አክብሮ ውሏል። ቀበሌዎች ለግንቦት 20 የገቢ ማስገኛ ድግሶችን አዘጋጅተው ነዋሪው ወደ ቀበሌው እንዲወጣ ጥሩምባ ቢያሰሙም አብዛኛው ነዋሪ ሊወጣላቸው አልፈቀደም። እንዲሁም በመስቀል አደባባይ የሙዚቃ ፌስቲቫል ተዘጋጅቶ ከጠዋቱ 3 ሰዓት ይጀመራል ተብሎ በተመልካች ማጣት ከቀኑ 11 ሰዓት ላይ ሙዚቀኞቹ በባዶ አሰምተው መሄዳቸው ታውቋል።

## በአዲስ አበባ 29 ነጋዴዎች የንግድ ፈቃዳቸውን ተነጠቁ

የአዲስ አበባ አስተዳደር በንግድ ቤቶች ላይ የመደበውን የናረ የቤት ኪራይ ተመን በመቋወም ግንቦት 11 ቀን የተካሄደውን የንግድ ሱቆችን የመዝጋት አድማ አስተባብራችኋል የተባሉ 29 ነጋዴዎች የንግድ ፈቃዳቸውን መነጠቃቸውና የንግድ ቤቶቻቸውም በጨረታ የሚሸጡ መሆኑ ተነገረ። የአዲስ አበባ አስተዳደር የንግድ ቢሮ በሰጠው መግለጫ «ግንቦት 11 ቀን እስከ ቀኑ 9 ሰዓት ድረስ በአድማው የተዘጉ ሱቆች እንዲከፈቱ ባይከፈቱ ግን የንግድ ፈቃዳቸውን እንደሚነጥቅ» በገለፀው መሰረት፣ በውሳኔያቸው የፀኑ 1100 ሱቆች ተዘግተው አድማውን ያስተባበሩ 84 ነጋዴዎች መታሰራቸውና በኋላም ተጣርቶ የ29 ነጋዴዎች የንግድ ፈቃድ መነጠቁንና የሌሎቹ «ተሳስተን ነውና በሀገወጥ አድማው የተሳተፍነው ይቅርታ ይደረግልን፣» የሚል ጥያቄ ለማቅረብ ፈቃደኛ የሆኑት ግን እሽጉ እንደተነሳላቸው አስታውቋል።

መንግሥት በሕግ ሳይሆን በኃይል የንግድ ቤቶችን ማሸጉና ፈቃድ መንጠቁ፣ ነጋዴዎችን ማሰሩ ሰብአዊ መብትን የሚፃረር ስለሆነ የታሰሩ እንዲፈቱ፣ በኃይል የታሸጉት የንግድ ቤቶች እንዲከፈቱ፣ የንግድ ፈቃዳቸው የተወሰደባቸው እንዲመለስላቸውና የነጋዴዎቹ ሠርቶ የመኖር መብት ይከበር ዘንድ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶችና የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት በተናጠል ባወጡት መግለጫ አሳስበዋል።

በተለይ ኢሰመጉ ባወጣው ልዩ መግለጫ «መንግስት ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የንግድ ቤቶችን እሽጉ እንደገና ነጋዴዎቹን ይቅርታ ጠይቁኝና ላንሳላችሁ ማለቱ አግባብነት የለውም ብሎአል። ዜጎች በህግ የተረጋገጠውን መብታቸውን ተጠቅመው ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ ተቃውሞአቸውን ባሰሙ ቁጥር መንግስት መብታቸውን እየደፈረ ይቅርታ እንዲጠይቁት የሚያስገድድ ከሆነ ዜጎች በህግ ላይተማመኑና ለሚያደርጉት ነገር ሁሉ ሕጋዊ ዋስትና ላይኖራቸው ነው» በማለት በመግለጫው አመልክቶአል።

## ኢሰመጉና የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር የአቶ አሰፋ ማሩን ግድያ አወገዙ

ባለፈው ሚያዝያ 30 ቀን 1989 አቶ አሰፋ ማሩ የአንጋፋው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልና የሕዝብ ግኑኝነት ኃላፊ በመንግሥት ታጣቂዎች ከቤታቸው ወጥተው ወደ መደበኛ ስራቸው በመሄድ ላይ እንዳሉ መንገድ ላይ መገደላቸው ይታወቃል።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) የአቶ አሰፋ ማሩን ግድያ በማስመልከት ባወጣው መግለጫ «የኢህአዴግ/ህወሀት አገዛዝ የፌዴራሉ ፖሊስ ገዳይ ቡድን አደራጅቶ አቶ አሰፋ ማሩን በአደባባይ መረሸኑን አውግዞ፤ አቶ አሰፋ የፖለቲካ ድርጅት አባል አልነበሩም ሆነው ቢገኙም እንኳ በአግባቡ ተይዘው ሕግ ፊት መቅረብ ነበረባቸው እንጂ በመንገድ ላይ በሽመቁ ልዩ የፖሊስ ገዳይ ቡድኖች መረሸን አልነበረባቸውም፤» ሲል ድርጊቱን አውግዟል።

የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር በበኩሉም ባወጣው የተቃውሞ መግለጫ «በአቶ አሰፋ ማሩ ላይ የተፈፀመው የጭካኔና የግፍ ድርጊት ማኅበሩን ለመንግስት አገልጋይ ለማድረግ ከመነጨ ፍላጐት መሆኑን አስታውቆ የመሪዎችም ሆነ የአባላት ስደት፣ እስርና ግድያ የትግሉን እቅጣጫ መግታት አይችልም» ሲል የመንግስትን እርምጃ አውግዟል።

መንግስት በግድያው ዕለት በሰጠው የሬዲዮ ዜና፤ «የኢትዮጵያ አርበኞች አንድነት ግንባር አመራር ሰዉዎች የነበሩት እነ ዶክተር ታዬ ወ/ሰማያት ከታሰሩ በኋላ አቶ አሰፋ ማሩ የግንባሩን እንቅስቃሴ በኃላፊነት ይመራ እንደነበር ተደርሶበት ለፀጥታ ኃይሎች እጁን እንዲሰጥ ተጠይቆ ፈቃደኛ ባለመሆኑ በተካሄደ የተኩስ ልውውጥ መገደሉን!» የፖሊስ ኮሚሽን መግለጫ በመጥቀስ የገለጸ ሲሆን በተጨማሪም የአቶ አሰፋ ማሩ ግብረ አበሮች ናቸው ያላቸውና በቁጥጥር ስር የሚገኙ የ7 ሰዎችን ስም ዝርዝር አስታውቋል።»

አቶ አሰፋ ማሩ የኢሰመጉ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴም አባል እንደነበሩም ይታወቃል።

## የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኰንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ዳዊ ኢብራሂም ተቃውሞአቸውን አሰሙ

የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኰንፌደሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ዳዊ ኢብራሂም በወያኔ መንግሥት የተጠመደባቸውን የእስርና የግድያ ሴራ በመሰበር ከሁለት ባልደረቦቻቸው ጋር አገር ለቀው የተሰደዱት ባለፈው ሚያዝያ ወር ሲሆን፤ አቶ ዳዊ በስደት ካሉበት ሀገር ለአሚሪካ ድምፅ በሰጡት ቃለ መጠይቅ «ማኅበሩ ሳይፈርስ ኢህአዴግ ተለጣፊውን ማኅበር በይፋ ማቋቋሙና ሌላ አመራር ተለውጧል መባሉ ፍፁም ሕገወጥ እርምጃ ነው» ሲሉ አስታውቀዋል።

አቶ ዳዊ «የኢህአዴግ መንግስት በኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ላይ የሚያደርሰውን በደል ለተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ክስ እንደሚያሰሙና አቅም በፈቀደም በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍ እንደሚታገሉም» በቃለ መጠይቁ ላይ ገልፀዋል።

## የባሕታዊ ፈቃድ ስላሴ ገዳዮች እንደሚታወቁ ኢሰመጉ ገለፀ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) በቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ጥር 1 ቀን 1989 የተገደሉት የባሕታዊ ፈቃደ ስላሴ ገዳዮች ምንነት በዓይን ምስክሮች በተጨባጭ መረጋገጡን አስታውቆ፤ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በግልፅ የፈጸሙትን ትቶ ግድያው ሲፈፀም ቦታው ያልነበሩትን ባህታውያን እስር እያንገላታ መሆኑን የኢሰመጉ ሪፖርት አመልክቶአል።

ፖሊስ ከባህታዊ ፈቃድ ስላሴ ግድያ ጋር በማያያዝ ዘጠኝ ባህታውያንን ያሰረ ሲሆን፤ የአዲስ አበባው ፍርድ ቤት ፖሊስ ያቀረበውን የክስ ይዘት በመገንዘብ ባሕታዊ ገብረመስቀልና ባህታዊ ሲፎኒያስ በዋስ እንዲለቀቁ ከሶስት ጊዜ በላይ ትዕዛዝ ቢያስተላልፍም ፖሊስ ለመፍታት ፈቃደኛ ያለመሆኑን የኢሰመጉ ልዩ መግለጫ ዘግቦአል።

## የተቃዋሚ ኃይሎች መጠናከር ኢህአዴግን አሳስቦታል

ለዘመናት ተከብሮ ሳይደፈር የኖረውን የኢትዮጵያ አንድነትና የህዝቧን ህብረት በጕሣ ፖለቲካ በመበተን ላይ ያለውን አገዛዝ ለመታገል ኢትዮጵያን ለመታደግ የኢትዮጵያ ሀቀኛ ልጆች ወደ አንድነት ግንባር እየተሰባሰቡ መምጣት የኢህአዴግን/ህወሀትን አመራር በንዴት እያወራጨው መሆኑ ተገለጠ። ግንቦት 12 እና 13 በጀርመን ከተማ ፍራንክፈርት ውስጥ ከኢትዮጵያ ውጭ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚኖሩና ከሀገር ውስጥም የተጋበዙ የተቃዋሚ ኃይሎች የተሳተፉበት ታላቅ ኮንፈረንስ መካሄዱና ኮንፈረንሱ የደረሰበት ሀገርን የማዳን ውሳኔ የጠቅላይ ሚኒስትር መለስን አመራር ክፉኛ አስደንግጧል። በኢድህቅ ውስጥ የተሰባሰቡ አራት የፖለቲካ ድርጅቶች ኢህአፓ፣ መኢሶን፣ የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ህብረት፣ የቤንሻንጉል ህዝባዊ ነፃነት ንቅናቄ፣ ከፋኝ ብሔራዊ አርበኞች ንቅናቄ፣ የቀድሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት መኰንኖች በከፊል፣ ባለሌላ ማዕረጐችና ወታደሮችን ያቀፈው የኢትዮጵያ አንድነት ግንባር ሰሞኑን ከወለጋ እስከ ጐንደር ባሉ አንዳንድ አካባቢዎች ወታደራዊ ጥቃት በመሰንዘር ውጤት እንዳስመዘገበ በመግለጽ ያወጣው መግለጫ ሌላው የህወሀት/ኢህአዴግ የስጋት ምንጭ ነው። እንዲሁም ሰሞኑን በዋሽንግተን፣ በበርሊን፣ በስዊዘርላንድ፣ በኔዘርላንድ፣ በእስራኤልና በሌሎችም ሀገሮች በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የግንቦት 20 በዓልን በተመለከተ ያካሄዱት የተቃውሞ ሰልፍና ያሰሙት የተቃውሞ ድምፅ ለኢህአዴግ/ህወሀት አመራርና ደጋፊዎች ያልተጠበቀ የራስ ምታት ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የግንቦት 20ን በዓል በተመለከተ የኢህአዴግ ልሳን ከሆነው አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ንግግር «በሀገር ውስጥ በሚንቀሳቀሱ በተቃዋሚ ኃይሎች ላይ ክንዳቸውን ለመሰንዘር አቋም እንዳላቸው ለማሳየት በአደባባይ ጦርነት ባያውጁም ለእነዚህ ጦርነት ላወጁ ፀረ ህዝብና ፀረ ሰላም ኃይሎች ተገንና መከታ በመሆን እያገለገሉ ያሉ ህጋዊ ዕውቅና ያገኙ ድርጅቶችና ኃይሎች አሉ። እነዚህ ክፍሎች በእሳት እየተጫወቱ እንደሆነ የገባቸው አይመስለኝም» ሲሉ ጠቆም አድርገዋል።

መለስ ዜናዊ ይህ በቃለመጠይቃቸው የሰጡት ማስጠንቀቂያ በግልፅ በመዐሕድና በአማራጭ ኃይሎች ላይ ያነጣጠረ ሲሆን ምናልባትም ጦርነትን ካወጁ ቡድኖች ጋር አብራችኋል በሚል ሰበብ ድርጅቶቹን ለማገድ የታለመ ነው የሚሉ ታዛቢዎች አሉ።

የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት (መዐሕድ)፣ የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤትና ሌሎችም በሀገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች በጀርመኑ የአንድነት ኮንፈረንስ ላይ ተሳታፊ እንደነበሩ ታውቋል።

## በሌንጮ ለታ የሚመራው የኦነግ አንጃ ከኢህአዴግ ጋር ተስማማ

የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር (ኦነግ) በዋና ፀሐፊው በአቶ ገላሳ ዲልቦና በአቶ ሌንጮ ለታ በሚመሩ በሁለት አንጃዎች የተከፈለ መሆኑ ሲታወቅ፤ በአቶ ሌንጮ ለታ

የሚመራው ቡድን በድርድሩ ላይ ኦነግን በመወከል ሲሳተፍ፣ ኢህአዴግን በመወከል ደግሞ የፀጥታ ሹሙ አቶ ክንፈ ገብረመድህን፣ የኦሮሚያው ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ሐሰን አሊ፣ የኦህዴድ አባልና አባዱላ በሚል የጦር ሜዳ ስም የሚታወቀው ጄኔራል ጫላ ገመዳ በመሆን በጀርመን ከተማ ቦን ውስጥ በጀርመን መንግሥትና በሻዕቢያ አደራዳሪነት በተደረገው ውይይት ከስምምነት መድረሳቸው ታውቋል።

የአቶ ሌንጮ ቡድን ባደረገው ውይይት መሰረት በቅርቡ ወደ አዲስ አበባ በመግባት ቢሮ ከፍቶ እንቅስቃሴ እንደሚያካሂድ የተገለፀ ሲሆን፤ በአቶ ገላሳ ዲልቦ የሚመራው ቡድን ግን መብት በልምምጥ አይከበርም በሚል በጦር ሜዳ ለመፋለም የቦኑን ስብሰባ ረግጦ መውጣቱ ታውቋል። የሌንጮ ቡድን ከኢህአዴግ ጋር በቦን ከተማ ባደረገው ስምምነት መሰረት፣

1. ኦነግ የኦሮሞን ህዝብ ጥቅም የሚወክል የፖለቲካ ድርጅት መሆኑን ኢህአዴግ ይቀበላል።
2. ኦነግ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ልዩ ልዩ ቀበሌዎችና ከተሞች በሐረር፣ በአዋሳ፣ በአዲስ አበባ፣ በድሬዳዋ ቢሮ ይከፍታል።
3. ኦነግ ተዋጊዎቹን ሳይበትን ይቆያል። ሠራዊቱም ቀላል የጦር መሣሪያ ትጥቅ እንዲታጠቅ ይፈቀድለታል።
4. ኦነግ የኦሮሞን ህዝብ በተመለከተ ዜናና ባህል ነክ ዝግጅቶችን ለማሰራጨት የራሱ ሬዲዮ ጣቢያ ይኖረዋል።
5. ኦነግ በወቅቱ መንግሥት ስር በሚካሄዱ አካባቢ ምርጫዎች አይሳተፍም።
6. ይህ መግባባት ሁለቱ ወገኖች በሚፈራረሙበት ስምምነት ተካቶ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀ ከአራት ዓመት በኋላ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች ባሉበት የኦሮሞ ሕዝብ የኢትዮጵያ አካል ለመሆን ወይም ነፃ የኦሮሚያ መንግሥት ለመመስረት የውሳኔ ህዝብ (ሪፈረንደም) ድምፅ ይሰጣል።
7. በዚህ የውሳኔ ህዝብ ድምፅ መስጠት ከሚችሉት ከ50% በላይ የሚሆነው ድምፅ ሰጪ የነፃ ኦሮሚያ መንግሥትን መቋቋም የሚደግፍ ቢሆን የኢትዮጵያ መንግስት በክልሉ የመንግሥትን ስልጣን ለሚመራ የሽግግር አካል ያስረክባል ይላል።

የዚህን ውሳኔና ስምምነት የተመለከቱ የፖለቲካ ታዛቢዎች ኢትዮጵያ ያለ ኦሮሞ ህዝብ ስለማትታሰብ የኢህአዴግን/ሕወሀት ሀገርን ለማፍረስ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም የሚፈፅመው ደባ መሆኑን ያሰምሩበታል። በአንድ አገር አብላጫው የህዝብ አካል ከአናሳው ልገንጠል ማለቱ ሀገርን የማፈራረስ ሴራ ከመሆን በቀር ሌላ ሊሆን አይችልም። በሌላ በኩል ደግሞ የኢህአዴግ ተለጣፊ የሆነውን የኦሮሞ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) የኢትዮጵያን አንድነት ተቀብሎ የቆየ ከመሆኑም በላይ የወያኔ መሣሪያ በመሆን የኦነግ አባላትን እያደነ ሲያስርና ሲረሽን ኖሮ አሁን ከሌንጮ ለታ ቡድን ጋር በምን መልኩ ተጣጥሞ እንደሚቀጥልም ሌላው ጥያቄ የሚያስነሳ ጉዳይ ነው። ኢህአዴግ በቅርቡ በርካታ የኦህዴድ አባላትን በግምገማ ከአባልነት ያስወገደና ያሰረም መሆኑ ሲታሰብ ኢህአደግ አዲስ የፖለቲካ ቁማር ለመጫወት የመዘጋጀቱ ፍንጭ እንደሆነም ታዛቢዎች ይገምታሉ።

በሌላ በኩል አንዳንድ የኦሮሞ ምሁራን ኦነግ ከኢህአደግ ጋር ያደረገውን መግለጫ በማስመልከት በሚሰነዝሩት አስተያየት ሙከራው የኦሮሞን ሕዝብ ትግል የሚያኮላሽና የኢህአዴግና የሻዕቢያ አመራሮች የገጠማቸውን ቀውስ ለመወጣጫ የሚታለም እንጂ በኦሮሞ ህዝብ ላይ የተጫነውን ግፍ የሚቀርፍ አይደለም ይላሉ።

## በኢህአፓ አባላት ላይ ክትትል ተጀመረ

የኢህአዴግ አገዛዝ በተቃዋሚ ኃይሎች እንቅስቃሴና በህዝብ ብሶት ከየአቅጣጫው በተወጠረበት በአሁኑ ሰዓት በኢህአፓ አባልነት የሚታወቁ ግለሰቦች በሙሉ በየቀበሌው ስማቸው በሚስጥር እየተመዘገበ እንዲያዝና ክትትልም እንዲደረግባቸው ለየመስተዳድሩ ማዘዣ ተላልፏል። ከቀበሌዎች የተገኙ አንዳንድ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ወያኔ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ ለቀበሌ መስተዳድሮች የኢህአፓ አባላት ጉዳይ ክትትል እየተደረገበት እንዲቆይ የቃል መመሪያዎችን ሲሰጥ ቢቆይም በአሁኑ ጊዜ ግን የጽሑፍ ማዘዣ ማውጣቱ የስጋቱ አቅጣጫ ይፋ እየሆነና እየጐላ መሄዱን ይጠቁማሉ።

ኢህአዴግ ስልጣን እንደያዘ በአገሪቱ የአስተዳደር መዋቅሮች ውስጥ በቀድሞ የደርግ መንግሥት ተደልድለው ይሰሩ የነበሩ ግለሰቦችን በማባረር የራሱን ካድሬዎች በመተካት፣ እንዲሁም የኢህአፓ አባላትን ደግሞ «በፎረም 84» አዋቅሮ በጉደሉ የስልጣን መደቦች የኢህአፓ አባላትን በመመደብ ሲሰራ ቢቆይም የኋላ ኋላ አብዛኞቹ የኢህአፓ አባላት የኢህአዴግን የፖለቲካ አቅጣጫ በማውገዝ ገሸሽ በማለታቸውና በተጨማሪ ደግሞ በአሁኑ ወቅት ከሀገር ውጪና በሀገር ውስጥ በበረሃ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ የኢህአፓ አባላት መግለጫዎች መበራከት በሀገር ውስጥ ባሉ የኢህአፓ አባላት ላይ ለተላለፈው የክትትልና ምዝገባ ማዘዣ መንስኤ መሆኑ ይገመታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ኢህአፓ ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ «ለእናት ሀገር አንድነትና ለሕዝቦቿ እኩልነት ተግባራዊ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ ከቆዩ ኃይሎች ጋር በመተባበር የኢትዮጵያ አንድነት ግንባር (ኢአግ) መስርቶ ፀረ ወያኔ ትግል በማካሄድ ላይ መሆኑንም ገልጾአል።»

## የኢህአዴግ አመራር በሰብአዊ መብት ረገጣ ተወነጀለ

የኢህአዴግ አመራር ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በከፍተኛ ደረጃ የሚረግጥ በመሆኑ እርምጃውን ለማስቆም አቋም ይወሰድበት ዘንድ የኢትዮ–ካናዳ የሰላምና የእድገት ድርጅት አመለከተ።

ይህ መቀመጫው ካናዳ ቶሮንቶ የሆነው ድርጅት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለሰብአዊ መብት ኮሚሽን ከፍተኛ ኮሚሽነር ቢሮ በጻፈው ደብዳቤ በኢትዮጵያ ሕግ አልባ ግድያ፣ ግርፊያና መሰቃየት፣ በኃይል አፍና መሰወር፣ በግፍ ማሰርና የሥራ መብትን ማሳጣት ጣሪያውን የዘለለ እርምጃ መሆኑን ገልጾ፤ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ በህገ ወጥ መንገድ የተገደሉ፣ የታፈኑ፣ ግርፋትና ድብደባ፣ የፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር የሰብአዊ መብት የተጣለባቸው ሁኔታዎች በመዘርዘር በማስረጃ ሲያቀርብ 184 ሰዎች ተገድለው፣ 8389 ሰዎች ያላግባብ ፍርድ በተጓደለ መልኩ መታሰራቸውን፣ 16800 ደግሞ ሠርቶ የመኖር መብት

ማጣታቸውን፣ 98 ታፍነው አድራሻቸው መሰወሩን፣ 4357 ደግሞ የጡረታ መብት መነፈጋቸውን፣ 501 የንብረት ባለቤትነት መብታቸው መገፈፉን፣ 43 ሰዎች ከግድያ ሙከራ ጋር በተያያዘ የመቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸው ዘግቦአል።

## አቶ አበራ የማነአብ የዓይን ሕመምተኛ ሆኑ

በታህሳስ ወር 1985 አዲስ አበባ ውስጥ በተካሄደው የሰላምና እርቅ ኮንፈረንስ ላይ ኢድህቅን በመወከል ለመሳተፍ አዲስ አበባ ሲገቡ የታሰሩትና ካለፉት ሶስት ዓመታት ጀምሮ ያለ ምንም ፍርድ በእስር የሚማቅቁት የኢድህቅ የውጭ ግኑኙነት ኃላፊና የመኢሶን ሊቀመንበር አቶ አበራ የማነ አብ በዓይን ህመም እየተሰቃዩ መሆኑ ተገለፀ።

ለአቶ አበራ የዓይን ህመም መንስዔ የሆነው ለብዙ ጊዜያት ብርሃን እንዳያገኙ በጨለማ ቤት በመታሰራቸው ሲሆን፤ ከፍተኛ ወንጀል ከፈፀሙ እስረኞች ጋር በጨለማ ቤት ውስጥ እንዲታሰሩ የተደረገው ከአንድ ዓመት በፊት ከአዲስ አበባ ወህኒ ቤት ያመለጡ እስረኞችን «አንሳስተሀል» በሚል ሰበብ መሆኑ ታውቋል።

## ስብሀት ገ/እግዚአብሔር በሀሺሽ ንግድ ጉዳይ ታሰረ

በኢትዮጵያ ውስጥ በደራሲነቱና በጋዜጠኛነቱ የታወቀው ስብሃት ገብረእግዚአብሔር በሀሺሽ ንግድ ዝውውር ጉዳይ መታሰሩ ታወቀ።

ስብሀት ገብረ እግዚአብሔር በተለይ ከ1983 ጀምሮ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ «እግረ መንገድ» በተሰኘው ገጽ አዘጋጅና የፅሁፉ አቅራቢ ሆኖ ሲሰራ መቆየቱ ሲታወቅ በአንድ ወቅት ባቀረበው ጽሁፍ ላይ አቶ መለስ ዜናዊ «የሰላም ሰው» ተብለው እንዲሸለሙ ሀሳብ አቅርቦ እንደነበር ተገልጿል። የስብሀት ባለቤቱና ሴት ልጁ የታሰሩ ሲሆን ሴት ልጁ ግን ከትንሽ ቀናት በኋላ መፈታቷ ተገልጿል።

ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ የሀሺሽ ንግድና ዝውውር በከፍተኛ ደረጃ የተስፋፋ ሲሆን በእጽ ዝውውሩ ላይ የኢህአዴግ ተጋዳላዮች ተሳታፊ መሆናቸው ደግሞ ችግሩን የበለጠ ማባባሱ ታውቋል።

## ከኤርትራ ዱቄት ወደ ትግራይ ለማሻገር የሞከሩ ነጋዴዎች ተቀጡ

ኤርትራ በገፍ ቡና፣ ስኳር፣ በርበሬ፣ ሌጦ፣ የቅባት እህሎችና ሌሎችንም መሠረታዊ ሸቀጦች ከኢትዮጵያ ያለገደብ በማጋዝ ላይ ባለችበት በአሁኑ ወቅት የኤርትራ ልዩ ፍርድ ቤት 410 ኩንታል የፉርኖ ዱቄት ወደ ትግራይ ለማሸጋገር የሞከሩ 2 ነጋዴዎችን ከ56 ሺህ ብር በላይ እንዲቀጡ መወሰኑ አነጋጋሪ ሆኖአል።

የኤርትራው ልዩ ፍርድ ቤት ጠበቃ የማይቆምበትና ይግባኝ የማይባልበት ሲሆን ወደ ትግራይ ዱቄት ለማሻገር የሞከሩትን ነጋዴዎች የቀጣው ዱቄት ከኤርትራ እንዳይወጣ የሚያዘውን የሻዕቢያን መመሪያ ጥሳችኋል በሚል መሆኑ ታውቋል። ቡናን የመሳሰሉ የኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ ምርቶች ያለአንዳች ገደብ ወደ ኤርትራ እየተጋዙ ባለበት ወቅት በህጋዊ መንገድ የተገዛ ዱቄት ወደ ኢትዮጵያ ለምን ተጓነ በሚል የኤርትራ ልዩ ፍርድ ቤት የሰጠው የቅጣት ውሳኔ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያን እያደኸዩ፣ ኤርትራንና ኤርትራውያንን ለማበልፀግ የሚደረገውን የተዛባ የኢህአዴግና የሻዕቢያ እርምጃ ባህርይ ምንነትን በጉልህ ያሳያል በማለት ኢትዮጵያውያን ቁጣቸውን ይገልፃሉ።

## የሻዕቢያ አገዛዝ ለ3ኛ ጊዜ የሽግግር መንግስት ሊያቋቁም ነው ተባለ

የኤርትራ ሕገመንግስት በቅርብ ጊዜ ያፀደቀው ጉባኤ እንደገና አዲስ የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም ወስኖአል። ይህ አዲስ የሚቋቋመው የሽግግር መንግስት በሕገመንግስቱ መሠረት ቋሚ መንግስት እስኪመሰረት የመቆየት ስልጣን አለው።

ለዚህ የሽግግር መንግስት መቋቋም ውሳኔ የሰጠው ጉባኤ የሽግግሩ መንግስት ምክር ቤት 150 የአመራር አባላት እንዲኖሩት ሲያፀድቅ የምክር ቤቱ ወንበር ድልድል ደግሞ የሻዕቢያ ድርጅት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት 75፣ ከስድስቱ የኤርትራ አስተዳደር ዞን የተወከሉ 60፣ በውጭ በሚኖሩ ኤርትራውያን የሚወከሉ 15 አባላት የሚይዙት ይሆናል ተብሎአል።

በሌላ በኩል ደግሞ የኤርትራ መንግስት በቅርቡ «ናቅፋ» ተብሎ የሚጠራ ብር አትሞ እንደሚያወጣ አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተገነጠለችበትን 5ኛ ዓመት ባከበሩበት ዕለት አስታውቀዋል። ኤርትራ መንግስት ከሆነችበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያን ብር ስትጠቀም መቆየቷ ሲታወቅ፤ የዓለም የገንዘብ ድርጅት፣ የዓለም ባንክና ሌሎችም ድርጅቶች ኢትዮጵያና ኤርትራ በተመሳሳይ ገንዘብ መጠቀማቸውን ሲቃወሙት መቆየታቸው ይታወቃል።

## ኤርትራ የአጃንስ ፍራንስ ፕሬስ (AFP) ጋዜጠኛን አሰረች

ሩዝ ሲመን የተባለች ፈረንሳዊት ጋዜጠኛ ኤርትራ መታሰሯ ሲታወቅ ጋዜጠኛዋ ልትታሰር የቻለችው አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ «የኤርትራ ወታደሮች ከሱዳን ተቃዋሚዎች ጋር በመሆን ሱዳንን እየወጉ መሆናቸውን» የገለፁትን መሰረት አድርጋ ሪፖርት በማድረጓ ሲሆን አቶ ኢሳያስ ይህን በተናገሩ በማግስቱ የሻዕቢያ ፓርቲ በሱዳን ጉዳይ ጣልቃ አልገባንም በማለቱ የተዛባ ዜና አቅርበሻል በሚል ምክንያት ነው።

ጋዜጠኛዋ ከአፕሪል 25, 1997 ጀምሮ ያለ ምንም ፍርድ መታሰሯ ሲረጋገጥ፤ የፈረንሳይ ዜና አገልግሎት ለአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ በቀጥታ በፃፈው ደብዳቤ ጋዜጠኛዋ እንድትፈታ የጠየቀ ቢሆንም ይህ ዜና እስከደረሰን ድረስ የተወሰደ እርምጃ የለም።

# ከኢትዮጵያ አንድነት ግምባር (ኢአግ) የተሰጠ መግለጫ

ግንቦት 1989 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት የወያኔን እብጠት ማስተንፈሱን ቀጥሏል!!

የኢትዮጵያ አንድነት ግንባር ከሚያዝያ ወር 1983 ዓ.ም ጀምሮ በኢዴኃቅ ውስጥ የተሰባሰቡትን አራት የፖለቲካ ድርጅቶች ማለትም (ኢሕአፓን፣ መኢሶንን፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ሕብረት(ኢዴሕ)፣ ኅብረ ሕዝብን) እንዲሁም በርካታ ማኅበሮችንና ግለሰቦችን፣ የቤንሻንጉል ሕዝባዊ ንቅናቄን፣ የከፋኝ ብሔራዊ አርበኞች ንቅናቄን፣ እንዲሁም የተወሰኑትን የቀድሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት መኮንኖችን፣ ባለ ሌላ ማዕረጎችንና ወታደሮችን አካትቶ በአንድ የጋራ ሀገራዊ መድረክ ለአንድ ሀገርን የማዳን ዓላማ መቋቋሙን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ካበሰረ ወራት ተቆጥረዋል።

የኢትዮጵያ አንድነት ግምባር ከተቋቋመበት ዕለት ጀምሮ «ኢትዮጵያን አጥፍተን እንጥፋ» ብሎ የተነሳውን የወያኔ ገ/ኢሕአዴግ አመራር በነፍጥ ብቸኛ ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ እብሪት ለማስተንፈስና የጥፋት ተልዕኮውንም ለመግታት፣ በዓላማው በይዘቱና በተግባሩም ሀገራዊና ኅብረ ብሔራዊ የሆነ፣ ለሁሉም ኢትዮጵያ አለኝታ የሚሆን፣ የኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት ምስረታን ሲያካሂድ እንደቆየ ስለግምባሩ መቋቋም በገለጸበት የታህሳስ ወር 1989 ዓ.ም. መግለጫው ለወዳጅም ለጠላትም ይፋ አድርጓል።

የኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት የተወሰኑ አሃዶችን ከወለጋ እስከ ጎንደር ባሉት የተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ መድቦ እያንቀሳቀሰ አንዳንድ ወታደራዊ እርምጃዎችንም እየወሰደ አዳዲሶቹንም በማሰልጠንና ሌሎችንም ወታደራዊ ዝግጅቶች በማድረግ ከአካባቢዎችና ከሕዝቡም ጋር አዳዲስ አባላትን በማስተዋወቅ ተገቢ ስራዎችን እየሰራ ቆይቷ ል።

ቁንጥንጡ የወያኔ አመራር በኢትዮጵያ ምድር ያለ እሱ ምንም ነፍጥ እንዲጨብጥ ካለመፈለጉም በላይ የአንድነት ኃይሉን በተለይም በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ታዋቂና ተቀባይነት አላቸው ብሎ የሚገምታቸውን ድርጅቶች ያካተተን የኅብረት ግምባር ጦር መፈጠር እውቆና ሰምቶ የሀሊና እረፍት ሊያገኝ ስላልቻለ በተለመደው ጥድፊያ በአንድ በኩል የኢ.አ.ግ.ን ጦር ከደቡብ ሱዳን ሕዝባዊ አርነት ሠራዊት ጋር ለማጋጨት ሲጥር፣ በሌላ በኩል ከኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት ምሥረታ ጋር ምንም ግኑኝነት የሌላቸውን የጎረቤት ሀገሮች በመክሰስና በማስፈራራት ላይ ተሰማራ፣ በጌቶቹና በሌሎችም አማካይነት የጎረቤት መንግሥቶችን ማሳጣቱን ተያያዘው። የኢትዮጵያ አንድነት ግምባር ሠራዊቱን የመሰረተው፣ ያሰለጠነውና ያስታጠቀው በራሱ ጥረት ላይ ተመስርቶ አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ በከፍተኛ ጥንቃቄ በተሰሩ ፖለቲካዊ፣ ድርጅታዊ፣ ወታደራዊ ስራዎች አማካይነት ስለሆነ የወያኔ መሪዎች መቁነጥነጡ የትም አላደረሳቸውም።

አሁንም የኢ.አ.ሠ. የተለያዩ አሃዶች በሶስቱም ክፍለ ሀገሮች ውስጥ እንቅስቃሲያቸውን ቀጥለዋል። በጎንደር ክፍለ ሀገሮች ውስጥ ከተሰማሩት አሃዶች መሐከል ከፊሉ በሚያዝያ ወር ውስጥ በተለያዩ ጊዜዎች በሁለት አካባቢዎች ላይ የወያኔ አመራር በየአካባቢው እየማገዳቸው ካሉት የወያኔ ኢሕአዴግ ሠራዊት አባላት ጋር ውጊያዎችን አካሂደዋል። ልዩ ስሙ ሳንኪሳ በተባለው የቋራ አካባቢ በሚያዝያ 5 ቀን 1989 ዓ.ም.(April 13, 1997) በተካሄደው ውጊያ ከወያኔ/ኢህአደግ ሠራዊት አባላት 27 ሲገደሉና በርከት ያሉ ሌሎች ሲቆስሉ ከኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት በኩል አንድ ታጋይ ተሰውቷ ል።

በዚያው በሚያዝያ ወር ውስጥ ጎጃምና ጎንደርን በሚያዋስነው ዓይማ ወንዝ አቅራቢያ ይንቀሳቀሱ ከነበሩ ሌሎች የኢ.አ.ሠ. አሃዶች ጋር ልዩ ስሙ ጃዊ በሚባል ስፍራ በተካሄደ ጦርነት ከእነዚያው የእነ አቶ መለስ ዜናዊ የስልጣን ማስጠበቂያ መሣሪያ ከተደረጉት የተፈረደባቸው የወያኔ/ኢሕአዴግ ሠራዊት አባላት መካከል 35 የሚሆኑ ሲገደሉ 10 የሚሆኑት ደግሞ ከባድና ቀላል የመቁሰል አደጋ ሲደርስባቸው የቀሩት በነፍስ አውጪኝ ሸሽተው አምልጠዋል። በወገን ጦር ላይ የደረሰ ጉዳት አልነበረም። የወያኔ አመራር ከብዙ ዓመት የትጥቅ ትግል ተሳትፎአቸው በኋላ እፎይታ ያሳጣቸውን የሕወሃት ሠራዊት አባላት ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አጣልቶ የእሳት እራት እሚሆኑባቸው ሁኔታዎች ውስጥ እየመረጣቸው እስከመቼ እንደሚቀጥል ባናውቅም ለሰላማዊ ፍትሕ በሩን ገጥግጦ በመዝጋቱ እነሆ በአዲስ ምዕራፍ ጦርነት የህይወት መጥፋት የማይመለጥ ጉዳይ ሆኗ ል።

የወያኔ አመራር ከሠራዊቱ ጋር ባሰማራቸው ምርጥ ካድሬዎቹ አማካይነት ሠርቶ ኗሪ በሆነው በሠላማዊ ህዝብ ላይ የተለመደው ጭካኔውን የተላበሱ ጭፍጨፋዎች እንዲካሄድ አድርጓል። የኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት አሃዶች በመሣሪያ ሊፋለሙት፣ ከፊቱ ቆመው እያሉለት በሰላማዊ የከብት እረኞች ላይ ኢሰብአዊ ጭፍጨፋ በማካሄድ ከ5–7 የሚደርሱትን በዚሁ በሚያዝያ ወር በቋራ በረሃ ውስጥ አሰቃይቶ ገድሏቸዋል። የኢ.አ.ሠ. በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ላይ የሚፈጸመውን ግፍና በደል በዝምታ እንደማያልፈው ለወያኔ መሪዎች አከብሮ ይገልጣል።

በዚህ አጋጣሚ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ለማንኛውም የጎሳ ፖለቲካ ሰለባ ላልሆነ አፍቃሪ አንድነት ኢትዮጵያዊ፣ የሰላማዊ ትግል በር ተዘግቶበት ለመብቱና ለህገሩ አንድነት ለመታገል በመቁረጥ አማራጭ ስልት በመፈለግ ላይ ላለው ወገናችን ሁሉ በተለይም ለወጣቱ ትውልድ ክፍል፣ ከኢትዮጵያ አንድነት ግንባርና ከኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት ኢ.አ.ሠ. ጋር እንዲወግን፣ አብሮ እንዲሰለፍ፣ ቆርጦም እንዲነሳ ጥሪያችንን በድጋሚ እናቀርባለን። እስካሁን ኢ.አ.ግን ላልተቀላቀሉ የተደራጁ ክፍሎችም ግንባሩ በሩን ከፍቶ እንደሚጠብቃቸው ልናረጋግጥ እንወዳለን።

የኢትዮጵያ አንድነት ግንባር/ሠራዊት ከሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ያለ ጥርጥር ያሸንፋል!!!

ለመብትህ፣ ለክብርህ፣ ለአንድነትህ ስትል ተነስ! ተደራጅ! ተሰለፍ! ታጠቅ!

ከአምላክ ቀጥሎ ኃይልና ጉልበት የሕዝብ ነውና በራሳችን እንተማመን!



የኢትዮጵያ አንድነት ግምባር (ኢአግ) ሠራዊት በከፊል



# አልሰሙ እንደሆን !

**ያልሰሙት ዜና ሊሆን ይችላል በሚል ግምት ትንሽ ዘግየት ያሉ ዜናዎችን አጠር አድርገን የምናቀርብበት አምድ**

◈ በአርባ ምንጭ ከተማ በተካሄደው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችና በመካነ ኢየሱስ እምነት ተከታዮች መካከል በተነሳው ግጭት 3 የፕሮቴስታንት የፀሎት ቤቶች የተቃጠሉና ንብረቶችም የወደሙ ሲሆን በተከታዮቹም ላይ የሞትና የመቁሰል አደጋ የደረሰ መሆኑ ታውቋል። ግጭቱ የተካሄደው የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች በከተማው ስታዲየም ኮንፈረንስ በማካሄድ ላይ እንዳሉ እንደሆነ ታውቋል።

◈ በጠባብ ጉሳ አመለካከት የተመሰረተው የኢህአዴግ አገዛዝ በየአካባቢው የመሰረታቸው ትናንሽ መንግሥታትና በየመዋቅሩ የሰገሰጋቸው ካድሬዎች መጠኑ ተለይቶ የማይታወቅ የሀገር ሀብት እየዘረፉ ሲሆን በአፋርና በደቡብ ክልላዊ ህዝቦች ብቻ ወደ 382 ሚሊዮን ብር መመዝበሩን የምርመራው ክፍል አስታውቋል።

◈ መለስ ዜናዊ በኢህአዴግ/ህወሀት የፓርቲ ስርዓት ውስጥ የፈላጭ ቆራጭነት አመራር እያሳዩ በመምጣታቸው በፓርቲያቸው ውስጥ አንጃ የመፈጠር አዝማሚያ መከሰቱን የሚጠቁሙ መረጃዎች ሲኖሩ በቅርቡ ሁለት እውቅ ተዋጊና የመለስ ልዩ ጥበቃ ቡድን አባላት ከቤተ መንግስት ወጥተው በመሰወራቸው ያልተጠበቀ ስጋት በቤተመንግስት አካባቢ ሰፍኖአል።

◈ አዲስ አበባ ውስጥ ካለፈው 4 ወር ወዲህ በሶስት የተለያዩ የንግድ ቦታዎች ላይ የእሳት ቃጠሎ መድረሱ ታውቋል። በመጀመሪያ የተቃጠለው በጨርቆስ አካባቢ ለ900 ሱቆችና ቤቶች መቃጠል መንስዔ የሆነው፤ ከዚያ በመቀጠል ከሚኒልክ ቤተመንግስት አጠገብ በአቧሬ ገበያ ላይ የፋሲካ ዕለት 44 የንግድ ሱቆች የተቃጠሉ ሲሆን፤ እንደገናም በመርካቶ ገበያ ሸማ ተራ በተባለው የንግድ ስፍራ 33 የንግድ ሱቆች እንዳልነበሩ ሆነዋል። የእሳት ቃጠሎው መንስኤውና በሽምቅ የሚለኩሰው ክፍል ባይታወቅም የንግድ ሱቆቹ ከተቃጠሉ በኋላ መንግስት መልሶ እንዳይገነቡ መከልከሉ ለንግድ ሱቆቹ መቃጠል የመንግስት እጅ እንዳለበት ፍንጭ ይሰጣል ሲሉ ታዛቢዎች ይናገራሉ።

◈ የአዲስ አበባ የፀጥታ ሁኔታ እያሰጋ በመሄዱ የስዊድን ኤምባሲ የዲፕሎማቲክ አባላቱን እንደሚቀንስ አስታወቀ። ከሚያዝያ ወር መግቢያ ጀምሮ በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ባልታወቁ ተቃዋሚ ኃይሎች በሽምቅ የሚጣለው የፈንጂ አደጋና አሁንም የቀጠለው ለኤምባሲዎችና ለትላልቅ ተቋማት የሚሰራጨው በራሪ ወረቀትና በስልክ የሚሰጠው የማስፈራሪያ ማስጠንቀቂያ የአዲስ አበባ ከተማን ፀጥታ ከፍተኛ ስጋት ላይ ጥሎታል። በሚያዝያ ወር ብቻ በአዲስ አበባ ውስጥ በትግራይ ሆቴል፤ በብሉ ቶፕስ ሬስቶራንትና በጣና ገበያ አዳራሽ በተጠመዱና በተወረወሩ የፈንጂ አደጋዎች ከ80 ሰዎች በላይ ቆስለው 3 ሰዎች መሞታቸው ሲታወቅ በድሬዳዋው ደግሞ 11 ሰዎች መቁሰላቸው ይታወቃል። ከዚያም በመቀጠል አዲስ አበባ የሚገኘው የብሪትሽ ካውንስል ህንፃ ላይ በአሜሪካ የንግድ ቢሮ ውስጥ ፈንጂ ተጠምዷል የሚል ማስጠንቀቂያ በመድረሱ በፒያሳ አካባቢ የሚገኙ የንግድ መደብሮች በሙሉ ተዘግተው አሰሳ ተካዶ እንደነበረም ታውቋል። በእነዚህ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ውስጥ ያልታሰበና ያልተጠበቀ የመንገድ ላይ አሰሳና የመኖሪያ ቤት ፍተሻ እየተደረገ መሆኑም ተገልጿል።

◈ በጅማ ቦንጋ ውስጥ የህዝብ ማመላለሻ አውቶቢሶችን በማስቆም በሰላማዊ ሰዎች ላይ ዝርፊያና ግድያ የፈፀሙ የኢህአዴግ/ህወሀት ተጋዳላዮች መያዛቸው ታወቀ። ዘራፊዎቹ ቴፒ ከሚገኘው የኢህአዴግ/ህወሀት የጦር ሰፈር የወጡና በተለያዩ ጊዜያት በህዝብና በተሽከርካሪዎች ላይ እያደቡ አደጋ ሲያደርሱ የቆዩ መሆናቸው ሲታወቅ ከአካባቢው በተገኘው መረጃ መሰረት ታጋይ ሠአረ ማህተመና አባይ በርሄ ለፍርድ የሚቀርቡ መሆኑም ታውቋል።

◈ በአትላንታው ኦሎምፒክ በሴቶች ማራቶን ድልን የተቀዳጀችው ኢትዮጵያዊቷ ፋጡማ ሮባ አሁንም በ101ኛው የቦስተን ማራቶን ውድድር የማትበገር ጀግና መሆኗን በድጋሚ አስመስክራለች። ይህ የቦስተን የሴቶች ማራቶን በጀርመናዊቷ ዩታ ፒፒግ ለ3 አመታት ተይዞ የነበረ ሲሆን ዘንድሮ በፋጡማ ተወስዷል። ሁለተኛና ሶስተኛ የወጡት የደቡብ አፍሪካ ተወላጆች ሲሆኑ ጀርመናዊቷ ዩታ አራተኛ፤ ደራርቱ ቱሉ ደግሞ አምስተኛ መሆኗ ታውቋል።

◈ ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል እንዲሉ ኤርትራ ከኢትዮጵያ በምታግዘው ቡና በዓለም ገበያዎች የቡና ምርት ተወዳዳሪ አቅራቢ መሆንዋን ሰምተዋል?

◈ ኤርትራ የሉሬት ካቢላን (አዲሱ የዛየር ፕሬዚዳንት) ቡድን ሠራዊት ታሰለጥን እንደነበረና በሌላ በኩል ደግሞ ኢህአዴግ ለፕሬዚዳንት ሞቡቱ ቅጥረኛ ወታደሮችን መላኩን ያውቁ ነበር?

◈ በኤርትራ የአምባገነኑ የሻዕቢያ አገዛዝ ተቃዋሚ ከሆኑት ቡድኖች አንዱ «ጓል ቀሺ» በምትባል ተጋዳላይ የሚመራው ቡድን ከአስመራ 35 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ህብርቲ በምትባል አካባቢ ሁለት የሻዕቢያ የጦር ሠራዊት ሻምበሎችን ከመኖሪያ ቤታቸው አውጥቶ ገድሎአል።

# የሲቪክ ድርጅቶች ሚና

## ከዶክተር ጌታቸው መታፈሪያ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

የሲቪክ (ብዙሃን) ማህበራት ወቅታዊነትንና አስፈላጊነት በተመለከተ ገብርዬ በጀመረው ሃሣብ ላይ ጌታቸው በጋሻው አክሉበት በብዙዎቻችን ዘንድ ትልቅ የውይይት መድረክ መክፈቱ ተሰምቶናል። ይኸው ውይይት ጠለቅ ባለ መልኩ እንዲካሄድ በማሰብ የፖለቲካ ሣይንስ ምሁር የሆኑትን ዶክተር ጌታቸው መታፈሪያን ቃለ መጠይቅ አቅርበንላቸው ያገኘነውን መልስ ቀጥለን እናቀርባለን።

**ላንዳፍታ፣**

የሲቪክ ድርጅቶች ስንል ምን ማለታችን ነው? አመሠራረታቸውስ? ምን ዓላማን ተመርኩዘው እንደሚሰሩ? አባሎቻቸውስ ምን ዓይነት መሆን አለባቸው? ሊያመጡ የሚችሉት ለውጥ? የሚያደርጉት አስተዋጽኦ? ሊገጥማቸው የሚችለው ችግር? ችግራቸውን ሊቋቋሙበት የሚችሉበት ዘዴ? ምናልባት የሚታወቁ ድርጅቶች ካለ የእሱን አመሠራረትና ተግባር በማውሳት መግለፅ ቢቻል፤ በሙያ፣ በሃይማኖት እምነት፣ በፖለቲካ ዓላማ፣ በመሳሰሉት መስከ ሊመሰረቱ ስለሚችሉ ድርጅቶች... ጠቅለል ባለ መልኩ ቢገልጹልን?

**ዶ/ር ጌታቸው፣**

ህዝባዊ ድርጅቶች ማለት ከመንግሥት ውጪ የተቋቋሙ የፈቃደኞች ስብስብ (Voluntary Association) ማለት ነው። ህዝባዊ ድርጅቶች የቆሙበት ዓላማ በይፋ የታወቀ ነው። አባላቱም ይህን ዓላማ እውን ለማድረግ ወይም ያመኑበትን መብት ለማስጠበቅ በገሐድ የሚታገሉበት መድረክ ነው።

በአጭሩ የሲቪክስ ወይም ህዝባዊ ድርጅቶች ማለት የሚከተሉትን መልክ የያዙ ናቸው፦

1ኛ) በህዝብ የተቋቋሙ፣ 2ኛ) ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች ተገለው ለቆሙበት ዓላማ የሚታገሉ፣ 3ኛ) መተዳደሪያቸው ከአባላትና ከደጋፊዎች በሚሰበሰብ መዋጮ ወይም ክፍያ የሆነ፣ 4ኛ) በትረ መንግሥት ለመጨበጥ ዓላማ የሌላቸው 5ኛ) የቆሙለትን ዓላማ ፍጹም ለማድረግ በመንግሥት ተቋማት ላይ ተጽእና የሚያደርጉ፣ 6ኛ) በመጨረሻም እንደኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ደግሞ ህዝባዊ ድርጅቶች ህዝቡን ስለመብቱና ግዴታው ያስተምራሉ፣ ንቃተ ህሊናውንም ያዳብራሉ ተብሎ ተስፋ ተጥሎባቸዋል።

እንግዲህ እነኚህ ህዝባዊ ድርጅቶች ዓላማቸውና ተግባራቸው በመንግሥት ደረጃ ታውቆ፣ በአገሩ ህገ መንግሥት መሠረት ህጋዊ ሰውነት ኖሯቸው ለመንቀሳቀስ ፈቃድ ያላቸው ናቸው።

እነኚህም ብዙኃን ድርጅቶች እንደ ዓላማቸው የተለያዩ ናቸው። የፖለቲካ፣ የሶሻል፣ የኢኮኖሚና የፕሮፌሽን እየተባሉ ይለያሉ። የወል ስማቸው ግን የመንግሥት ድርጅት ያልሆኑ(Non Govemmental Organization - NGO) ይባላል። የየአንዳንዱ ህዝባዊ ድርጅት ጥንካሬውና ውጤታማነትም በብዙ ምክንያት የተለያየ ነው። ለምሳሌ በአባላት ቁጥር ብዛት፣ በዓላማቸው ጥራት፣ በመሪዎቻቸው ብቃት፣ በሕዝባዊ ግኑኝነት ስፋት በመሳሰሉት ይለካል።

እንግዲህ የቆሙበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስም ሆነ የአባላትን መብት ለማስጠበቅ የሚያደርጉት የአሰራር ዘዴም የተለያየ ነው። ለምሳሌ በተለያዩ ብዙኃን መገናኛዎች ስለድርጅታቸው ያስተምራሉ፣ አባላትን ያበራክታሉ፣ በህግ አውጪዎችና አስፈጻሚዎች ላይ (Legislative and Executive branches) ተጽእና (pressure) ያደርጋሉ። ዓላማቸውን ለሚረዱና ለሚደግፉ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆነ ግለሰቦች በህጉ መሠረት ዕርዳታና ድጋፍ ይሰነዝራሉ።

እዚህ ላይ ላስገነዝብ የምፈልገው፣ እነኚህ ህዝባዊ ድርጅቶች ህጋዊ ሰውነት ኖሯቸው ሊንቀሳቀሱ የሚችሉትና ከመንግሥት ተጽእና ውጪ የሚሆኑት ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ወይም ሥርዓት ባለበት ብቻ ነው። እንዲያውም የዲሞክራሲ ሥርዓት አንደኛው መለኪያ ነው ተብሎ የሚገመተው ህዝባዊ ድርጅቶች በነፃ የመቋቋምና ለቆሙበት ዓላማ በህቡዕ ሳይሆን በገሐድና በይፋ ለመንቀሳቀስ ሲችሉ ብቻ ነው። እነኚህም ድርጅቶች ከመንግሥት ተቋማት ውጪ የሆኑና ሙሉ ነፃነት ያላቸው ናቸው። የመንግሥት እጅ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በእነኚህ ድርጅቶች ውስጥ መኖር የለበትም። የመንግሥት እጅ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ካለባቸው እነኚህ ድርጅቶች የህዝብ ሳይሆኑ የመንግሥት አካል ይሆናሉ ስለዚህም የመንግሥትን ወይም የገዥውን ክፍል ጥቅም ለማስከበር የተቋቋሙ ናቸው።

ህዝባዊ ድርጅቶች ችግርና ፈተና የለባቸውም ማለት አይደለም። ለምሳሌ ያህል፦

1ኛ) ቃል የሚገቡላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ የፖለቲካ ሰዎች ቃላቸውን ላይጠብቁ ይችላሉ።

2ኛ) የዲሞክራሲ ሥርዓት በደንብ ባልሰፈነበት አገር ደግሞ እነኚህ ድርጅቶች እንደ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ይቆጠሩና ኢ-ዴሞክራሲያዊ መንግሥት በህልውናቸው ላይ ይዝታል፣ መሪዎቻቸውን ይተናኮላል፣ ደብዛቸውንም ያጠፋል።

3ኛ) ኢ-ዴሞክራሲያዊ መንግሥትም ተለጣፊ ድርጅቶችን በእጅ አዙር መስርቶ በህዝብና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ላይ ሊያላግጥ ይችላል። እንግዲህ ከቀዝቃዛው ጦርነት በኋላ ብቅ ብቅ ያሉ አዲሶቹ ዴሞክራት የተባሉት መንግሥታት የሚጫወቱት የፖለቲካ ቁማር ይኸንን ይመስላል።

ተቃውሞን ተቀብሎ፣ ወይም የህዝብን ብሶት የሚያስተናግድና ለማስተናገድም ብቃትም ሆነ ትዕግሥት

የሌለው መንግሥት የዴሞክራሲ ጠባይና የአሠራር ዘዴ ያንሰዋል። የብዙኃን ፓርቲና የብዙኃን ድርጅቶችን ጥያቄ፣ ብሎም የህዝብን ብሶት ተቀብሎ በማስተናገድና በፖሊሲ ደረጃም ተርጉም ከሥራ የማያውል ማንኛውም መንግሥት ዴሞክራሲያዊ ነው ሊባል አይችልም።

ብዙሃን ድርጅቶች የብዙሃን ልሣን፣ ዓይንና፣ ጆሮ ናቸው። ህዝብንና መንግሥትን የሚያገናኙ ድልድዮች ናቸው። እነኚህን ድልድዮች አፍርሶ ከህዝብ ጋር እገናኛለሁ የሚል መንግሥትም ጣልቃ መግባት ወይም በህዝብ ላይ አስፈላጊ ያልሆነ ጫና ማድረግ ይሆንበታል።

4ኛ) በመጨረሻም የዴሞክራሲ ባህል ባልዳበረበት ሁኔታ፣ እንዲሁ ከመንግሥት ውጪ የሆኑት አካላት ... ለምሣሌ የፖለቲካ ኃይሎች የእነኚህ የብዙኃን ድርጅቶችን ዓላማ ተቀብሎ ነፃነታቸውን ከማክበር ፈንታ እነኚህን ከፓርቲ ፖለቲካ (Partisian Politics) ሊገለሉ የሚሹትን ህዝባዊ ድርጅቶች ሊውጧቸው የመፈለግ ችግርም ይኖራል።

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ብዙኃን ድርጅቶች የቆሙለትን ዓላማ ለማስከበር ሲሆን ያንን ዓላማ የሚያስከብርላቸውን ሥርዓትና ብሎም መንግሥት እንዲኖርላቸውም በዴሞክራሲያዊ መንገድ በወልም ሆነ በግል ይለፋሉ።

## ላንዳፍታ፣

እንደነኚህ ያሉ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታወቁ ካሉ፣ ስለ እነሱ አመሠራረትና ተግባር፣ ስላመጡትም ውጤት መግለጫ ቢሰጡን?

## ዶ/ር ጌታቸው፣

ከላይ የተጠቀሱት ዓይነት ድርጅቶች፣ በአሠራርና በሥነልቦና ለአገራችን አዲስ ቢመስሉም ለየት ያሉ ህዝባዊ ድርጅቶች በታሪካችንና በባህላችን ውስጥ ነበሩ አሁንም አሉ። እንደዛሬዎቹ በአገር ደረጃ ሳይሆን ውስን በሆነ ዓላማቸውና በመልክዓ ምድር አካባቢያቸው ህዝብን በማስተባበር፣ የህዝቡን ባህላዊም ሆነ ቁሳቁሳዊ ችግር ለመፍታት ብሎም በህዝብ ስም ሹማምንትን ከመማፀንና አቤት ከማለት ያልተቆጠቡ የተለያዩ ደረጃና ጥንካሬ ያላቸው ህዝባዊ ስብስቦች ነበሩ። እንደዛሬው ግን በድርጅት መልክ ተዋቅረው የሚንቀሳቀሱ ሳይሆን ልል የሆኑና በጣም ውስን የሆነ ህዝባዊ ግልጋሎት የሚሰጡ ነበሩ።

ስለዚህ ምንም እንኳን ብዙኃን ድርጅቶች ወይም Civil Organization ሲባል አዲስ መስሎ ቢታየንም በኢትዮጵያና በጠቅላላው አፍሪካ ሥረ መሠረታዊ ድርጅቶች (grass roots organization) ነበሩ አሁንም አሉ። ነገር ግን እንዳልኩት በተለይ በፖለቲካው በኩል የተጫወቱት ሚና በጣም ውስን ነበር ምክንያቱም የሚያዳብራቸው ሥነ መንግሥት አልነበረም። ዓላማቸውም በጣም የተወሰነ ቢሆንም በአካባቢያቸው ለምሳሌ የተጣላ በማስታረቅ፣ ሌባ በመያዝ ወዘተ የተጫወቱት ሚና ነበር። በአብዛኛውም ቦታ መንግሥት ለሁሉ ጥያቄ መልስ ያለውና ሁሉን አዋቂ ተብሎ ይወሰድ ነበር። ስለዚህ መንግሥት ላይ ተጽእኖ ለማድረግ (በትንሹ አቤቱታ ከማቅረብ) በስተቀር ከዚያ ያለፈ እርምጃ የመውሰድ ባህሉም አልነበረም ይህንን የሚያስተናግድ ህግም አልነበረም። ስለዚህ እነኚህ የህዝብ ስብስቦች ከአካባቢያቸው አልፎ ሰፋ ያለ ሚና አልተጫወቱም። ባሉበት አካባቢ ግን በባህሉና በልምዱ መሰረት የማይናቅ ሚና ተጫውተዋል። አሁንም እየተጫወቱ ነው።

ከዚያ ባለፈ ግን በፖለቲካው በኩል ሹማምንት ለህዝብ እንባ ደንታ ስለሌላቸው ጨቋኝ መንግሥትና ክፉ ሹማምንትን ለመቋቋም የነበረው አማራጭ ሰጥ ለጥ ብሎ መገዛት ነበር። የኋላ ኋላም ሹማምንት ካስቸገሩ ሸፍቶ ዱር መግባት አልፎ አልፎ ይከሰት ነበር። ይህ ሁኔታ በአገራችን የተከሰተና አሁንም እየተደረገ ያለ ሁኔታ ነው።

ከሽፍትነት በመለስ ግን ህዝቡ ሸንጎ በማቋቋም ሌባ ይይዛል፣ ነፍሰ ገዳይ ለፍርድ ያቀርባል፣ እድር እያዋጣ እርስ በእርሱ የሚረዳዳበት ባህል አለው። ከዚህ ሁኔታ ላቅ ብሎ በ1960ዎቹ አካባቢ በአውራጃዎችና በጠቅላይ ግዛቶች ደረጃ የተቋቋሙ ህዝባዊ ድርጅቶች ነበሩ። ለምሳሌ የወላሞ ሶዶ መንገድ ሥራ አስተባባሪ ድርጅት፣ የሜጫ ቱለማ መረዳጃ ማኅበር፣ የጉራጌ ህብረተሰብ መንገድ ሥራ ድርጅት፣ የኢሉባቡር መረዳጃ ማኅበር እያሉ በተለይ በአዲስ አበባ ውስጥ የተመሰረቱ ድርጅቶች ነበሩ። እነኚህ ድርጅቶች ከመንግሥት ውጪ የሆኑ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ ሹማምንትና አባላት ያላቸው ነበሩ፣ ናቸውም። ዓላማቸውና ተግባራቸውም የሰሻል፣ የትምህርትና የመረዳጃ ብቻ ነው። በዚህም አኳያ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ህጉና ባህሉም በዚያን ጊዜ ስላልነበረ የፖለቲካ ተጽእኖ ከማድረግ የተቆጠቡ ነበሩ። ነገር ግን በጊዜው የነበረው ዘውዳዊ ሥርዓትና መንግሥትም ልክ እንደዛሬው የኢሕአዴግ መንግሥት የህዝብን ብሶት ለማዳመጥና ለማስተናገድ ደንታ ቢስ በመሆኑ የሜጫ ቱለማ መረዳጃ ማኅበር አቅጣጫውን ለመለወጥ ተገደደ።

በመሰረቱ ግን የመንግሥት ተፅዕኖ (influence) ባልደረሰበት ስፍራና ጠንካራ መንግሥት በሌለበት ወቅት እንደ መንግሥት ሆነው ፀጥታ የሚያስከብሩ፣ አካባቢያቸውን የሚያስተዳድሩ ህዝባዊ ድርጅቶች ናቸው። ለምሳሌ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የደርግ መንግሥት ወድቆ ኢህአዴግ ገና አዲስ አበባ በገባበት ወቅትና መንግሥት በሌለበት ሰዓት ሽማግሌዎች፣ የቀበሌ ማኅበራት ፀጥታን በማስከበር በአንዳንድ አካባቢዎች የተጫወቱት ሚና የሚናቅ አይደለም። እንዲሁም የሱማሌ መንግሥት ሲወድቅ የአገር ሽማግሌዎችና የሐይማኖት አባቶች በአስተዳደርና በፀጥታው አኳያ የተጫወቱት ሚና ነበር።

## ላንዳፍታ፣

ህዝባዊ ድርጅቶች በፖለቲካው አንፃር ምን ያህል ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ ብለው ያስባሉ?

## ዶክተር ጌታቸው፣

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ውስጥ ህዝባዊ ድርጅቶች ከፍ ያለ ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ አይካድም። ከዚህ በፊት በአገራችን የፖለቲካ ሂደት እነኚህ ድርጅቶች የተጫወቱት ሚና ግን እምብዛም አልነበረም። ምክንያቱም አንደኛ የፖለቲካ ሥርዓቱ ለእነኚህ ድርጅቶች መንሰራራትም ሆነ መፈጠር ያበረከተው አስተዋጽኦ አልነበረም። ሁለተኛ፣ በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች ታዳጊ አገሮች ውስጥ የእነኚህ ድርጅቶች በፖለቲካው መስክ የሚያደርጉት ትግል በህዝብ ዘንድ አልታወቀም ወይም

ከግንዛቤ አልገባም ነበር። ሶስተኛ፣ ባህልን ተመርኩዘው የተመሰረቱት ህዝባዊ ድርጅቶች በአገራቸው ፖለቲካ ውስጥ ያገባናል ለማለት ልምዱም አልነበረም፣ የህዝቡም ንቃተ ህሊና አልዳበረም ነበር። በመጨረሻም ለፖለቲካ ጥያቄ መልስ ሊሰጡ የሚችሉት የመንግሥት ሹማምንት ናቸው የሚል እምነት በአብዛኛው የሰፈነበት ወቅት ነበር። በኋላ ግን አንዳንድ ግለሰቦች፣ ማለትም የተማረው ክፍል፣ የፖለቲካ ትግል ሊያራምዱ የሚችሉ፣ ወይም ያለውን መንግሥት ሊቀናቀኑ የሚችሉት በሚገባ የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ናቸው የሚል እምነት ተመርኩዘው ተነሱ።

አሁን ግን ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የፖለቲካ ድርጅቶች የተፈለገውን ያህል ውጤታማ አልሆኑም፣ ህዝባዊ ድርጅቶች በመንግሥት ላይ ተገቢውን ተጽእና ሊያደርጉ ይችላሉ፣ ህዝብንም በተወሰነ ዓላማ አካባቢ ለማሰባሰብ አይሳናቸውም፤ በማለት በኢትዮጵያና በሌሎች ታዳጊ አገሮች ህዝባዊ ድርጅቶች መቋቋም ጀምረዋል። ስለዚህ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጪ የሚደራጁ ህዝባዊ ድርጅቶች መቋቋምና በፖለቲካው መስክ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ ከዚህ ሂደት አንፃር መታየት አለበት፡

## ላንዳፍታ፣

የፖለቲካ ትግል ሁልጊዜ "Partisan" ማለትም በፓርቲ ብቻ መመራት አለበት ማለት ነው? በፓርቲ አመራር የሚደረግ የፖለቲካ እንቅስቃሴና በሲቪክ ድርጅቶች የሚደረግ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ልዩነት፤ በአመሰራረት፣ በተግባርና ሊያመጣ በሚችለው ውጤት ምን እንደሆነ ቢያብራሩልን?

## ዶ/ር ጌታቸው፣

የፖለቲካ ትግል ሁልጊዜ በፓርቲ ላይ ብቻ መመስረት የለበትም። ሌሎች ለምሳሌ የብዙኃን ድርጅቶች የፖለቲካ ጥያቄዎችን እያነሱ ለሚመለከታቸው የመንግሥት ድርጅቶች ወይም ዘርፎች ላይ ተጽዕና ሊያደርጉ ይችላሉ። የሃይማኖት አባቶችም እንዲሁ ለህዝብ እኩልነት የሚናገሩና ፀረ ዴሞክራሲን መንግሥት የሚኮንኑ እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል። በደቡብ አሜሪካ ያሉት የአርነት ትምህርት (Liberation Theology) ተከታዮች ለደሀው ሽንጣቸውን ገትረው የሚሟገቱ ናቸው። ስለዚህ ለፍትህ፣ ለእኩልነትና ለወንድማማችነት ማንኛውም ይመለከተኛል የሚል ድርጅት ሐሳቡን መሰንዘርና መተግበር ይጠበቅበታል ማለት ነው። ማንም ከፖለቲካው ጥያቄ ሊያመልጥ አይችልም። መኖርና አለመኖርም የፖለቲካ ጥያቄ ነው።

በፖለቲካ ፓርቲዎችና በብዙኃን ድርጅቶች መሐከል አንዳንድ የሃሣብና የአሰራር ዘዴዎች ልዩነት ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስ በሁለቱ መሐከል ያለው ዋናው ልዩነት የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገሩ ህገ መንግሥት መሠረት በምርጫ ተወዳድረው የህዝቡን አመኔታ በማትረፍ ምርጫውን በማሸነፍ መንግሥት ተረክቦ አገር ለማስተዳደር ነው። ምርጫው ያልቀናው የፖለቲካ ፓርቲ(ዎች) ደግሞ ከገዢው ፓርቲ ለየት ያለ አማራጭ ፖሊሲና ፕሮግራም በመንደፍ አባላትን በማባዛት ፕሮግራማቸውን በማሳመን ለሚመጣው የምርጫ ዘመን መዘጋጀት ነው።

ብዙሃን ድርጅቶች ግን የሚቆሙበትን ዓላማ ለማስከበር ከመንግሥት መዋቅር ወይም ተጽእና ነፃ ሆነው ሁልጊዜ የሚለፉ ናቸው። ስለሆነም የዓላማቸው ተባባሪ የሆኑትን ሁሉ ይረዳሉ፣ ይደግፋሉም። የብዙኃን ድርጅቶች ከፖለቲካ ፓርቲዎች በጣም የተለየና የላቀ ሚና ይጫወታሉ። ድምፅ ላጣው ድምፅ በመሆን፣ ስለመብቱ ለመከራከርም ሆነ ለማስጠበቅ፣ ጉልበት ላነሰው ሽንጣቸውን ገትረው የሚከራከሩ ናቸው። የፖለቲካ ፓርቲዎች የህዝብን ድምፅ ለማግኘትና መንግሥት ለመጨበጥ ብቻ የሚያወላውሉ ናቸው በማለት ሲተቹ እውነተኞቹ የብዙኃን ድርጅቶች ግን ለቆሙበት ዓላማ በህዝብ ሸንጐም ሆነ በፍርድ ቤት ከመከራከር አይቆጠቡም። ለምሳሌ የሴቶች፣ የሙያተኞችና የሰብዓዊ መብት አስከባሪ ድርጅቶች ለቆሙበት ዓላማና ለቆሙለት ወገን መብት ለማስከበር አልበገሬ ናቸው። ስለዚህም ኢዴሞክራሲያዊ ለሆኑ መንግሥታት ሁሉ የጐን እሾህ በመሆን የሚያስጨንቋቸው ስለሆኑ እነኚህንና እነኚህን የመሳሰሉትን ብዙኃን ድርጅቶችን ለማጥፋት፣ ለማሰናከል፣ ስማቸውንና ድርጊታቸውን ለማጉደፍም ሆነ፣ ብሎም በእጅ አዙር ተለጣፊ ድርጅቶችን ከማቋቋም አይመለሱም። ስለዚህ ሐቀኞቹ ብዙኃን ድርጅቶች የህዝብን እርዳታና ድጋፍ ማግኘት ለድርጅታዊ ህይወታቸውም ሆነ ለቅዱስ ተግባራቸው ዋስትና ይሰጣቸዋል።

## ላንዳፍታ፣

በውጭ አገር ባሉ ኢትዮጵያውያን ሊቋቋሙ የሚችሉ የብዙሃን ድርጅቶች ምን መልክ ቢኖራቸውና በምንም መልክ ቢቋቋሙ፣ በምን ሁኔታ ቢሰሩ አገር ውስጥ ላለው የፖለቲካ፣ የሶሻልና ኤኮኖሚ ችግር አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ?

## ዶ/ር ጌታቸው፣

በውጭ አገር ባሉ ኢትዮጵያውያን ሊቋቋሙ የሚችሉ የብዙሃን ድርጅቶች በመጀመሪያ ደረጃ ዓላማቸውን በደንብ ካስቀመጡ፣ የድርጅታቸውን መዋቅር ከዘረጉና፣ መተዳደሪያ ደንባቸውን ከቀረፁ በኋላ በአገሩ ደንብ ህጋዊ ሰውነት ማግኘት አለባቸው። ከዚያም አባላትን ማሰባሰብና ለሚመለከተው የመንግሥት አቋማትና ሹማምንት ስለአገራቸው ሁኔታ በጽሁፍም ሆነ በቃል ማስረዳት ነው። ለምሳሌ በአሜሪካ ኮንግሬስ ውስጥ ለሚመለከተው ህግ አውጪ ንዑስ ኮሚቴ ፊት በመቅረብ የምስክርነት (testify) ቃል መስጠት ነው። በህግ አስፈጻሚው አካልም ለምሳሌ ስቴት ዲፓርትሜንት የአፍሪካ ክፍል ላይ ተጽዕኖ ማድረግ ነው። በተጨማሪም የመሰል ድርጅቶችንና የህዝብንም ድጋፍ መሻትና ማግኘት፣ ህዝባዊ ግኑኝነት (Public relations) ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይህንንም ሁኔታ በደንብ ለመተግበር በቂ ገንዘብ ካለ ደጅ ጠኚዎች (lobbyist) መቅጠሩ አይነተኛ የአሠራር ዘዴ ነው።

ከዚህም በተጨማሪና በተለይም አገር ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ መሠል ድርጅቶች ጋር በቅርብ መስራት፣ ሃሳብ መለዋወጥና ተግባርን ማቀናጀቱ በጣም አስፈላጊ ነው። በየአህጉራቱ ካሉት ድርጅቶችና ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ጋር መተባበርና የሥራ ግኑኝነት ማድረግም

ያሻል።

እነኚህ የሥራ አውታሮች ከተዘረጉ በኋላ በውጪ የሚቋቋሙት ብዙሃን ድርጅቶች አሠራራቸው በግብታዊነት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በጥናት፣ በምርምርና በተጨባጭ ሁኔታ ላይ መመስረቱ አመኔታን (credibility) ያስገኛል፣ ያስከብራልም። የሚወጡትም መግለጫዎችም ሆኑ አስተያየቶች ሚዛናዊ፣ ብሩህ የሆኑና ከእውነት የራቁ መሆን የለባቸውም። በዚህ አይነት ዘዴ ከሰሩ አገር ውስጥ ላለው የፖለቲካ፣ የሶሻልና የኢኮኖሚ ችግሮች መፍትሔ ሊሹና የማይናቅ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ።

**ላንዳፍታ፣**

በእነኚህ ድርጅቶችና በአሁኑ ጊዜ ባሉ ተቃዋሚ ኃይሎች (ፓርቲዎች) ሊኖር የሚችለው ግኑኝነት ምን መልክ ሊኖረው ይገባል?

**ዶ/ር ጌታቸው፣**

በእነኚህ ድርጅቶችና በተቃዋሚ ኃይሎች (ፓርቲዎች) መካከል ያለው ግኑኝነት የመከባበርና በሚያስተባብራቸው ነጥቦች ላይ አብሮ መሥራት ነው።

በመሠረቱ ብዙኃን ድርጅቶች የሚቃወሙት መንግሥትን ሳይሆን የመንግሥትን ፖሊሲና የአሠራር ሁኔታዎችን ነው። የዛሬ ተቃዋሚዎች ነገ መንግሥት ቢመሰርቱና ህገ ወጥ ሥራ ቢሰሩ በተለይም ህዝባዊ ድርጅቶች የቆሙበትን ዓላማ የሚጻረሩ ከሆኑ በአዲሶቹ ሹማምንትና መንግሥት ላይም ምግባራቸውን ከመኰነን አይመለሱም። ስለዚህ በአጭሩ ገዢዎች ይመጣሉ ይሄዳሉ፣ ህዝባዊ ድርጅቶችና ዓላማቸው ግን ቋሚ ነው።

ይህ መሠረታዊ የሆነ የህዝባዊ ድርጅቶች የአሰራር ዘዴአቸው ሆኖ ሳለ፣ በሚስማሙበት ነጥቦችና ከዓላማቸው ጋር ከፉኛ ከማይጋጩ ድርጅቶች ጋር አብሮ ከመሥራት የሚያግታቸው ምክንያት የለም።

ለምሳሌ የሰብአዊ መብት አስጠባቂ ድርጅት የጊዜው መንግሥት (government of the day) በተቃዋሚ ግለሰቦችና ድርጅቶች ላይ የሚያደርገውን ኢሰብአዊ ተግባር ይቃወማል። ነገ ደግሞ እነኚህ የዛሬዎቹ መሪዎች በኃይል ተገልብጠው ከርቸሌ ቢወርዱ፤ የእነኚህን የአዲሶቹን እስረኞች ሰብዓዊ መብት እንዲጠበቅ ከማድረግ ሰብዓዊ ድርጅቶች አይቆጠቡም። ስለዚህ ነው ብዙኃን ድርጅቶች ከፓርቲ ፓለቲካ ልቀው ይሰራሉ፣ የሞራል በላይነት አላቸው የምንለው። ይህ ሐቅ የሚሆነውም በተለይ በአሁን ጊዜ በብዙ አገሮች የመንግሥታት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና መሪዎች፣ ጥራት፣ ብቃትና፣ ዴሞክራሲያዊነት አጠያያቂ በሆነበት ሰዓት ነው። ሁሉም በቂም በቀል ልግዛ ሲል ተው አይሆንም የሚል ህዝባዊ ድርጅት መኖር አለበት።

አምባገነን ሥርዓት ሰፍኖ፣ የአገር ህልውና አጠያያቂ በሆነበትና ዴሞክራሲ በጠፋበት አገር፣ ህዝባዊ ድርጅቶችና የፖለቲካ ፓርቲዎች ጠንካራ ግንባር ፈጥረው አገርን ከማዳን የሚቆጠቡበት ምክንያት አይታየኝም። ይህም ሁኔታ በቅርቡ በናይጄሪያ የተወሰደውን የተቃዋሚ ድርጅቶችና የብዙሃን ድርጅቶች እርምጃ ያሳስበናል። ይኸውም ከ30 የበለጡ የናይጄሪያ ተቃዋሚ ድርጅቶችና ህዝባዊ ድርጅቶች ለምሳሌ፣ የሰብዓዊ ድርጅቶች፣ የሞያ ማኅበራትና የተማሪዎች ድርጅቶች ሆነው የአሁኑ የናይጄሪያ አምባገነን መሪ ጄኔራል ሳኒ አባቻ በሚመጣው ምርጫ ላይ እንዳይመረጡ ለመታገል አዲስ ድርጅት፣ ማለትም ለዴሞክራሲ የተባበረ ኃይል (United Action for Democracy) የሚባል ፈጥረዋል። ስለዚህ ህዝባዊ ድርጅቶች ይህንን የመሰለ የላቀ (serious) የፖለቲካ እርምጃ የሚወስዱት ኢ-ዴሞክራሲያዊ የሆኑ መሪዎች ለሚያደርጉት እርምጃ መልስ ነው። ቁምነገሩ ግን በአጭሩ ናይጄሪያ ውስጥ ሁለት የፖለቲካ ፓርቲዎች በመንግሥት የተቋቋሙ አሉ። ተቃዋሚ ፓርቲዎችም እንዲሁ አለን ብለው ብቅ ብቅ ብለዋል። ሁሉም ግን ለምርጫ የምናቀርበው ጄኔራል ሳኒ አባቻን ነው ይላሉ። ከቀዝቃዛው ጦርነት በኋላ ብቅ ብቅ ያሉት መንግሥታትና የብዙኃን ፓርቲ (multi party) ድርጅቶች መሪዎች ተለጣፊ ድርጅቶች የመፍጠርና የጣልቃ መግባት ቁማር ይጫወታሉ። ይህ ሁኔታ በግብርም ሆነ በዓላማ የዲሞክራሲ ሂደት ነው ሊባል አይቻልም።

ስለዚህም በጠቅላላው ህዝብ በመሪዎች ላይ እምነት ሲያጣ፣ ህዝብ እንደጅል ሲቆጠር፣ በዘርና በሃይማኖት ሲከፋፈል ያሳዝናል። በዚህን ወቅት ህዝባዊ ድርጅቶች ቁልጭ ያለ ትምህርት መስጠትና በህዝብ የሚያላግጡትን ዘረኛና አድሉአዊ የዘመኑን መሪዎችን ከቅርብም ከሩቅም ሆኖ ማጋለጥና መታገል ይኖርባቸዋል።

**ላንዳፍታ፣**

በመጨረሻ የሚሰጡን አስተያየትና መደምደሚያ ካለ።

**ዶ/ር ጌታቸው፣**

መልሴን በአጭሩ ለመቋጨት ያህል ጥቂት አጠቃላይ ነጥቦችን ልሰንዝር፣

1) በአጠቃላይ መንግሥታት፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና መሪዎች በህዝብ ፊት አመኔታን እያጡ ሄደዋል። ይህም በአገራችን ብቻ ሳይሆን በብዙ አገሮች የተከሰተ ሁኔታ ነው። ስለዚህ የህዝብን መብት ከመንግሥት ውጪ ሆነው የሚያስተምሩና የሚያስከብሩ ብዙሃን ድርጅቶች አስፈላጊነታቸው ከምንጊዜውም የበለጠ ሆኗል።

2) የፖለቲካ ድርጅቶች በዙሪያቸው ህዝብን የማሰባሰብ አቅማቸው በየምክንያቱ ተዳክሟል። የፖለቲካ ፓርቲዎች ዋነኛው ተግባራቸው አባላትን ማበራከት ነው። ይህን ግን ሲያደርጉና ህዝብ ሲያቅፋቸውና ህዝብን ሲያቅፉ አልታዩም። ስለዚህ ብዙኃን ድርጅቶች ህዝብን የሚያሰባስብ ራዕይ (Vision) እያቀረቡ በዚያ አካባቢ ህዝቡን ስለመብቱና ግዴታው ማስተማርና ማካተት ይጠበቅባቸዋል። ይህንንም የማስተማርና ንቃተ ልቦና የመስጠት ድርጊት የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊሰጡ አልቻሉም ወይም ተስኗቸዋል። ስለዚህ በልዩ ልዩ ምክንያት የተፈጠረውን የፖለቲካ ቀዳዳ (Vaccum) የሚሞሉ የብዙሃን ድርጅቶች መፈጠርና መበራከት አለባቸው። ይህ ካልሆነ ኢ-ዴሞክራሲያዊ መንግሥታት ህዝብን እንዳፈቀዳቸው ሲያተራምሱት ይኖራሉ ማለት ነው። ይህ ከቀጠለ የአገር እድገት አይኖርም። አገር የሚባልም ይጠፋና የጥቂቶች የግል ሀብት ትሆናለች ማለት ነው። የኢትዮጵያም ሁኔታ ከዚህ አኳያ መታየት ያለበት ነው።

3) የብዙኃን ድርጅቶች መበራከትና በጉዳዩ መንግሥት አሰራርና ፖሊሲ ላይ ጥያቄ ማቅረብ፣ መንግሥታትንም ከኢ-ዴሞክራሲ ስራቸው እንዲቆጠቡ ማድረግ በአሁኑ ጊዜ የብዙሃን ድርጅቶች ተፈላጊነትን አስመስክሯል።

ስለዚህም ነው ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ብዙኃን ድርጅቶች በየአገሩ በብዛት የተመሰረቱት።

4) በመጨረሻም ሁላችንንም ሊያሳስብ የሚያስፈልገው እነኚህ የብዙኃን ድርጅቶች በህዝብ ስም የሚነግዱና የጥቂት ክፍሎችን ጥቅም ብቻ ለማስከበር የተደራጁ መሆን የለባቸውም። እንዲሁም የመንግሥት ተለጣፊ ወይም የሹማምንት ተገዢዎች እንዳይሆኑ ይጠበቅባቸዋል። ይህ ከሆነ በተለይ በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ለተከሰተው የፖለቲካ ችግር መፍትሔ ከመሆን ፈንታ ራሳቸው የፖለቲካ ችግር አመንጪ እንዳይሆኑ ህዝቡ በንቃት መጠባበቅ አለበት። በህዝብ ስም መነገድ ኪሣራ (Deficit) ፖለቲካ ነው።

በመጨረሻም አንዳንድ ግንዛቤዎችን እንድሰነዝር ይፈቀድልኝ።

በህዝብ የተነሱ የፖለቲካ ጥያቄዎች በሚገባ ከመንግሥት መልስ ካላገኙ ኢትዮጵያ ውስጥ ዘለቄታ ያለው እድገትና የኤኮኖሚ ግንባታ ሊኖር አይችልም። መንግሥትና ህዝብ በአንድ አገር ውስጥ ተለያይተው ሊኖሩ አይችሉም። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ ግን ይህ ነው። ይህም ሁኔታ ከቀጠለ ኢትዮጵያ ወደ ኋላ የምትቀረው በኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን በሌሎች በተቆራኙ ሁኔታዎች ... ለምሳሌ፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በሰው ኃይል ግንባታ በመሳሰሉትም ጭምር ነው። የህዝቡም ሞራልና ለስራ ያለው ትጉህነትና ታታሪነትም ይዳሽቃል። በአጠቃላይ አገር ቀስ በቀስ ከእድገት ጉዳና ወደ ኋላ ትቀራለች ማለት ነው።

ባለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ የተከሰተው ሁኔታ ይህ ሆኖ ሳለ አሁን የፖለቲካና የህዝብ ድርጅቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ሌሎቹም ለአገር ተቆርቋሪ ግለሰቦች አገር አቀፍ አጀንዳ አውጥተው አገርን ከጥፋት፣ ህዝብንም ከስቃይ ማዳን ያለብን ጊዜ አሁን ነው። ለዚህም የህዝብ መብት ለማስጠበቅ የተደራጁና የሚደራጁም ህዝባዊ ድርጅቶች አስፈላጊነታቸው አሁን በበለጠ ጉልቶ ይታያል። በተናጠል ለሚባዝኑ ለፖለቲካ ድጅቶችም አመቺ ሁኔታ መስርተው ሊያሰባስቡና ብሎም ለኢትዮጵያ ህዝብ አማራጭ የፖለቲካ ስርአት ሊፈጥሩ ይችላሉ። እነኚህ ህዝባዊ ድርጅቶች አመሰራረታቸውና አሰራራቸው አጠያያቂ እስካልሆነ ድረስ በህዝብም፣ በፖለቲካ ድርጅቶችም በኩል ተቀባይነት ሊኖራቸው ይችላል። እንግዲህ ተቀባይነትን ካገኙና ለስልጣን አለመሮጣቸው ከታወቀ፣ ለፖለቲካው ትግል ስልትና ስርዓት ሊቀይሱና በዚያ አካባቢ ድርጅቶችንና ህዝቡን ሊያሰባስቡ ይችላሉ። ይህንንም ስል በየጊዜው የሚፈጠሩትን የፖለቲካ ግንባር ወይም ቅንጅቶችን ሚና መናቄ አይደለም። ሁሉም አስፈላጊ ናቸው ወደ አንድ አቅጣጫ እስካመሩ ድረስ። አሁን የሁሉም ችግር የፖለቲካ ጨዋታ፣ ስልትና ህግ በአግባቡ ተተርጉሞ የግብ መድረሻው አቅጣጫና ራዕይ የታወቀ አልመሰለኝም። ይህም ስለሆነ ነው የፖለቲካ ድርጅቶች በየአቅጣጫው የሚባዝኑትና ወርቃዊ ጊዜንና ንብረትን የሚያባክኑት። በተለይ የህዝብ ተሳትፎ እንዲከስምና ከፖለቲካው ትግል እንዲገለል አስተዋጽኦ አድርገዋል። ለዚህ ተጠያቂው ማን ይሆን? መፍትሔውስ ምን ይሆን? የፖለቲካው ትግል እምርታ እንዲያገኝ ወደ ተቀናጀና ወደተባበረ ስርአት እንዴትና በምን ዓይነት ለመሸጋገር ይቻላል? እነኚህ ጥያቄዎችና ሌሎችም ተመሳሳይ ጥያቄዎች መልስ የሚያሻቸው የወቅቱ ትኩረት መሆን አለበት።

ዶክተር ጌታቸው መታፈሪያ የሞርጋን ስቴት ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ ፕሮፌሰር ናቸው።

# አርቲስት አስቴር አወቀ ከኢትዮጵያ ጉዞዋ ተመለሰች።

ታዋቂዋ አርቲስት አስቴር አወቀ ለረዥም ጊዜ ከተለየችበት አገሯ ኢትዮጵያ ሄዳ መመለሷ የሚታወቅ ነው። የአስቴርን የአገር ቤት አካሄዷንና ትርዒቶቿን በተመለከተ የተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች የተለያየ አስተያየቶች ሰጥተዋል። የአስቴር አወቀን አገር ወዳድነት በብዙ መድረኮች ያየንና ሁላችንም የምንመሰክረው ሆኖ ሳለ ይህ ውዝግብ እንዴት ሊነሳ እንደቻለ አጠያያቂ ሆኗል።

አገር ቤት እያለች የሰጠችውን ጋዜጣዊ መግለጫ ተንተርሰን እዚህ ከመጣች በኋላ ስለ አገር ቤት ጉዞዋና ስለተነሱት አንዳንድ ጉዳዮች ለምናቀርብላት ጥያቄ የምትሰጠንን መልስ በሚቀጥለው እትም ላይ የምናቀርብ መሆኑን ለአንባቢዎቻችን እንገልፃለን።



"በምወደው ገብሬል እምላለሁ፤ እኔ ዘፋኝ ብቻ ነኝ! ዘፋኝ ብቻ ነኝ! . . ."

"የአገሬን ሕዝብ እወዳለሁ፤ ካለአገሬ ሕዝብ ምንም የለኝም፤..."

(አስቴር አዲስ አበባ ከሰጠችው ጋዜጣዊ መግለጫ የተወሰደ)

**እርማት**

ባለፈው የሚያዝያ/ግንቦት 1989 እትም በገፅ 42 ላይ ስለ ኢትዮጵያ ቋንቋና ጽሁፍ <u>በአቶ ሰይፉ መኩሪያ</u> የሚለው በስህተት ስለሆነ <u>በአቶ ሰይፉ መታፈሪያ</u> ተብሎ እንዲነበብ ከይቅርታ ጋር እንጠይቃለን።

# አጭር ልቦለድ ታሪክ

## ያዳፈኑት እሳት

ከተምሳሊት ጨዋታ የተዘረፈ
በሰይፉ ኣዳነች ብሻው
(መ) መብቱ የተጠበቀ ፲፱፻፹፰/፹፱ ዓመት
SAFEU © Copyrighted 1986/97

ለፌይ ማስታወሻ
ወቅቱ – በዓለም ድንጋይ ዘመን
ቦታው – አቅሱም የባህር ዳርቻ

ይህ ልብወለድ ፅሁፍ በ፲፱፻፹፰ ዓመት ላይ በአትላንታ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በተምሳሊት ጨዋታ ቀርቦ የነበረ ነው።

ተራኪው አዛውንት አቶ አዙማንትራ ወጣት አድማጮቻቸውን አዘጋጅተዋል፤ ለዛሬው ታሪካቸው። ባለፈው ሌሊት ትረካቸውን ሲጨርሱ ያነደዱትን እሳት ከማጥፋት እንዲያዳፍኑት ልጆቹን አዝዘዋቸው ነበር። *‹ዛሬ የምተርክላችሁ ታሪክ ‹የተዳፈነ እሳት› የተሰኘ ነው። ስለዚህ ይህንን አዳፍነን ያሳደርነውን እሳት እስቲ እንፈትነው።»* ብለው በበትራቸው አመዱን ገለጥ ገለጥ አደረጉት። በውስጡ ታምቆ ያደረው እሳት ሙቀቱን መትንፈስ ጀመረ። *«ያዳፈኑት እሳት አይጠፋም። ሲገለጥ ማቃጠሉን ይቀጥላል። የሚነድ ካገኘ ደግሞ ወደ ነበልባልነትና ሰደድነት ይለወጣል።»* አሉ። በግምት ወደ መቶ አስራ–አስር ዘመን ይሆናቸዋል። ከወጣቶቹ አንዱ ማተጎ *«በውሃ አጥፍተነው ቢሆን ጠፍቶ ይቀር ነበር።»* አላቸው። *‹ብእርግጥ እሳቱ ጠፍቶ ይቀር ነበር። አመዱስ? እሳት ነድዶ እንደነበር ፍንጩ አይጠፋም፤ ማስረጃው ባይገኝ። ዐይንን አውጥተው ቢጥሉት ጉድጓዱ ይጠፋል? ክርክሩን በዚህ ከቀጠልን ታሪኩን ሌላ ጊዜ ማድረግ ይኖርብናል»* አሏቸው። አጠገቡ የተቀመጠው ወጣት ማተጎን ሌላ ጥያቄ እንዳያመጣ ጎንተል አደረገው። ሁሉም በአንድነት ትረካቸውን ለመስማት መጓጓታቸውን አሰሙ። አቶ አዙማንትራም ፈገግ ብለው ትረካቸውን ጀመሩ።

* * *

ኮከብ ቆጣሪው፣ ፈላስፋውና የጤና መኮንኑ ዕለታዊ ተግባሩን ከሚያካሂድበት ሠገነት ላይ ይገኛል። ወርቃዊ የቀለም ቢልቃጡ ውስጥ በህብረ ቀለም የተዋበ የወፍ ላባውን ማፍ ጠቀስ አድርጎ ከተለጠለጠ የእህል ዘር ተጠፍጥፎ እንደነጠላ ከተዘረጋው የታሪክ መዝገቡ ላይ የጥናቱን ውጤት ይመዘግባል። በጎዋ ውስጥ ተሰግስገው ከተቀመጡት በየጊዜው እያወቃቸው ከሄዱት አዳዲስ ዓለማት ጋር የሰበትን ኃይል አሸንፎ የሚደርስበትን የጠፈር መንኮራኩር በገፁ አካፋይ ላይ በመንደፍ ሃሳብ ክፉኛ ተውጧል። ድቅድቅ ጨለማውን ዘልቀው ሊሰሙት ከንፈራቸውን አሹለው በዐይኖቻቸው የሚጠቅሱት ጓደኞቹ ፍቅር ይበልጥ እያደገ ከመጣ ዘመኑ ብዙ ነበር። ይቻላል! ሲል አመነ። ምድርን እንደ አሞራ ለቅቆ እንደሚብለጨለጩት ከዋክብት ብርሃን ተጉዞ የድንጋይ ቋጥኞችን መጎብኘት ይቻላል።

በውሃ ልክ የተሠራውን እንክብል መስተዋቱን አቅጣጫና ከፍታ የእጅ መዘውሩን በማንቀሳቀስ ዘወር አደረገው። ከፍተኛ ብርሃን ከውሃ መስተዋቱ ላይ እንደ ጠብታ ጀምሮ ቀለበቱን እያሰፋ እየቀረበ ሲመጣ ተመለከተ። ዓለማት በተፈጥሮ ትዕዛዝ ውጊያ አድርገው የተጎዳው ክፍል መድረሻ አጥቶ እየተቅነዘነዘ ማረፊያ አድርጎ ወደ አለመው የመሬት ክፍል ሲጓዝ የፈጠረው የእሳት ነበልባል ሳይቀር ጎልቶ ታየው። ምፅዐት ታሰበው። ክፉ ነገር እየቀረበ መሆኑ ተሰማው። ዓላማውን ካሰበው ሳያደርስ የሚያሰናክልበት መዓት እንዳተኮረበት ሰውነቱ ነገረው። ሰላማዊው ምኞቱና ህልሙ ከማይረበሽበት ፀጥ ካለው ሠገነት መጥቶ ሲያተራምስበት ታወቀው። ለዚህም ነው ልዕልቲቷ በድንገት ስትመጣበት ልቡ ሊቆም የደረሰው።

«ማማሽ አካሌ የት ነው ያለችው? ይንገሩኝ? ልዕልቲቷ የንግሥቲቷ እናቴን ማኅፀን ከእኔ ጋር የተካፈለችው? በሕይወት አለች ወይስ ሞታለች?»

ጠቢቡ በድንገተኛ ጥያቄው ተሸብሯል። ሆኖም ራሱንና አስተሳሰቡን አሰባስቦ በረጋ መንፈስ «ሌላ አካል የለሽም፤ የተከበርሽ ልዕልት ሆይ! ለንጉሡና ለንግሥቲቱ አንድ አንቺው ብቻ ነሽ። ተጋሪ አልነበረሽም፤ የለሽምም።»

«ችሎታዎትንና ኃይልዎን በመጠቀም ካለችበት ይንገሩኝ። ካለችበት ይምሩኝ፤ የሚያቆመኝ የለም ልፈልጋት እሄዳለሁ። ይህችን ገነታዊ ጣፋጭ ምድረ—ሕይወት ላካፍላት እፈልጋለሁ።»

«ያለችበትን ለማወቅ ጥበብ አይጠይቅም። ምስክርነት ብቻ ነው የሚያስፈልገው። ለዚህም ምስክርነት እኔ ብቻ ሳልሆን ማንንም መጠየቅና ፍፁም እህት እንዳልነበረሽ መረዳት ትችያለሽ።» አላት ጠቢቡ። ይህን ሃሳብ ከየትና እንዴት እንዳገኘች ለማወቅ እያሰበ።

«ከእርስዎ ችሎታ የሚበልጠውን መንፈሴን እየሰደቡት ነው?» በቁጣ ነበር የተናገረችው።

«የተከበርሽ ልዕልት...» ሊናገር ጊዜ አልሰጠችውም። በጨዋ ባህርዩ ይቅርታ ሊጠይቃት እንዳሰበ ተረዳች። «የለም ሊቀ ጠበብት፣ ይቅርታውን እኔ ልጠይቅዎ።» ነገሩን በመገልበጥ ራሷ ይቅርታ በመጠየቅ «ህልሜን አጨልመው ከውርደት ጋር ስላከናነቡኝ አስቀድሜ ይቅር ብዬዎታለሁ።»

«ውርደት አድርገሽ የወሰድሽው ምኑን ነው፤ የተከበርሽ ልዕልት?»

«ለጥያቄዬ በቂ መልስ መነፈጌን። እንዲሁም ከጠቢብ የሚጠበቅ ባኅርይ አልታየኝም። ያበሳጨኛል።»

አባባሏ ትዛታ አመጣበት። ወደ ኋላው የዕድሜ ጉዞውን በቅፅበት ተጉዞ እናቷን አስታወሰ፤ ንግሥቲቱን። ውበትና ግርማዋ ከልዩ የዕፅዋት ቅጠል እየተመዘዘ በተሰሩ ውብና ልስልስ ልብሶች ተውባ ታየችው። «አንቺም እንደእናትሽ!» ሲል ለራሱ ያህል ተናገረ። በመስማቱ ግን አልተደሰተም።

«ምን አሉ!?» ስትል አጥብቃ ጠየቀችው።

«የተከበሩት ንጉሣችንን ዛሬ ጎብኝተሻቸው ነበር? የቀመምኩላቸውን መድኃኒት በወቅቱ ወስደዋል?» ሲል ነገር ለመቀየር ጠየቃት።

«ደመኛዬ ሆነዋል። ራስዎትን ሳይስቱ አልቀሩም። ይህን ያውቃሉ? ስለ ንጉሤ እንደሆነ ፍቱን መድኃኒት እንድትቀምሙላቸው እፈልጋለሁ።»

ጠቢቡ የልዕልቲቱን ሃሳብ ወዲያውኑ ተገነዝበው። የክፉ አስተሳሰቧ ተሳታፊ እንዲሆንላት ማሰቧ ሰቀጠጠው። «ምነው? እንዴት እንደዚህ?» ሲል በመገረም ጠየቃት።

«አንቋ አልገድለው ወይን በስለት አልገላግለው። ዕድሜዎን በማርዘም ተድላና ደስታን ከፈለጉ መንገድ መፈለግ አለብዎት። ይኼ ደግሞ ለነፍስ የሚነገር አይደለም። ማናችንንም ሳያጋልጥ መፈፀም ያለበት ነው።» ትዕዛዝ ነበር በስተመጨረሻ ላይ የሰነዘረችው። አንዱን ዘብ በመላክ ጥናቱን ከሚያደርግበት ሠገነት ላይ እንደ ዕብድ ወርውሮ ሊጥለው እንደሚችል ያውቃል። ቢሆንም ዕድሜውን ሙሉ ታማኝ ሆኖ ትኩረት የሰጠበት ጥበብንና ምርምርን ነበር። የመንገሥ ፍላጎት ቢኖረው ከረጅም ጊዜ በፊት ያደርገው ነበር። ነገር ግን የአመራር ሰው ሳይሆን የቅመማና የምርምር ሰው ነበር።

«ፍፁም አላደርገውም! ጊዜው አሁን አይደለም። በጣም ዘግይቷል።» ሲል እንቢተኛነቱን አሰማ።

«ምን ማለትዎ ነው ዘግይቷል ሲሉ?»

«ፍላጎቱ ኖሮኝ ቢሆን ኖሮ ከረጅም ጊዜ በፊት አደርገው ነበር። ወጣትና ጠንካራ የነበሩ ጊዜ። አሁን ከሞት አፋፍ ላይ ነው ያሉት። ነፍሱን የሞት አማልክት ወደ ልዩ ዓለማቸው ሊወስዷቸው ጉዟቸውን እያቀረቡ ናቸው።» ሲል ወደ ሰማይ አንጋጠጠ።

«ከገደልኩዎት በኋላ እራሴው ላደርገው የማልችለው እንዳይመስልዎት።» በማለት ከቆመችበት ተስፈንጥራ በስለት መፍትሄ ልትፈጥርለት ስትሳብ ልዑሉ በድንገት ይደርሳል።

«የእኔ ልዕልት!» ልዑሉ ነበር የተናገረው።

«ምንጊዜም ካለፈው ትምህርት እናገኛለን።» አለችው ለጠቢቡ ወደ ልዑሉ ከመዞሯ በፊት። «የንጉሡ ጤንነት እንዴት ነው ዛሬ?» ስትል ጠየቀችው፤ በውስጧ የነበረውን ብሽቀት በመደበቅ።

«ስምሽ ካፉ አይለይም። ስለፍቅርሽና መልካምነትሽ ምረቃው እልባት የለውም። በሕይወት ያለው ባንቺ ስም ነው።» ቀርቧት ሁለት እጆቿን ጨብጦ በመያዝ። በእሷና በአባቷ መሀከል ባለው ፍቅር በመቅናት ዐይኖቿን ተመለከታቸው። የውሸት ፈገግታዋን አሳይታው ወደ ጠቢቡ ዞር በማለት በማስጠንቀቂያ አስተያየት ተለየችው።

«ስለ እሱው ጤንነትና ታሪክ ነበር ስንወያይ የነበርነው። ዛሬ ምን የማደርግልህ ነገር አለ? የእኔ ልዑል።»

«ንጉሡ ከፉኛ ታሟል። ዕድሜው እያጠረ ነው።» ሲል ልዑሉ በሃዘንና በሃሳብ ተናገረ።

«ዓለማትን በተለያየ ዑደት ውስጥ አንቀሳቅሶና ወቅትን አፈራርቆ የሕይወትን ርዝመትና እጥረት የሚለካ ኃይል ጋር እየተጋገዝን በተፈላጊው ሂደት ውስጥ ከመጓዝ ወደ ኋላ አንልም።»

«ካለማት ጋር የሕይወትን ሂደት እየለኩ መጪና አላፊውን አስቀድመው ያውቃሉ።» እስከ አሁን ድረስ ያላስተዋለውን ከጠርሙስ በተሰራ በርሜል ላይ ተቀምጦ የሚዋዥቀውን ሉል ይመለከታል። «ይህ ደግሞ ምንድነው?» ሲል በመገረም ይጠይቃል። ከሠገነቱ ላይ ከወጣ አንድ ሺህ አርባ አዲስ ጨረቃ የፍቅር ጉዞዋን ከምድር ጋር አስተካክላ ተጉዛለች። በጣም ረዥም ጊዜ እንደሆነ ትዝ አለው። በጣም ወጣት ነበር በዚያ ወቅት።

«ይኼ አዲስ የፈጠርኩት የኅዋ መስተዋት ነው። ዓለማትን ወደ ምድር አቅርቦ በዚህ የውሃ ልክ ሰሌዳ ላይ ያሳየኛል። ይህንንም ማስመሪያ በመጠቀም እንቅስቃሴአቸውንና አቅጣጫቸውን እቀምራለሁ። የኅዋ መስተዋቱን ወደ ግራ፣ ቀኝ፣ ፊትና ኋላ በማንጋለል ባራቱ ነፋሳት ያልተደረሰባቸውን ክፍሎች ማካለል ይችላል። ይህንን ከማድረግ በፊት ግን እንቅስቃሴውን በዚህ መተመኛ ማገናዘብ ይኖርብናል። ምክንያቱም ከማናውቀው ዓለም ውስጥ ከትቶን ካለንበት ለመመለስ አስቸጋሪ ይሆናል። ሂደቱ ሁሉ ከቤት ዓለማት ጋር እያገናዘብን መሆን ይኖርበታል። ይህ እጀታ ደግሞ የውሃ ልኩን ከፍና ዝቅ የሚያደርግ ነው። በርቀት ስብስብ ከዋክብትን ለማየትና ነጥሎ በማቅረብ ለመመርመር ያገለግላል። የዓለማትን ነፀብራቅ በዚህ መቅረፅ ይቻላል።»

«ፍፁም ያለቀለት ነው።» አለ ልዑሉ ታዝቦና ተገርሞ።

«ፍፁም ገና ነው። ብዙ መሻሻል የሚያስፈልገው ነው። የወደፊት ጉዟችንን የሚመራን እስኪሆን ድረስ ጉድለቱ ከፍተኛ ነው። እስከዚያው ድረስ የጨለማ ጉዟችንን በህሊናችን እየታገዝን በቀስተ ደመና እንጓዛዋለን። ምድራችንን መንደርደሪያ አድርገን ቅርብ ከምትባለው ኮከብ ከደረስን የኢላማችን መረብ በመዘርጋት ልንስፋፋ እንችላለን። አውቃለሁ፤ በቀወሰ ጠቢብ ምኞትና ህልም እንደማትማረክ።»

በዕድሜ፣ በተመክሮና በምርምር የተገኘ ምክሩን ጠጥቶ እንደሚናገር ራሱን በመገመትና በችሎታ መራራቅ አለመጣጣምና አለመግባባት በመኖሩ ነገሩን ለማቋረጥ ቢፈልግም ልዑሉ የማወቅና የመረዳት ፍላጎትና ጉጉት ስላደረበት እንዲያቋርጥበት አልፈለገም። ስለ ጭራቅና ልዩ በዐይን ስለማይታዩ ፍጡራን በአፈ-ታሪክ ሲነገር የሚያስፈራ ቢሆንም ፍርሃቱ የታሪኩን መጨረሻ ለመከታተል ከማገድ ይልቅ እንደሚያጓጓ ሁሉ ነበር ሆኖ የተሰማው። «ይቀጥሉ፤ የበለጠ ይንገሩኝ እባክዎትን።» በማለት ተማፀነ።

«ህልም ረቂቅ ነው። ለማንም ይታያል ወይንም ይከሰታል። ጥሩም መጥፎም አለው።»

«የእርስዎ ግን የሚደነቅ ነው!»

«መንፈሴ የኅዋ ክምችቶችን እየሰባበረ ዘወትር ያለማቋረጥ ይጓዛል። ሁሉንም ፈጥሮም መዝግቦም የሚይዘው ግን አዕምሮ ነው። ዓይን ማያ ብቻ ሳይሆን የውስጣዊ ስሜት እንደ ፍፍቴ መፍለቂያም ነው። ድምፅ የአዛዥ ኃይል ነው። ብርሃን የእውነት መሸፈኛ ነው።»

ብርሃን የማይታየውን እንድናይ የሚረዳን ረቂቅ ፀጋ ነው። ምን ለማለት ፈልጎ ነው? የልዑሉ ጭንቅላት ውስጥ በጥርጣሬ የተቋጠረ ድንቁርና ሊመልሰውና ሊረዳው የማይችለውን ጥያቄ መጣበት። ስለዚህም ጠቢቡን ማቋረጥ ነበረበት።

«ቆይ፣ ቆይ፣ ይቆዩ!» ሲል አቋረጠው። «በአብዛኛው ገለፃዎ ብስማማም አሁን በስተመጨረሻ ላይ ያቀረቡትን እቃወማለሁ።»

«ሰዎች ብርሃንን ከሚገምተው በላይ በጣም ነው የሚፈሩት። ስለዚህም ነው ወንጀልና ወሲብ (ፍቅር) በብርሃን ጎልቶ የማይታየው። ወንጀልም ሆነ ፍቅር የሰው ባህሪይ እርካታዎች ናቸው። ጨለማን ተገን አድርገው እውነተኛ ስሜታቸውን መግለፃቸውም ለዚሁ ነው። ሆኖም ጨለማን የፈሩ መስለው ይገኛሉ። ይህ ጭለማ፣ ይህ ድቅድቅ እውነተኛ የዓለማችን ነፀብራቅ ነው። በጨለማ ተገንነት ባይሆን በተለይ አሁን ባለንበት ዘመናችን የሌሎችን ህልውና መገንዘብ አንችልም ነበር። በብርሃን የሚታይ ሁሉ በስውር መጋረጃ የተሸፈነና አሳቻ ብቻ ነው።»

«እሺ ስለመጪው ዘመን ይንገሩኝ፤ ልወቅ። የሰማየ-ሰማያትን መዝገብ ከፍተው በዓለማትና በከዋክብት

መካከል ስለ እኔ የተፃፈውን ይንገሩኝ። ስለ መጪው በድንቁርና አልቆይ።"

"መጪው በአሁኑ ላይ የተመረኮዘ ነው። ዛሬ ከሌለ ነገ አይኖርም። ዛሬና ነገ እንደ ነጠላ ተገጣጥመው ያሉ ናቸው። ስንሠራ ነገ ሊደርስልን ይችላል። ስናፈዝ ነገ ሊደርስብን ይችላል። የመዘጋጀት እንጂ ስለ ነገ ማወቁ በሕይወት ላይ የሚያመጣው ለውጥ ምንም አይኖርም። ምክንያቱም ዛሬ የነገ አሳቻ ነውና። ስለነገ ማወቅ ስለዛሬ ማለፍ ብቻ ይሆናል።"

"አዲስ ጅማሬንም ማወቅ ይሆናል።"

"ሰዎች ስንባል አጀማመሩ ሳናይ አጨራረሱ ያጓጓናል።"

"ያለንበትን በመመርኮዝ።"

"አሳዛኝ ነው።"

"ምኑ?"

"መጪው ጊዜና ሁኔታ። የንጉሡ መሰናበቻ ተቃርቧል።"

"እኔ እነግሣለሁ። ስለዚህ ምን የሚያሳዝን ይሆናል?"

"ከፍተኛ ጦርነት ሲነሳ ይታየኛል።"

"ጦርነት ለእኔ የተፈጥሮ ጨዋታዬ ነው።"

"የጦር ሜዳው ከቤተመንግሥቱ ይሆናል። ድል አድራጊነትን ግን አትጎናፀፈውም።"

"የጃጁ ሽማግሌ የሚናገሩትን አያውቁም ልበል?"

"አደጋ! ልዑል ሆይ! አደጋ ይታየኛል። የወጣት ውበት ፀጋህን ሲያሸንፍህ ይታየኛልና ተጠንቀቅ።" ልዑሉ በማሾፍ ሳቀበት። "ፍቅር ሕይወትህን ያስጋዋል። አንተ ተዋጊ ነህ። ጠንክረህ ቆይ። በምታየው አትረታ። ውበት እንደ ብርሃን ደምቆ እንዳያሳውርህ ተጠንቀቅ።

"በቅዠትዎ መንፈሲ ከሚረበሽ ተኝቼ ባልም የበለጠ ደስታን አገኛለሁ። ነገን እየተጨነቅሁ ልጠብቀው አልሻም። የፍቅር ጠላትነት የሚገርም ነው! ደህና ይደሩ።"

"የንጋት ሮራ መፈንጠቂያዋ ጊዜዋ ተቃርቧል። ልብህን ከሚያሳውርህ የውበት ብርሃን ተጠንቀቅ። ዓለማት እየታዘቧት ኀዋውን ሰንጥቃ እየተጓዘች ነው። መድረሻዋ ተቃርቧል።"

* * *

ወፎች ከቅርንጫፍ ወደ ቅርንጫፍ ክንፋቸውን እያማቱ ቱር ቱር ማለትና ነጋ ነጋ እያሉ መጯጯህ ጀምረዋል። ፀሀይቱ ሁሉን ነገር ዘልቄ ካልሄድኩኝ እያለች በብርሃኗ እያደነች በወስፌ ጨረርዋ ሁሉንም በሙቀቷ መውጋት ጀምራለች። አጢዘው ያደሩ የውሃ እርጥበቶች የሌሊቱ ህይወታቸው ተቀጭቶ በመትነን የንጋቱን አየር እያቀዘቀዙት መሰናበት ጀምረዋል።

ከረጢቷን ተንተርሳ ተኝታ ካደረችበት የዛፍ ሥር ዛሂዳ ባንና ትነሳለች። በመጥፎ ህልም ውስጥ እያለች እግሯን አሽትቶ የሄደው ነገር ምን እንደሆነ ፍፁም ልታውቅ ባትችልም በአውሬ ተበልታ ባለማደሯ ዕድለኛ በመሆኗ እምና አልተጨነቀችበትም። ቅዠቷ ግን መከርከር ጀምሯታል። "ጉድ ነው!" አለች ልክ ለሰው እንደምታወራ። "ምን ዓይነት ቅዠት ነው? ደግሞም ረፍዷል። አሁን የትኛውን መንገድ ይዤ ነው የምሄደው?"

በፀሀይ ብርሃን ነጭ ልብሱ የመላዕክትነት ቅርፅ የሰጠው ፍጡር ሲያነጋግራት ድንግጥ አለች። "እንግዳ ነሽ ላገሩ፤ ዕርዳታ ትፈልጊያለሽ? ከገጠር የመጣሽ ትመስያለሽ"

"መላክ ነዎት? ቅዱስ? የላልይበላው? ከነፎችዎት የት ነው ያሉት?"

"መላክም ቅዱስም አይደለሁም። ቅዱስናውን እንኳን ባልጠላውም።"

"ልክ እንደ ተረቱ፣ እንደ አፈ-ታሪክ ይመስላል። ግን፣ ግን ..."

"የትና ከማን ዘንድ ለመድረስ ነው የምትፈልጊው?"

"እርስዎም እንግዳ ነዎት ለእኔ። ማን ነዎት ለመሆኑ?"

ፊቱ እንዲታይ ብርሃኗ ወዳለችበት ዞር አለላት። በዚህን ጊዜ የፀሃይ ፍንጣቂው የተሟሸ አዲስ ምጣድ የመሰለ ጠይም ፊቷ ላይ ሲያርፍ የሰውየው ልብ አይቶት በማያውቀው ልዩ ኃይል ተመታ። ዛሂዳም ገፅታውን ስትመለከተው ምክንያቱ ግልፅ ያልሆነላት አንዳች ነገር ሰውነቷን ወረረው።

"ራሴን ላስተዋውቅሽና እኔ የአቅሱም ልዑል ያማዲስ ነኝ። እባክሽን ትተሽኝ አትሂጂ!" ትታው መሄድ ስትጀምር እንደ ተራ ሰው ሆኖ ለመናት።

"አትከተሉኝ! ደግሞም እንዳይቀርቡኝ!" ስትል አስጠነቀቀችው።

"ልረዳሽ ብዬ ነው እኔ።"

"እርዳታ አልፈልግም። መንገዴን እኔው ራሴ አገኘዋለሁ። አይጨነቁ።"

"ላሳስርሽ፣ ላስገድልሽ ወይንም ባሪያዬ ላደርግሽ እንደምችል አታውቂም?" አላት በሥልጣኑ የፈለገውን ሊያደርግ መቻሉን ለመግለፅ። በፍቅር ያላገኙትን በኃይል ማግኘት የተካነው ልዑል።

"ታዲያ ምን አገደዎት? ሥልጣንዎት ድሃን መግፋት ከሆነ ከልማድዎት ለምን ይቆጠባሉ?" አለችው ሞቷን ወሳኝ እሱ ከሆነ ትንፋሿን ሳታጣ ህልውናዋን ስትገልፅለት።

"ከዐይኖችሽ ውስጥ የሚፈልቀው ልዩ ኃይል ያግደኛል።" ሲል መለሰላት። ልዩ ኃይል በሠራ አካላቱ ገብቶ የጦረኛ ኃይሉን ስለበረዘበት።

"ሊያምርዎት ይቅር።" አለችው ቅንዝርናው ሊወጣባት የከጀለ መስሎ ስለታያት። ኡ! ኡ! ብትል የሚደርስላት በሌለ ወጥመድ ውስጥ መሆኗን ከመጤፍ ሳትቆጥር። "አሁን መንገዱን ቢለቅቁልኝ ወደምሄድበት እሄዳለሁ። ብዙ ጉዞ ይጠብቀኛል።"

በጉልበት የማያዋጣው ሆኖ አገኘው። ቢያሳስራት ልቡን አትሰጠውም፤ ቢያስገድላት በፍቅሯ ተጠምዶበታል። አገልጋዬ ቢያደርጋት ዐይኖቿ እንደ እሳት እየለበለቡት መሰቃየቱን አልወደደም። መማረክ አለበት። መደለል አለበት። ህልውናዋን ሰርቆ በቁጥጥር እስኪያደርግ ድረስ በቀና መንፈስ አይዞሽ ማለት አለበት። የዱሯን ወፍ ከወጥመዱ ማስገባትና እንደፈረሰ ገርቶ የፈለገ ጊዜ ወደፈለገበት መጋለብ ይኖርበታል። "በእሳት ሰረገላዬ የፈለግሽበት አደርስሻለሁ።" ንጉሥ ጰሌዎስ በርዶስ ላይ ጠላቶቹን ሁሉ ድል ያደረገበት መብራሪያው የነበር ነው።"

"ሰው እንዴት የውሸት ጎተራ ይሆናል? ያውም ልዑል።" አለች እንደ አጠና ክምርና ውቅሪት ውስብስብ ብሎ ድንኳን መሳይ እንደ ጃንጥላ በአናቱ ላይ የተሰካውን ነገር በርቀት ላይ እያስተዋለች። እርግጥ ይህ ነገር ተነስቶ ይበርራል? ብላ በመገረም ራሷን መጠየቋ አልቀረም። አገር ጥላ የወጣችው ግን ለዚህ ምርምር አልነበረም። ሃሳቧ ወደምትሄድበት እየበረረ ነው።

"በእውነት እመኚኝ። በግዛቴ ውስጥ የሚኖረው የሽማግሌው ቅቤአልስ ሥራ ነው።"

"የጠቢቡ?" በመደንገጥና በመገረም ነበር የመለሰችው።

"ስለ እሱ ታውቂያለሽ? ዝናውን ሰምተሻል ማለት ነው?"

"አፈ-ታሪክ ይመስለኝ ነበር።"

«ሁሉ ነገር ስለእሱ እውን ነው። በእሱ ጥበብ አሞራ ሆኜ ነው ግዛቴን እየዞርኩ የማስተዳድረው። ብትተዋወቂው መልካም ነው። ከእርሱ ብዙ መማር ትችያለሽ። ላገናኛችሁ እችላለሁ።»

«ከአክብሮት ጋር አልቀበለውም። አሁን መሄድ ይኖርብኛል።»

«ለአደን ወጥቼ እንዴት እታደናለሁ? ውበትሽን ሳይ ፀሀይ የወጣችልኝ ነበር የመሰለኝ። እባክሽን ትተሽኝ አትሂጂ።»

«እኔ በባላገርነቴ የፀናሁ ነኝ። በግዛትዎ ውስጥ ውብና ለእርስዎ የሚሆኑ አይጠፉምና አያስቸግሩኝ። እንመጣጠንም። ደረጃዎትን ይወቁ።»

ትታው መሄድ ስትጀምር 'ወየው እኔ!' እያለ ሲያለቅስ ሰማችው። ለማረጋገጥም ተመልሳ ቀረብ አለችው። ፊቱን በእጆቹ ጋርዷቸዋል። እጠገቡ እንደቆመች ሲያውቅ አሾልቆ አያት።

«አዎን እያለቀስኩ ነኝ። በልቤ ህመምና ስቃይ የተነሳ አለቅሳለሁ።»

«ዕንባ ግን አይወጣዎትም?»

«በውስጤ እየተንቆረቆረ ነው። ምክንያቱም ...»

«ምክንያቱም?»

«በፍቅርሽ ስለምሰቃይ።» በድንገት ይዞ ይስማታል።

«ሕይወቴን ለመበረዝ ነው ይህ መሳም።»

«እንደ ብርቱ ጦረኛነቴ አይደለም መንፈሴ። በፍቅርሽ ተረትቻለሁ።»

«ይልቀቁኝ አሁን። ከምሄድበት ደርሼ ባንድ ልቤ እዚሁ እመለሳለሁ።»

የሰጠችውን ቃል እንደገና ከጆሮዋ ሰማችው። ምን ሆኛለሁ? መለከፍ እንደዚህ ነው? አዎን ከአንድ ወድቃ አትቀርም። ዕድሏ በመንገድ ላይ ያመጣላትን በእንቀልባ አዝላ መጓዝ ይኖርባታል። ግን አሁን ለመንገዱ አያመቻትም።

«እስከምትመለሽ ድረስ እጠብቅሻለሁ።» ሲል ቃል ገባላት የትም ላለመሄድ ወስኖ። «ምን ያህል ጊዜ ይወስድብሻል?»

«የጣፋጭ ከንፈርዎን ጣዕም ይዞ ወዳጥናፍ መጓዝ ምንም ያህል ጊዜ አይወስድም።» ተመልሳ ሮጣ ተጠመጠመችበት። ስቃዩን ህመሙን ለመካፈል። ልቧ ከፉኛ ገፋፍቷታል።

«ልዑል ሆይ! ሕይወቴን ባዶ አደረጉት። ትርጉም የለሽ አደረጉት። አባቷን ፍለጋ ከገጠር የወጣች ባላገር በሰለጠነው ዓለም ውስጥ የፍቅር እስረኛ ሁናለች። ህልም ነው እንዳልል ንጋትን ከሌት ለይቼ አይቼዋለሁ። ቢሆንም መንቃት ይኖርብኛል። ዱርና በረሃን ለብቻ መንከራተት በመንፈስ የሚታይ አዋጅ ነገሮችን ይፈጥራል ሲባል እሰማ ነበር። ይህም በእኔ ደረሰ ማለት ነው። ከእውነተኛ ሰው ከባላገር አይደለም ፍቅር የጣለኝ። ራሴን ስቻለሁ ማለት ነው? ወይ ፍቅር እንዲህ ያስለፈልፋል? ልዑልን አግኝቼ በፍቅር መውደቅ በተረት እንጂ በእውን የሚሆን አይመስለኝም ነበር። አሁን ግን ካጠገቡ ሁኜና ሁሉን ማድረግ በሚችል ኃይለኛው ክንዱ ጠለላ ሥር እያለሁ ቅር የሚለኝ ነገር አለ።»

«የእኔ ውብ አነጋገርሽ ለዛ የተሞላ ነው። ነገር ግን ቅር የሚለኝ ነገር አለ ስትይ እኔንም ቅሬታ ገባኝ። ምንድነው የእኔ ውብ?»

«ሳመኝ የእኔ ፍቅር።» በፍቅር ወጥመድ ውስጥ እኩልነታቸው ታያት። አልበልጥሽ ብሎ ተሰማት። እንደ አንድ አካል መተንፈስ ከተጀመረ የደረጃ መበላለጥ አይኖረውም። መተናነስም አይታይም። እንደ ውሃ ዋና የውሃውን ኃይልና ጥልቀት እየተቆጣጠሩ እርጥበት፣ ቅዝቃዜውን ችለው የመጣውን ግፊት በስልት ገጥመው በውህደት ሂደትን እንደሚፈጥሩት የመላ አካል ስርጭት ተመስርቶ ተሰማት። «ደግመህ ደጋግመህ ሳመኝ።» ስትል ተማፀነችው። «ከመቅደሉ ላይ እንዳለ ሻማ ልቅለጥልህ። ነገር ግን ልቤን አታሸፍተው። ልቤ ግን የማንም አይሆንም።» ስትል መንፈሷን አራቀችው የጋለ ሰውነቷ በላብ እንደተዘፈቀ።

«የጉድ ነው!» አላት መንፈሱ የደስታ ደመናን ተንተርሶ እየተንሳፈፈ። «ልቤ መሰቃየት ጀመረው።» አላት ነፍሱን ሳይቀር ለእሷ ሰጥቶ ያለበትን ዓለም መዘንጋት ላይ ሲደርስ። ጦርን በድል አድራጊነት ሲወጣው ለእሷ በፍቅር መተናነሱ ምርኮኛዋ ስላደረገው «ለምንድነው በፍርሃት የተጠመድኩት?» ሲል ጠየቃት።

«ከቀንጃጅቶቹና ከልዕልቶቹ ምኔ ነው ሊማርክህ የቻለው? ምን ልሁንልህ?» ጥያቄውን በጥያቄ ሸፈነችው። «ልጥፋ ልሸሸው አደገኛውን ፍቅርህን።» ብላው እንደ እብድ ተነስታ በረረች።

«መርዘኛ ፍቅር!» በማለት ዕድሉንና አጋጣሚውን ረገመ። «በፍቅርሽ ነድፈሽኝ ወዴት ትሄጃለሽ?»

«ደህና ሰንብት ፍቅሬ፤ ደህና ሁንልኝ!» ተነስታ ወደምትሄድበት በረረች።

* * *

«ሽሜ፣ ሽሜ፤ የት ነው ያሉት?» አለ ልዑሉ ወደ ሠገነቱ የታሪክ መዘክር ሲገባ።

«እዚህ ነኝ ጌታዬ። እሽሽ .. የሕይወቴ ምዕራፍ ሳይዘጋ በፊት የትውልዳችንን ታሪክ መዝግቤ ለመጨረስ እየተቻኮልኩ ነው።»

«ፍቅር ይዞኛል!» በማለት ልዑሉ ጠቢቡን ሊያቅፈው ሲል የላባ ብርዑን ቀለም ሊያጠቅስ የነበረው ቅቤአልስ የቀለም ወርቅ ቅሉን ይገጨውና በውስጡ ያለው ቀለም ፅፎት ከነበሩት የታሪክ ጥቅሎች ላይ ይፈስስበታል።

«ያማልክት ያለህ! ቀለሜ በሙሉ ከመዝገቡ ላይ ተደፋ።» ሲል ጮኸ።

ለልዑሉ የሚታየው የዛሂዳ ፍቅር ብቻ ስለነበር ስለ ታሪክም ሆነ ስለደረሰው ጥፋት አልተጨነቀም። «ፍቅር ይዞኛል! ሰምተውኛል?»

«ያስደነገጡኝና ቀለሙን ያስደፉኝ ምኑ ሆነና ነው? ግን ይቅርታ ብታደርግልኝ ወጣት ልዑል ይህንን እንደገና መፃፍ ይኖርብኛል። ጊዜ የለኝም።»

«ደስታዬን መካፈል የሚፈቅዱ ይመስለኝ ነበር።»

«አሰቃቂ ፍፃሜ ያለው ደስታን ለመካፈል አልሻም። የተሰጠህን ማስጠንቀቂያ የዘነጋህ ይመስለኛል።»

«በዚህ ትዕቢትህ ላስገድልህ እችል ነበር።» ሲል ልዑሉ ዛተበት። ታዲያስ ምን ያዘህ? ነፍሰ-ገዳይነትህን እንደሆነ አላጣሁትም በሚል አስተያየት አየው። «ግን ባሳለፍኳቸው ጦርነቶች ብዙ ነገሮችን ተምሬአለሁ። አሁንም ከፍቅር ተመክሮን አግኝቻለሁ። አንድ ሰው በጦርነት ድል አድራጊ ለመሆን ይችላል፤ ነገር ግን በአመፅ! እንዲሁም የሌላውን ልብ መማረክ ይቻላል፤ በሰላምና በፍቅር።»

«ይህ ፍቅር ግን አመፃን ያረገዘ ነው።» በፍቅር ተድበስብሶ ሰላም ሊደፈርስና ህይወት ሊጠፋ አሳቻነቱ የተከሰተለት ጠቢብ ተቃወመው። «ጦርነት ሊከፍትብህ ከሰማያት የተላከ።» ሲልም አስጠነቀቀው።

«ሆኖም ሰላማዊ ውጊያ ነው። የበረታ አይረታም።»

«ለልብህ ፍላጎትና ፍቅር ልዕልቲቱ አለችልህ። የግልህን

ትተህ እንግዳ መፈለግህ ምን ይጠቅምሃል?»

«የማይረቡ ሽማግሌ። ይህቺ ፍፁማዊ ደስታ የሚሰጠኝን ኃይል የታደለች ነች።» ብሎት አንቋሸሾት ወጣ።

«እውነቱን እንደነገርኩህ ግን እመነኝ።» በማለት ድምፁ እንዲሰማው እየራቀ ለሄደው ልዑል ጮኾ ተናገረ።

* * *

ዛሂዳ ደረጃዎቹን ወጥታ ከሠገነቱ ላይ ስትደርስ ከአስራ አራቱ የጥናት ማዕከል ውስጥ ከየትኛው ገብታ ጠቢቡን እንደምታገኘው ግራ ገብቷታል። ስለዚህም በቀለበት መልክ የተሰራውን ሠገነት እየዞረች ለመፈለግ ስታስብ ሠገነቱ እንዳለ ከፊቷ ላይ ይዞር ጀመር። ክፍሎቹም ተራ በተራ አጠገቧ ሲደርሱ ይቆሙ ነበር። እያንዳንዱ የጥናት ክፍል መግቢያው ላይ የፅሁፍና የምስል ምልክት ተቀርፆበት ይገኛል። እጅግም የንባብ ጥናትን ስላላደረገች ፅሁፉ ሲያስቸግራት በምስሉ ትለየው ነበር። በመጀመሪያ መጥቶ አጠገቧ የቆመው በር ላይ የጣት አሻራ ይገኝበታል። ይህም የነገሥታቱ ማኅተምና አሻራ ተቀርፆ የተቀመጠበት ነበር። የሚቀጥለው ደግሞ የልብ ቅርፅ የያዘ ነበር። ይህም የነገሥታቱን የደም ጥናት የያዘ የዘር ሐረጋቸው የተካበተበት ነበር። ለጥቆ ያየችው ክፍል በር ላይ ምንም ዓይነት ፅሁፍ ስለሌለው ቀስ ብላ ተጠግታ ከፈተችው። ከጨለማው ውስጥ የሚሰቀጥጥ ድምፅ በጣርና በልቅሶ አስተጋባባት። ወዲያውም ፈጥና ዘጋችው። ከርስ–መቃብር መሆኑንም አወቀች። የኪነት ክፍሉን አየች። ከዚያም ጥላ ተይዞላት የተጋደመ ሰው መቃብር ተብሎ የተፃፈበትን አይታ ተሳቀቀች። የእናቷ መቃብር እዚህ መሆኑን ስላላወቀች ልትከፍትና ልትጎበኝ ሃሳብ አልነበራትም። የዕፀዋት ምልክት ያለበት የመድኃኒት መቀመሚያ ክፍል መጥቶ ካጠገቧ ቆም ብሎ ወዲያውኑ የቢላዎች ምስል ያለበት በር ደረሰ። የምግብ አዳራሽ ይሆናል በማለት ልትከፍተው እጅዋን ጠጋ ስታደርግ ውልብ ብሎ አለፋት። ሆኖም የቀዶ ጥገና ማከናወኛው እንጂ መመገቢያ ክፍል አልነበረም። የጥያቄ ምልክት ያለበት በር ቢያደናግራትም ቀጥሎ የታያት ግን አስደነቃት።

ሃውልቱ ከፊቷ የነበረውን ክፍል መሽከርከር ወደሚገባው ክፍል ገፍቶ ከፊቷ ሲቆም በስሟ ጠርቶ ሰላም አላት። የመደነቅ ድንጋጤዋን ከፊቷ ላይ እንዳየባት ፈገግ በማለት በዐይኑ ይጠቅሳትና የዘውድ ምልክት ላለበት ክፍል ቦታውን ይለቅቃል። ቁሳቁስ፣ አልባሳትና ንዋይ ማከማቻ መሆኑ ተገለፀላት። የክንድ ያህል ርዝመት ያለው ጦር የተሰካበት ጋሻ የጦር ስልት የሚነደፍበት የግዛት አንድነት ማዕከል መሆኑን አወቀች። በድንገትም በሚያብጠረጥሩ ብርሃን ዐይኖቿ ሊታወሩ ደረሱ። በጠቢቡ ቅቤአልስ የፈለክ ጥናት ውስጥ ተመዝግበው የተቀመጡ የሰማየ–ሰማያት ክፍሎች ነበሩ። ይህንንም አንተርሶ የስበትን ኃይል በማሸነፍ አካሏ የሚንሳፈፍበት ክፍል ደጃፍ መድረሷ ተሰማት የላባና የቀለም ቅል ምስል ያለበት የታሪክ ማዕከል ስትደርስ እንደተንሳፈፈች በሩን ለመክፈት እጅዋን ዘረጋች። የቀለም ቅል ምስል ያለበት የታሪክ ማዕከል ስትደርስ እንደተንሳፈፈች በሩን ለመክፈት እጅዋን ዘረጋች። በሩ ግን ወደ ደመናነት ተለውጦ በውስጡ እየሰነጠቀች ይህ ነው የማይባል ጉ'ዞ ተጉዛ እግሮቿ ከአለት ተጠርቦ ከተሠራው ወለል ላይ አረፉ። ጠቢቡንም በሥራው ተጠምዶ ከጀርባው አየችው።

«ፈጣሪው፣ ጠቢቡ፣ እውነቱ ይውጣ እስቲ?» አለች የመጣችበት ጉዳይ አላስችልሽ ብሏት። የልዑሉ ፍቅር በአንድ በኩል፤ ከሠገነቱ ላይ ያየቻቸው የጠቢቡ ሥራ በሌላ በኩል አየር ተሞልቶ እንደተለቀቀ ፊኛ በመንፈሷ ውስጥ መዋለሉ ግን አልቀረም ነበር።

«ለዚህ ነው እዚህ የመጣሽው? ሰዎች እኔ ዘንድ የሚመጡት ስለ ፈለክ እውቀትን ለመገብየት፤ ያልተስተካከለ አዕምሮአቸውን ቀድጄ እንድጠግንላቸው፤ የሕይወት ሂደታቸውን ለማወቅ ነው።»

«ይህ ቀን እንደሚመጣ ግን አልተከሰተለዎትም ነበር።»

«እውቀቴ የተወሰነና በፍቅር የታወርኩ ነበርኩ።» ሲል ዘጋባት በወጣትነቱ ወቅት የፈፀመውን ጥፋት ሊያቆም የሚችል ቢሆንም እንኳን ለዕለታዊ ተድላው አድልቶ እንደነበር በማስታወስ።

«ጥፋትዎን በዚህ ለመሸፈን ለምን ይሞክራሉ?»

«በእኔ ዕድሜ ሰላምና የመንፈስ ፀጥታ በጣም አስፈላጊ ነው።»

«ሕይወቴ በምን ዓይነት ሂደት ውስጥ እንደነበረች ያውቁ ነበር?»

«እባክሽን በዚህ ልታንገበግቢኝ አትሞክሪ። የሕይወቴን ሃያ ዓመታት በመለየት ናፍቆት ነው የኖርኩት።»

«እሺ ስላለፈው ግድ የለም። አሁን የወደፊቱ ዕድሌ ወዴት እየጠራኝ ነው?»

«አሁን መንፈሴ ስለተሸበረ ነገሮችን ላገጣጥምና ውጤት ያለው መልስ ሊኖረኝ አይችልም።» ሲል መለሰላት ቀድሞ የደረሰበትንና የሚያውቀውን ላለመግለፅ። ልዑሉም እንኳን የተመከረውን አምኖ አልተቀበለውም።

«አሁንም እውቀትዎ የተወሰነና በፍቅር የታወሩ ነዎት ማለት ነው። ስለወደፊቱ ይተንብዩልኝ!»

«የወደፊት ሕይወትሽን እዚህ አታባክኚው። በፍጥነት ወደመጣሽበት ተመለሽ። ሂጂ ሕይወትና ተፈጥሮ ተዋህደው ኑሮሽን እንደለመድሽው ወደምትኖሪበት።»

«አልሄድም!»

«ይህን ግዛት ለቅቀሽ ሂጂ! ወደነበርሽበት ወይንም ወደ ሌላ፤ ሂጂ ይሻልሻል።»

«ሕይወቴ አደጋ እንደሚጠብቃት ልትነግሩኝ ቢሞክሩ አልደነቅም።»

«ከፍተኛ አደጋ ላይ ትወድቂያለሽ፤ የእኔ ልጅ። ከባድ አደጋ ይጠብቅሻል።»

«የተነገረኝ በቂ ነው።»

«እባክሽን ልለምንሽ።»

«ያላወቅሁትን ዓለም ለሙቆርቆር ከገነት ብወጣ በአንደበቱና በውበት ማራኪ የሆነ ልዑልን ልብ ለመቆርቆር የታደልኩ መሆኔን ያውቃሉ?»

«የእኛን ልዑል እንዳይሆን?» የሚመጣውንና የሚሆነውን ያውቃል። ታዲያ መገረሙ፣ መደንገጡና እንግዳ መሆኑ ሞት የማይቀር የተፈጥሮ ክስተት መሆኑ እየታወቀ ሲደርስ እንደመበርገግ ያህል ነበር። ሞትን ማዘግየት እንጂ ማቆም እንደማይችል በሚገባ ያውቃል። ክስተቶችን የመቀየር ኃይል ሳይኖረው አሁን በእርጅና ተይዞ ጊዜ እያጠረው ነው።

«ገና እንዳየሁት የልቤን አዳራሽ ቤቱ አደረገ። እንደ ማር የሚጣፍጠውንም ከንፈሩን ስቀምሰው ልቤ በፍቅሩ ቀለጠለት።»

«በዚህ አትታለይ የእኔ ልጅ። ከቀድሞው ይበልጥ ሕይወትሽን ለአደጋ አትዳርጊው። ስለ ራስሽ አስቢ። የሆነውን ሁሉ እንደ ቅዠት ቆጥረሽ ሂጂ፤ ብረሪ፣ ራስሽን አድኚ።»

«ከእናቴ አለያይተውኝ በበረት እንዳድግ አደረጉኝ።

ህልውናዬን አወደቁት። አሁን ግን የእኔ ወደሆነው ዓለም መጥቻለሁ። የሥልጣኔ አውታሩን እናግቼ የዓለምን ጉድ አያለሁ እንጂ አልለቅም። የልዕልነትንት ማዕረጌን ተጎናፅፌ የአቅሱምን ድሩ ከቅጠላት፣ ማጉ ከከበሩ ዛፎች ቅርፊት የተሠራውን ቀሚሴን ለብሼ ስታይ ዓለም በውበቴ እየተደነቀ በዘፈንና በተረት ዘላለማዊ አድርጎ ያኖረኛል። ይህንን ክብር አትኑሪው፤ ህልምሽና መብትሽ ተዳፍና ይቅር ነው የሚሉኝ?»

«ይህ እብደት ሊያጠፋሽ እየጣረ ነው። ከዚህ ዓለም ዕድሜሽን ሙሉ ተገልለሽ ስለኖርሽ ምንም የሚቀርብሽ አይኖርም።»

"ስለርሱ አሁን ተከስቶልኛል። ማብራራት አያስፈልግዎትም።»

«ከሞት አፋፍ ያለን የሽማግሌ ልብ አታሳዝኚ። ከገጠር ወስጄሽ እንድታድጊ ያደረግሁሽ ሕይወትሽን ለመጠበቅ ብዬ ነበር። ትገደይ ነበር። ይህንንም ያደረግሁት ለሁለታችሁም ስል ነበር። ላንቺና ለእናትሽ።» በትዝብት እንደምትመለከተው አያት። የተሚላና አባባሉን ተጨባጭ ለማድረግም «ለእኔም ጭምር።» ሲል አከለበት። «ለዚህም ነው እስካሁን በሕይወት የኖርሽው።» በማለትም ሊሸንግላት ሞከረ።

«እናቴ ማን ነበረች?» አልፋው ከመጣችው ጥላ ተይዞለት የተጋደመ ሰው ምስል ካለበት ቤት አካላቷ እንዳይፈርስ ተገንዞ መቀመጡን አታውቅም።

«ኃይል የነበራት ሴት ነበረች። ያልታሰበ ነገር ተፈጠረ። መፍትሄም መፈለግ ነበረብን። አገር ለቅቆ ለመጥፋትም አስቤ ነበር። ሆኖም እስካጥናፍ ሄጄ ብሰወርም ከህሊናዬ ልደበቅ ስለማልችል ሃሳቡን ውድቅ አደረግሁት። ምርጫ ሆኖ ያገኘነውም ለማደኅ መስጠት ብቻ ነበር፤ ህይወትሽን ለማትረፍ።»

«ከምኑ?»

«ኣባከሽን ልጄ ያን ሁሉ ነገር ላስታውስ አልፈልግም። እስከምትወለጂ ድረስ መንፈሴ ሲንገበገብና ስሰቃይ የኖርኩትን እኔ ብቻ ነበር የማውቀው። ለዘጠኝ ወራት በምጥ፣ በፀሎትና መንፈሴን በማረጋጋት ተሰቃየሁልሽ። ከአማልክትም ጋር በመንፈስና በዚህ በሥራዬ ተገናኝቼ ተማፀንኩ።»

የሰማያትን በሮች ከፍቶ፤ የከዋክብትን ሂደት አጥንቶ፤ ክስተቶችን ለመቀየር የተቻለውን አድርጎ ነበር። በወቅቱ የከሰቱት ነገር ቢኖር ጦርነት እንደሚመጣና የሚወስደው ጊዜ ፋታ ሰጥቶት መፍትሔ እንደሚፈልግለት ነበር። ለማድበስበስ፣ ለማዳፈን፣ በምስጢር ለመያዝ።

«እናቴ ማን ነበረች?» ቁጣ በተሞላበት ቃል ደግማ ጠየቀችው። «ማን ነበረች እናቴ?»

«ከንግሥቲቱ ጋር ፍቅር ያዘኝ። እሷም ዕረፍት አጣችብኝ። በስርቆት ፍቅር በጣም ታውረን ነበር። በፍቅራችን ፈጠርንሽ። የአንቺንም ሕይወት ለማትረፍ እንድትሰወሪ ያደረግነው በዚሁ የፍቅራችን ግለት ነበር። ፍቅራችን ካንቺ ጋር ስለተሰደደ መቀጫችን ሆንሽብን። ከዚህ በኋላ አንቺ በልጠሽ ታየሽን። በመካከላችን ሰላም ጠፋ። የንጉሡን ከመካከላችን መወገድ በጣም ፈልጋ በእኔ መቃወም ጥረቷን በሙሉ አከሸፍኩባት። ፍቅራችን መልኩን ቢቀይርም በፍፁም አልጠፋም ነበር፤ እስከመጨረሻው።»

«ፍቅራችሁን እንድካፈል ምንም ያደረጋችሁት ጥረት የለም። መንገድ ፈልጋችሁ እዚሁ በማደኅ ተቀምጨ ማንነታችሁን አውቄ መኖር እችል አልነበረም። እውቀቴን ሸፍናችሁ ብታሳውሩኝና አሁን ብነቃ እናት የሌለኝና አባቴም የምኮራበት ሳይሆን ቀረ።»

«አማልክት የከፉዎችን ዓይኖች አሳውረው፣ ልቡናቸውን ደፍነውና ጆሮአቸውን አደንቁረውልን ነበር። ንጉሡም ከሄደበት ጦርነት ሳይመለስ ቆየልን። እንቢልታና መለከት እያስነፋ፣ ነጋሪትና ከበሮ እያስጎሰመ በድል አድራጊነት ካስገበረው አዲሱ ግዛቱ ሲመለስ እኛም ጥረታችን ተሳክቶልን ተቀበልነው።»

«የትም ጣሉኝ፣ ረሱኝ። እናቴም ናፍቆቷን ሳትወጣኝ ሞተች።» መሞቷን በማወቋ አልተደነቀም፡፡ ልትፈታተነውና እልኳን ልትወጣ ብላ እንጂ በሠገነቱ ውስጥ መንፈሷ በጎቡህ አንዳንድ ነገሮችን ቀስሟል።

«ስላለፈው ላዝን አልፈቅድም። ጊዜዬ ተቃርቧል። በትዝታ ይዤው የምጓዘው ነገር አይደለም። ከመወለድሽ በፊት እኔን አሳውሮኝ የነበረው ፍቅር አንቺን ውድ ልጄን እንዲያሳውርብኝ አልፈለግም።» ልዑሉ ሚስት አለችው። ያውም ሰይጣን የሆነች ልዕልት።»

«ምስጢርን ለመፍታት ተዓምር የሚፈለግበት ግዛት ነው የገባሁት። ይህ ከመሆኑ በፊት ግን ቀላል ሊያደርጉት ይችሉ ነበር።»

«ቀላል ሊታደርጊ የምትችይው አንቺው ብቻ ነሽ። በቀላሉ ወደመጣሽበት በመመለስ።»

«ይህ ምስጢር እስከተጋለጠ ድረስ የትም አልሄድም።»

«ፍፁም አስቸጋሪ ፍጡር ነሽ።» ሲል ሮኸባት። ልዑሉ ዛሂዳ ያለችበትን ቦታ ፈልጎ በማጣቱ በከዋክብት ተመርቶ እንዲጠቁመው ሲመጣ ዛሂዳን ሲያባርራት ያገኘዋል። «አህ፣ የተከበርከ ጌታዬ! ያልተጠበቀው ጉብኝትህ ስሜቴን ነክቶታል። እሷ እየሄደች ነው።»

«ወዴት?»

«ኣትብት መሰረቷ ካለበት። ቀጥይ! በይ ሂጂ እንጂ!» ሲል ገሰፀው። ዛሂዳ ግን ሮጣ ትጠፋለች።

«ስለ አድራጎቴ ይቅርታ፤ የአቅሱም ልዑል።» እጅ በመንሳት። «የራሴን ተዋጥቼዋለሁ። የቀረው የራስህ ነው።»

ልዑሉ በንዴት ተከትሏት ይወጣል። ብዙም ሳይርቅ ተመልሶ ይገባል።

«ምንድን ነው የነገሯት?»

«ባለትዳር ከመሆንህ ሌላ ለባተሌ ምን ይነገራል? የንጉሣዊ ደምህን እንደሆነ ረስተሽዋል።»

«ደማችን ተቀድቶ ቢታይ ልዩነቱ ፍፁም አይታይም።» በማለት ሮኸበት።

ቅቤአልስ የነገሥታቱን የዘር ሀረግና ደም አጥንቶ ምንም ልዩነት እንደሌለው ከትቦ በክፍል ቁጥር ሁለት ውስጥ አስቀምጦታል። ከትውልድ እስከ ትውልድ ከእኛ የተሻለ ፍጡር የለም እያሉ እጅ ያልነሳቸውን፣ በጉልበቱና እውቀቱ ያላገለገላቸውን፣ በመገበር የክፍል ቁጥር አስርን ያላጣበበላቸውንና በተፈጥሮ እውቀቱም ይሁን በምርምር አለመተናነሳቸውና ዓለምን እንዲጋሯት የጠየቃቸውን ሁሉ ከክፍል ቁጥር ሦስት ካልተመዘገበው ከርሰ–መቃብር እንዳላስጣሉ ያህል አሁን የልዕልናው ደም መዘውሩ በፍቅር ቢነደፍ ደረጃውን በማሳነስ ለራሱ ፍላጎት እኩልነትን ቢሰብክ የሚመፃደቅ መስሎ ታየው እንጂ እውነተኛ ስሜቱን ሊቀበለው አልወደደም።

«መቸም በቅንነት፣ የእኔ ልዑል፣ ልዑልነትህን በመዘንጋት ነው ከኅብረተሰብ ዝቃጭ ጋር ከንፈርህን ያጋጠምከው።»

«ስለ ፍቅረኛዬ ይህንን በማለትህ አዋርደኸኛል።» የልዑሉ ፊት በንዴት ይንቀጠቀጥ ነበር። በታጠቀው ጩቤ ወደ ክፍል ቁጥር ሶስት ቢሰድደው በወደደ ነበር። እውቀቱን ይሻዋል። የግዛቱ ኃይል የሚጠበቀው በእርሱ ሥራና ችሎታ ነው። እውቀቱ ከጠላት እውቀት የላቀ ነበር። ምንጊዜም ከእነሱ ተሽሎና ቀድሞ ይገኛል እንጂ ወደ ኋላ ቀርቶ አያውቅም። ብረቱን አቅልጦ፣ ሳር ቅጠሉን አሰባስቦ፣ ሀረግ ቅርፊቱን አስተልትሎ ...ከጢያራው አንስቶ እስከ ጭንቅላት ቀዶ ጥገናውን የተካነ አገልጋዩ ነበር። ስለዚህ መኖሩን ይፈቅዳል። በሕይወት መቆየቱን። ባይሆንማ ኑሮ አንተ ብሎ ስለሚጠራው እንኳን የልዕልና ክብርን በመንሳት ተብሎ ለመቀጣጫ በአደባባይ ፊት ሞት ይበይንበት ነበር።

«ኢንዲያውም የእኔ ጌታ! በሰማያት የተፃፈውን ነው ያነበብኩልህ። የመጥፎ ዕድል ምልክቱ ከተገለፀልኝ ጊዜ ጀምሮ ...»

«ያለ ፍቅር በክብር መኖር አልችልም።»

«ያ አይደለም ያንተ ፍቅር። አጥፊህ ነው። አስብ፤ አድምጠኝ!»

«ያችን ከይሲ ልዕልት እንደዚህ ለመናገር አይደፍሩም ነበር።» ብሎት ትቶት ይወጣል።

«ኢባካችሁ አማልክት ከዚህ ጉድ ሰውሩኝ። ወይንም ሕይወቴን ተቀበሏት።» በማለት ሕይወቱን አማረረ።

«ልዑሉ የት ነው ያለው? የት ነው ያለው እሱ?» ስትል ልዕልቲቱ እየተጣደፈች ትገባለች።

«ልዕልት፣ ካልጠፋ ቦታ ይህ የእሱ መደበቂያ አይደለም።» ሁላችሁም ገደል ግቡ ቢል በፈቀደ ነበር።

«ጭንቀት ሲይዘው እርስዎ ዘንድ ለምክር ሁልጊዜ እንደሚመጣ አውቃለሁ። ያዳምጥዎታል፤ ይሰማዎታል። የጥንት ፍቅሩን ወዳጁ ልቡን እንደምሻ ይነገሩልኝ ስሜቱ ተሰልቦ ነው ከእኔ ዘንድ የሚመጣው። በዚህም በጣም ከፍቶኛል። አዲስ የፍቅር ዜማ የምታሰማው ፍቅረኛ ሳያገኝ አይቀርም በዚህ ከሃዲና ዱር ዓለም ውስጥ። ያገኘኋት ጊዜ ግን እስከነነጆዋ ነው የማቃጥላት።» በመጣችበት ኃይል ተሽርክራ በመሽቀንጠር ትወጣለች።

* * *

ልዑል ያማዲስ የክፍል ቁጥር አስራ ሶስትን በመጠቀም ከእሳት ሠረገላው ደረሰ። ክንፎቹ ለመብረር እየተጣቀ ሲዘረጋጉ ብሶሉ በአራት ነፋሳት መዋለል ጀመረ። ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላም የመነሻውን ሥፍራ በሚዛናዊ ማዕከሉ መዝግቦ የሚጓዝበትን በመንደፍ ቀስቱን አጉልቶ አሳየ። በልዩ ጥበባዊ ኃይል የሚሰራው ይህ መብረሪያ ለዋና እንደሚወረው ዋናተኛ ክንፎቹን ወደ ፊቱ ዘርግቶ ከገጠመ በኋላ በደረቱ ላይ በማሳለፍ ከኋለኛው አካሉ ጋር አጋጥሞ አፍንጫውን በማሾል አየሩን ሰንጥቆ መብረር ጀመረ። ጊዜም ሳይወስድበት ዛሂዳ ካለችበት ደን ደረሰ። ከደኑ አናት ላይ ካንሳፈፈው በኋላ በዘረጋው መንጠላጥል ተንጠልጥሎ በደኑ ውስጥ ሾልኮ ይወርድና መንገዱን ይዘጋባታል።

«ወዴት ነው የምትበርሪው?»

«ፍቅርህ ቅዱስ መስሎኝ ነበር፤» አለችው ገና እንዳየችው። አስራ አራቱንም የሠገነት ማዕከሎች በጥልቀት ባትመራመራቸውም ደርሳባቸው ሳለ አንዳንድ ነገሮች ለመረዳት በቅታለች። ከእሷ ብጤው ወስደው የግል ሃብት ያከማቹበትን፤ የጦር አድማና ማስገበሪያቸውን፤ የራሳቸውን ክብር የሚያጎላ ታሪክ ፅፈው ያከማቹበትን፤ ከዋክብትና ዓለማት በሙሉ ለእነሱ እንዲገብሩላቸው የሚያጠኑበትን፤ የራሳቸውን ጤንነት ብቻ የሚንከባከቡበትን፤ በአየር መንሳፈፊያው እየታገዙ የሚዝናኑበትን፤ ሃውልት በመሥራት ህያውነታቸውን የሚያሳዩትን፤ በከፍተኛ ክብር አስከሬናቸውን በምቾት ያሳረፉትን፤ ሃዘናቸውን ወደ ደስታ ለመለወጥ የኪነት መድረኩን፤ የዘር ሀረጋቸውን እንደ ደሴት ያጠሩበትን፤ ህልውናቸውና ግዛታቸው ተጋኖና ተከብሮ የሚኖርበትን ሁሉ ተመልክታለች። ለእሷና የእሷ መሰሎችን የሚጠቅም ምንም ነገር አላየችም። መንፈሷ ከፉኛ ተከፍቷል። የአምላክነት ባህርያቸውን የጠየቀውን ሁሉ በሰይጣናዊ ሥልጣናቸው ቀጭተውታል። እጅ ያልነሳቸውን ሁሉ በሰይፍ ሰይደውት በክፍል ቁጥር ሶስት ካልታወቀው ከስውሩ መቃብር ውስጥ አጭቀውታል። አዳፍነውታል። ለመክፈት ስትሞክርም ውይ! ውይ! ብለው የጮሁባትም ትዝ አላት። አታውቃቸውም። ግን አቤቱታቸውን አሰሙ። በራሳቸው ስለደረሰው ሳይሆን ስለ እውነት ብለው ጮኹባት። ጆሮዋ ቢሰማም ልቦናዋ አላስተዋለላትም።

«ግን ሁላችንም ሰውን በአምላክነት እናመልከዋለን። አክብሮት ምክንያታዊ ነው። ነገር ግን ከሌላው ማግ መውደቅና ራስን ማሳነስ ተገቢ አይደለም። ሰብዓዊነታቸው በአምላክነት የተነደፉት ሳይቀሩ ውስጣቸው ወንጀልና ከፋትን የተሞላ ነው። ቅድስና የላቸውም። ከፋታቸውና ደካማነታቸው ከአዕምሮ የማይጠፋ መጥፎ ትዝታ ነው። ግዴታም ኅብረተሰቡን እንዲቀበላቸው አድርጓቸዋል።»

«ሕይወቴን ከጦረኞችና ከጠቢባን ጋር ያደረግሁ ሁሉ በእጄ ሁሉ በደጄ የጎደለኝን ለማሟላት እንዴት ይሳነኛል? አንቺስ ይህን ልታሟይልኝ ምን ያህል ያስቸግርሻል? ሕይወታችን እስካለች ድረስ እስቲ እንካፈላት።» አቅፎ ሲስማት ተዝለፍልፋ ትወድቃለች። ልዕልቲቱ በብሶል እየተመራች መጥታ ስለነበር ካሉበት ትደርስባቸዋለች። «ወየው! ዛሂዳ። ምን ነካሽ? ተናገሪ እንጂ።» አጠገቧ ይንበረከካል። እባክሽን ንቂ።»

«ለነገሩ የምትሳሳሙ መስሎኝ ነበር።» አለች ልዕልቲቱ በነገሩ ሁሉ ግራ ተጋብታ።

«ሚጂና መድኃኒት ፈልገሽ አምጪ።»

«ስሟን ስትጠራ የሰማሁህ መሰለኝ?»

«ታማለች። አንድ ነገር አድርጊ!»

«ኢንዴት ልታውቃት ቻልክ?»

«ስለአማልክት ብለሽ!» ንዴት ባለው ልምምጥ ነበር።

«ሚጂ ጠቢቡን እልካቸዋለሁ።»

ጠቢቡ የታሪኩን ፍፃሜ ከመዘገበ በኋላ ለዐይን ምስክርነት ካሉበት ሲመጣ ልዕልቲቱ ስላየችው ተደስታ «አ! ይኸው፤ ልክ እንደጠሯቸው ያህል።» ስትል ወደ ጠቢቡ አመለከተችው።

«ይፍጠኑና ይመርምሯት። ፍጠኑ!» አለ ልዑሉ ያማዲስ። ጠቢቡ የሚያደርገውን ምርመራ ሲመለከት ከቆየ በኋላ «እንዴት ነች?» ሲል ጠየቀው። ቅቤአልስ ግን ክስተትን ለመቀልበስ ከመጣር ወደኋላ የማይል በመሆኑ ምክንያት አድርጎ ሊያራርቃቸው ፈለገ።

«ክፉኛ ተለክፋለች። ትኩሳት ለቆባታል።»

«ያክሟት።»

«አቅም የለኝም። ለመትረፍ አትችልም። ጣረ—ሞት ተጣግቷታል።» ከአቅሙ በላይ መሆኑን በመግለፅና በሽታው ለእነሱም ቢሆን አስጊነቱን ገልፆ ችግሩን ሊፈታው ስለፈለገ «ከመጣችበት ብትመለስ የተሻለ ነው። ይህንንም ለማድረግ ፈቃደኛ ነኝ።» ሲል በጥሞና ገለፀላቸው።

«በጣም ወጣትና ውብ የሆነች ልጅ። ከእኔ ዘንድ ትቀመጣለች እስከተሻላት ድረስ፡፡» አለች አይታት ያዘነችላት ልዕልት በተኑሽ።

«ግን እኮ ልዕልት በተኑሽ ...»

«ልዕልቲቱ ያለችውን ሰምተዋል። ይህችን ምስኪን ማዳን ይኖርብዎታል፡፡»

«እንዲያውም በይፋ እንደ እህቴ አድርጌ አሳድጋታለሁ፡፡»

«በሽታዋ ወደ ነገሥታት ዘር እንዳይተላለፍ እሰጋለሁ፡፡»

«አምስት ዓመት ሙሉ የማይንቀሳቀሰውን የንጉሡን በድን በህክምና ጥበብህ ዕድሜውን አራዝመህለታል፡፡» ለህዝብና በአደባባይ ነው እንጂ እርስዎ እርሳቸው የሚባባሉት በውስጣቸው በመሃከላቸው እንደማናቸውም ሰብዕ ተራና ሟች ፍጡር በመሆናቸው የማያንፀባርቁት ጠባይ የለም።

«አማልክት ረድተውት ነው፡፡»

«ሷንም ይረዷታል፡፡»

ክርክሩ የማያዛልቅ ስለሆነ ይዘዋት ይሄዳሉ። የሾስቱም መብረሪያቸው በአንድነት ተሰካክቶ ሲበር ግዙፍነቱ በአገሩ ላይ ግርዶሽ ፈጥሮ ነበር።

* * *

የልዕልቲቱ መኝታ ቤት በሙቀት እየቀለጠ በብልቃጥ ውስጥ የተሰኩትን ክሮች ለማንደድ ሰሙ በሰከ መቃ ውስጥ ይንጠባጠባል። ክፍሉን የወርቃማነት ብርሃን ከመስጠታቸውም በላይ የወርቅ ጌጣጌጦቹ በሚያገኙት ብርሃን ዐይንን ስለሚያጥበረብሩ የተለያዩ የጌጥ ልባሶች ተሸልመዋል። የጥላ ቅርፁን እየቀያየረ ወቅቱንና ሰዓቱን የሚለካው ተውለብላቢት ከክፍሉ በአንደኛው ጎን ተሰቅሎ ይገኛል። የንጉሡን ግዛት የሚያሳይ ካርታ የዘውድና የንጉሡ መለያ የሆነው የጦርና ጋሻ ምልክት ታትሞበት ከሰፊው ግድግዳ ላይ ይታያል። አልጋው በጨሌ በተጌጡ ክሮች ተጋርዷል።

«የት ነው ያለሁት? ምንድነው የሆንኩት?» ያለችበትንና ወቅቱን የሳተችው ዛሂዳ አካባቢዋን ካጤነች በኋላ አጠገቧ የነበረውን ሰው ጠየቀች።

«ዛሂዳ የእኔ ፍቅር፤ በሕይወት አለሽ። ነቃሽልኝ፡፡»

«ማን ነህ አንተ?»

«የአቅሱም ልዑል ነኝ። አስታወስሽኝ?»

ልዑል?! የማነው ልዑል? እኔስ ማነኝ? ራስ ምታት ተሰማት።

«ማን ነኝ እኔ?»

«የእኔ ፍቅር ዛሂዳ! ዛሂዳ ነሽ። ከእኔ ቤተመንግሥቴ ውስጥ ነው ያለሽው፡፡»

የልዕልቲቱ አገልጋይ ምግብ ይዛላት ስትመጣ ልዑሉ የሚያወራውን ትሰማለች፡፡ ተደብቃም ማዳመጧን ቀጠለች። «የእኔ ውድ! ንጉሡ ትናንት አረፈ። ነገ እንጋባና ልዕልት አደርግሻለሁ። የቃሌንም ማኅተም በዚህ መሳም አረጋግጥልሻለሁ፡፡»

አገልጋይዋ ዘቦነሽ ስትሮጥ ወደ ልዕልቲቱ በመሄድ ያየችውንና የሰማችውን ትነግራታለች።

«ልዕልት። ልዕልት እመቤቴ!»

«ምነው ሞተች?» ድንጋጤ ይዟት ነበር የጠየቀቻት።

ልዑሉ ዛሂዳን ብቻዋን ትቷት ወደ ሠገነቱ ወጣ። ጠቢቡን ሲያገኘውም በአክብሮት እጅ ነሳው፡፡ «ላመሰግንዎት ነው የመጣሁት ጠቢብ ቅቤአልስ። የምትደነቁ መድኃኒተኛ ነዎት፡፡»

ልዕልቲቱ ከአገልጋይዋ የሰማችው ሃሜታ ከፉኛ አስቆጥቷታል። ንዴትም ቅናትም መንፈሷን ወዲያውኑ ተቆጣጠረው። የእህቷ መተኪያ እንድትሆናት በፈለገችና ከህመሟ እንድታገግም በቅንነት ባቀረበቻት ከዚህ በመድረሷ አንገበገባት። «የሰማሁትን ማመን ያስቸግረኛል። ቃል ኪዳን?» ስትል ጮኸች፤ የአገልጋይዋ ዘቦነሽን ቃል በመድገም። ልዕልቲቱ ከአገልጋይዋ የምግብ ማቅረቢያ ላይ የነበረውን ቢላዋ አንስታ እየዛተች በጥድፊያ ዛሂዳ ካለችበት ትሄዳለች።

«ይምጡና ይመልከቷት፡፡» ሲል ልዑሉ ጠቢቡ አብሮት ወደ ዛሂዳ ዘንድ እንዲወርድ ጋበዘው። «ሕይወት የሰጧት ስለሆኑ እንደአባቷ ነው የሚቆጠሩት፡፡»

ልዕልቲቱ ቢላውን በዛቻ እያወዛወዘች ዛሂዳ ዘንድ እንደደረሰች «የፍቅረኛውን ባሌን ልብ ወሰድሽብኝ። አሁን ደግሞ ግዛቴን ልትወስጅብኝ ነው?!» ስትል ልትወጋት ስትል ጠቢቡ ይደርስና ሊያስቆማት ጮኾ ይናገራታል።

«ልዕልት፣ አይሆንም፤ ተይ! የገዛ እህትሽ ነች!» ጩኸቱ ሊያቆማት አልቻለም። ንዴቷ በቀላሉ ሊበርድላትና ራሷን ልትቆጣጠር አልቻለችም። ያለ ርህራሄ ደጋግማ ወጋቻት። ዛሂዳም ከመሬቱ ላይ ተዘረጋች። ባደረሰችው ጥፋትና እህቷ መሆኗን በማወቋ በድንጋጤ ቢላውን ከመሬቱ ላይ ጣለችው፡፡ ልዑሉ ባየው አድራጎት ተሳቅቆ ከቆመበት በድንጋጤ የሚንቀጠቀጠውን አካሉን ወባ እንደያዘው በሽተኛ እየተርገፈገፈ ሄዶ ከዛሂዳ ሬሣ ላይ በመንሰቅሰቅ ይወድቃል።

የተፈጠረውን አደጋ ለማቆም ያልቻለው ጠቢብ ይህ የአሰቃቂን ሁኔታ መነሻ ማውራት ይጀምራል። «አባትሽ ጦሩን እየመራ ምሥራቅን ለማቅናት በሄደ ሰሞን በነፋሻማው ምሽት እናትሽ ከጎዋ ምርምር ጣቢያዬ ከሠገነቱ ላይ መጣች። መንፈሴ ሁሉ በከዋክብትና በርቀት ባሉ ዓለማት መካከል ይዋልል ነበር። ለብዙ ዘመን ሁለት ህልሞች ነበሩኝ፡፡ ከራቁት ዓለማት ለመድረስና የንግሥቲቱን ልብ ለመመርመር። ክብርና ሥልጣን፣ ውበት፣ ፍቅርና፣ ሱስ በተሞላው ሁኔታ ሞቃት እጆቿንና ለጋ ሰውነቷን አሳረፈችብኝ። በመውደድ መቅለጥ ውስጥም ገብተን ጠፋን። በዚህም ውብ ልጃችንን እሷን አፈራን። ዛሂዳም ብለን ሰየምናት። ለጤናና ነፋስ ለመቀበል በሚል ሰበብ አሳብበን ከዚህ ቀደም ወዳልታወቀ አገር በመሄድ በምስጢርና ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ ለማደጎ ሰጠናት። ያን ጊዜ ብርቱ የነበረ ጊዜ በፍቅር ኃይል ተገፍቼ ንጉሡን ልመርዘው አስቤ ነበር። ሕይወቷን በዚህ መንገድ ካተረፍኩላት ሌላ ሕይወት ማጥፋት ህሊናዬ አልቀበለውም አለኝ። ያዳፈኑት እሳት ረመጥ ሆኖ ማቃጠሉ ግን አልተከሰተለኝም ነበር።

ልዑሉ የዛሂዳ ሬሣ ላይ ተጣብቆ እየተንሰቀሰቀ ማልቀሱን አላቋረጠም። ልዕልቲቱ ከመሬት ላይ ጥላው የነበረውን ቢላዋ አንስታ ጀርባውን ሰጥቶ ታሪኩን የሚነግራትን ጠቢቡን ቅቤአልስን ትወጋዋለች፡፡ ጠቢቡምበስቃይ ተሰቅጥጦ ጮኸ። ልዑሉ ይህንን ሲመለከት ከነበረበት ተነስቶ ታጥቆት በነበረው ጩቤ ልዕልቲቷን ወጋት እሷም እጅዋ ውስጥ ባለው ቢላዋ ትወጋውና ሁለቱም እንደተያያዙ ከመሬት ላይ እንደወደቁ ሳይነሱ ቀሩ።

* * *

የጠቢቡ ልጅ፣ የልዕልቲቱ እህትና የልዑሉ ፍቅረኛ ታሪክ እንዳፈኑት ሳይቀር በአሰቃቂ ሁኔታ ተፈፀመ ብለው አቶ አዙማትራ የምሽቱን ትረካቸውን ሲጨርሱ ያሞጨሞጩት ዐይኖቻቸው ሩቅ የሚያዩና ትዝታን የተሞሉ ነበሩ።

ተፈጸመ

# የግጥም ጉባኤ

## በታኘ!

ከአዲስ ተገኝ – ከዳላስ

ሰው ይሉኘታን አጣጥሎ
እንደዚህ እንዴት ይዋሻል
ዓይን አውጥቶ ቅንድብ ነቅሎ
ለምን ለሚያልፍ ዓለም ይቀጥፋል!
እግዜር የሚጠየፈውን ኃጢአት
የጥል ጥንስስ መርዛም መግል
መካሪ መስሎ በመሰሪነት
መዝራትስ እንዴት ያስችለዋል!
እንዴት እንደይሁዳ
የሕሊና ፍርድ ቃላባይ
ብልሹ ግብረ–ገዳዳ
ድራኩይላ ነፍሰ–ገዳይ
ከቶስ እንደነ ቃዬል
የጥፋት አባት ይሆናል።
እኔስ እርሱን በመስራቱ
ያሕዌን በውነት ጠላሁት
ልዩ ገሀነም በስልቱ
ስላልመደበለት ኮነንኩት
ቢሻው ያቃጥለኝ እንጂ –
ይቅርታውን አወገዝኩት።
ኧረ ተው ስማኝ ያገሬ ልጅ
በታኘነቱ ቃል የለውም
ሥነ–ጽሑፍን ይገድላል እንጂ
በሰው ሳንቃ አይገለፅም!
ቢሆንም እንደዚያ ሆኖ
ጠማማ መርፌው አይወጋም
ለረጋ ቅቤ ለሊጥ ፋርኖ
ለስምጥ ረግረግ አይበጅም።
እንደዚሁም ሰው በድሎ
ፈጣሪውን አስወቅሶ
«ሞኝ እኮ ሞልቷል» ብሎ
ሕዝብን ሲልጥ አተራምሶ!
የጠጣነት ናላው ታሽቶ
የቀስ በቀስ የለውጥ ምርቁ
ተሻሽሎ ተሰካክቶ
ከቶ ቢሆን ሸንቁጥ ንቁ
መካች አጋዥ ወገን ሞልቶ
እንዴት ሊጣል በደረቁ።
እኔስ እርሱን በመስራቱ
ያሕዌን በውነት ጠላሁት
ልዩ ገሀነም በስልቱ
ስላልመደበለት ኮነንኩት
ቢሻው ያቃጥለኝ እንጂ –
ይቅርታውን አወገዝኩት።
የለም በርሱ ቤትማ
እንደሀሳቡ አፈራርሶናል
ብንታገል ቢቻለውማ
እንደቁብ ዶሮ ጠባብሶናል።
ኧረ ስማኝ ተው ወገኔ
ስለዚህ የሌት ቀበሮ
ከፋፋይ አባ ጉንጉኔ
የዝግመተ–ለወጥ ዝንጀሮ።
ለነገሩማ ዋጋ የለውም
ስለእርሱ መነጋገር
ግን ምሣሌያዊነቱ ይተምም
ለሌሎች እንዲያስተምር
ለታሪክ እንዲመሰከር።
እናም የሚገርመው እኮ
ሌት ከሠላይ ተዋውሎ
እንደዱር የውድቅት እሸኮኮ
ቀን ከወገን ተመሳስሎ
አፍነክንኮ ተፍነክንኮ
እንደ ሠርገኛ ተመሳስሎ።
እኔስ እርሱን በመስራቱ
ያሕዌን በውነት ጠላሁት
ልዩ ገሀነም በስልቱ
ስላልመደበለት ኮነንኩት
ቢሻው ያቃጥለኝ እንጂ –
ይቅርታውን አወገዝኩት።
ይህን የፍጥረታት ታናሽ
ማንሳቱም እኮ ያሳፍራል
ግናም በወጉ ቢጉሽ
የትግል ጥንስስን ያበስላል።
ለዚህ ለጠፋ ሕይወት
በከንቱ ለፈሰሰ እስፐርም
ለወንድማማችነት ጠሳት
ማንሳቱስ ከቶ አይጠቅምም
ማስታወሱ እንኳ ይከተት
ሕሊናም አይነወርም።
እኔስ እርሱን በመስራቱ
ያሕዌን በውነት ጠላሁት
ልዩ ገሀነም በስልቱ
ስላልመደበለት ኮነንኩት
ቢሻው ያቃጥለኝ እንጂ –
ይቅርታውን አወገዝኩት።
ዕውቀት ኖሮት ነቅቶ ቢሆን
የቁም ጽሕፈት ቢገራራው
ያባት ታሪክ መቅድም ተመን
ስንኝ ደርሶ ቢያቀልመው
የቅኔ ቤት ሠፍሮ መቅኑን
ልማድ ወግን ቢያስተምረው
ባለለዛ ታሪካችን ቀጥቶ ገርፎ ቢያሳድገው
«የእርጉም ሽንት ያገር ገበን
አሰዳቢ ሙት አስወቃሽ»–
ኃይለስልቱን መች ቢጋራው!
ቦዘኔነት በዋል ፈሰስ
ምቀኝነት ባይነካካው
በየዕለቱ በወሬ ሱስ
ሙሉ ዕድሜውን ባያረከሰው
የሕይወቱን እኩይ ፈረስ
ላይሆንለት ባይጋልበው
እንደወላጅ አብሪ ፋኖስ
ላዲስ ትውልድ ቢያድለው
አዛኝ ወገን አኩሪ ለጋስ
እንዴት ሆኖ ሊያሳፍረው።
እኔስ እርሱን በመስራቱ
ያሕዌን በውነት ጠላሁት
ልዩ ገሀነም በስልቱ
ስላልመደበለት ኮነንኩት
ቢሻው ያቃጥለኝ እንጂ –
ይቅርታውን አወገዝኩት።

## ጅብና ቆረንጮ (ፍልሚያ በሠረንጌቲ)

ከልሳኑ ሥምረት (ሴንትሉዊስ ሚዙሪ)

ጅብም እኮ ያሸላል፥ እያነከሰ ይጉማለላል
በተንኮሉ ተፍነክንኮ፥ በእሬቡ ሳይቀር ይስቃል
እየተገላመጠ የጉሪጥ፥ ሲሻው ብቻውን ያሽካካል
በለጥኩ ብሎ ሳይበልጥ፥ ቃት ቃት እየሳበ ይነጉዳል
እየተገላመጠ የኋሊዮሽ፥ እንዲያው ራሱን ያታልላል፤
የማያውቁት አገር አቋርጦ፥ ቆረንጮ አንጥፉልኝ ይላል
አጋዘኖችን እንዳላፕከ፥ ውሸት ቆርጦ ይቀጥላል
ጥሬ ሥጋቸውን እንዳልበላ፥ ምንጣፍ አድርጓቸው ይተኛል፤
በማግሥቱም ወንዝ ሳይሻገር፥ በቀን ብርሃን ይጋለጣል
ጀምበር ስትወጣ ብራ ሲሆን፥ መውጫያ መግቢያ ይጠፋዋል
እንደገናም ባይተዋር መስሎ፥ ሃገር ካገር ይሰደዳል
የማያውቁት ጅረት አቋርጦ፥ ቆረንጮ አንጥፉልኝ ይላል።

አጋዘኖችም ሲነቁ፥ ግልገሎቻቸውን ጥለው
ከድካመታቸው ይማራሉ፥ በተፈጥሮ ተጠልለው
እየወደቁ እየተነሱ፥ ቆዳቸውን ተገሽልጠው
ከመንገዳቸው ሳይዛነፉ፥ ገደል ቧጠው ዳገት ወጥተው፣
እንዳባቶቻቸው ሰግረው፥ ፍኖታቸውን አስልተው
በኮቴያቸው ተለካክተው፥ በዱካቸው ተሰባስበው
የጅብን የሥራይ መንገድ፥ በኀብረታቸው ፈውሰው
ተመካክረው ተመራርቀው፥ በትግላቸው ተፅናንተው።

የሠረንጌቲ አጋዘኖች ... እንዲህ ብለው ተነጋገሩ
የለያያቸውን አድቢ ጅብ ... በየሜዳው ተጋተሩ።
«ምነው ጠላት ገብቶብን፥ ለመበተን ሲሞክረን
ሹሉ ቀልማማ ቀንዳችን፥ ዶልዱሞ ሳይፈይደን
ምነው ድንበራችንን ለጅብ፥ ለጊዜውም ቢሆን ከፈትን
ከቶስ እንዴት አታሉን፥ ለመበተን ይሞክረን
የሕቡዕ ሰላይ ልኮብን፥ በጭለማ እንዴት ይፍታን
ለቅፅበትም ቢሆንስ እንኳ፥ እንዴት ደፍሮን ያበራገን
በየጥሻው እየተሳተምን፥ ግምባር ለግምባር ተጋጭተን።»
ሲያሰኘንም አከርረን፡ በውሸት ግጭት አምርረን
የመጣንበትን ምድር፥ ለምለም ማኅፀኗን አሰደብን
አንዳንዶም «በመስመር» ሄደን፥ በሸሆናችን ለክተን
ጅብ ግን በዝግዛግ መንገድ፥ ጠልፎ ሲያታልለን
በወገናችን መካከል፥ «የኳስ አብዶ» ሲሰራብን
በመካከላችን ገብቶ፥ ያካይስት ሸር ሲዘራብን
በኮቴያችን አቧራ እንኳ፥ በኀብረት ማወር እየቻልን
የአፈር ጉም አስነስተን፥ ዓይኑን ማጨለም አቅቶን
እርስ በርሳችን ተጫለምን፥ ለጠላት «ፋኖስ» አብርተን
የተፈጥሮ ፀጋችንን፥ ድንበራችንን አስደፈርን
የጥንት ኀብረታችንን፥ ለቆራጭ ጅብ አስበላን።

እርሱም እኮ እውነት አለው፥ በጅብስ ማን ይፈርዳል
አጋዘኖችን ለመበተን፥ በየሰልፉ ይርመሰመሳል
የኑሮ ትግል ነውና፥ እርሱም ግዳይ ያምረዋል፤
ሲሸነፍም ይከንፋል፥ ሀገር ለቆ ይሰደዳል
ባይተዋር ይመስልና፥ አንገቱ ይቅለሰለሳል
ጅብነቱን በናት ዓለም፥ በቦራላሜ ይቀይራል
ደግሞ እስኪነቃበት፥ ሌላ «ታሪክ» ይጀምራል
የተከለፈለፈ ሕይወቱን፥ እስኪሞት ይዞ ይማስናል።
እንዲያው ለታሪኩ ነው እንጂ፥ አሁንስ ጅቡም ፈዟል
በኀብረት መዳፍ ዳሽቆ፥ አልሞት ባይ «ተጋዳይ ሆኗል
የተከለፈለፈ ሕይወቱን፥ እስኪሞት ይዞ ይማስናል።

ማስታወሻ፦ ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው ሀገራቸውን ከዘረኞች
ነፃ እንዲያወጡ ኀብረተሰብን በሚያፈርሱ፣ ወገንን
በሚለያዩ የጠላት ቅጥረኞች ላይ ተመስርቶ
በምሳሌያዊነት የቀረበ ግጥም።

## የትኛው ይሻላል?

ጥሩ አድራጊ ለህዝብ ይሻላል የትኛው
ደርግ ወይስ ወያኔ፣ ኃይለስላሴ ነው?
ጉሳዎች ተምረው አብረው እንዲሰሩ
ሰርተው ጥረው ግረው እንዲተባበሩ
ያደረገ ማነው እዛውንት መስክሩ
የታገለስ ማነው እስቲ እናንተ መርምሩ?
ችግር በሁሉ አለ በደርግ፣ በወያኔ፣ በኃይለስላሴም
የትኛው ይብሳል አስቅቋል በዓለም
ትምህርት ቤት ያሰራ እስቲ የትኛው ነው?
የባህር የአየር የምድር ጦሩንስ ያዘጋጀ ማነው?
ደርግ ወይስ ወያኔ፣ ኃይለስላሴ ነው?
የትኛው ኃይል ነው አዋጅ ያስነገረ
ከሁሉ አስቀድሞ እውቀት ያከበረ
ትምህርት እንዲቀድም ስልጣኑን ሲረከብ ንግግር ያረገ
ደርግ ወይስ ወያኔ ፣ጠቅል ነው ያረገ።
እስቲ እናንተ ፍረዱ ያለብንን ጣጣ
ማርክ እንስጠውና እንስጥ ውሳኔ መከራ ከመጣ
እንመለስ እንፍጠር አዲስ ሞናርኪ
ወይስ ደርግ ይምጣና ይበል ኮምንስኪ
ወይስ ይዘርፈጥ ወያኔ ይበል ከምሲ ኮምኪ።
እስቲ እናስብበት ሁላችሁም እርዱ
እንሂድ ወደኋላ ወይስ እንገስግስ በብርዱ
ፍርድ መስጠት ይገባል ሳትውሉ ሰታድሩ
አገር የለሽ ሰዎች ሆናችሁ ሳትቀሩ
ኧረ እናስብበት ብዙ አናመንታ
ሳይጠፋ ድራሿ ያቺ መልካም ቦታ።
ኢትዮጵያ ስንል የትኛው ክፍል ነው?
የደርግ፣ የወያኔ፣ የኃይለስላሴ ነው
ከሳሽ ተከሳሹ ምስክር ማን ይሁን
ለመንግስት ተወካይ ማን አቃቢ ይሆን
ወደዚህ ወደዚያ እንደ እሳት ራት ሲበር
እንዲያው በያለበት ይገደል ይቀበር
ጥያቄ ብናቀርብ ይህን የመሰለ
የሚቆጣ ይኖር ለምን ይህን አለ
ቸግሮኝ ነው እኔ መላ ስለጠፋኝ
ጥያቄዬን መልሱ ብዙ ሳትሰለቹኝ
ጋላ ነኝ ወረሞ አጋሜ ነኝ ትግሬ
ጉጃሜ ነኝ ወይስ ተግደርዳሪ ጉንደሬ
እስቲ እናንት መስክሩ የትኛው ነው ዘሬ
አስተያየት እንስጥ የጤፍ ቅንጣት ታህል
ሃሳብ ብንሰበስብ ይጠቅመን ይሆናል
እስቲ እንመካከር የትኛው ይሻላል
ኧረ እናስብበት አገር ሳትጠፋ
ቅርሷ ሳያልቅብን ተጨልፎ ባካፋ
ቡልዶዘር እንዲቆም መቆፈር ከአስመራ እስከከፋ
እንሁንም ተላላይ እንሁን ከርፋፋ
መፍሀ ይገባናል አንድ ሆነን በይፋ።

ኃይለማርያም አጉናፍር – ከአትላንታ

## የተፃፈ

(ከዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሣ)

አገኞት ወይ አጣት
እጠልቃት አልጠልቃት
በማለት ወዳጄ የምትባክነው
እንደው ነው፣ ከንቱ ነው ...
ረቂቅ እጅ የፃፈው
ፍቅርከ ትንቢት ነው
ላንተ ከተፃፈች፣
ለሰኮንዶም ሆነ ወይም ለዘላለም
ያንተ እንዳትሆን ሊያቆማት የሚችል
አንድም ስልጣን የለም!
ላንተ ካልተፃፈች
እሷ የሌላ ነች።
ምን ቅርቧ ብትሆን
ካንድ አልጋ ብትሰፍሩ
አንድነት ብታድሩ
አብራችሁ ብትውሉ
ገላችሁ ተጣብቀው
ቢነዱ ቢግሉ
ትንፋሾቻችሁም ምን ቢቀላቀሉ
የማይታየው እጅ
ለሠኮንድም ቢሆን ላንተ ካላደላት
ከቶም አትችልም ጠልቀህ ልትገባት።
ላንቺም እንዲሁ ነው የፍቅር ምስጢሩ
ምን ብትባዝኚ ምንኛ ብትጥሪ
ላንቺ ካልተፃፈ
እሱም ሊሆን አይችል የአንቺ አፍቃሪ።

## HOT DOG

ትርጉም ለቸገረው ቋንቋ ለከፋበት
ቃልን በቃል መውሰድ ወሰን ለሰፋበት
ግብሩ እንጂ ቃሉ ለማያስጨንቀው
የባዕዱን ቋንቋ በቅጥ ላላወቀው
Hot Dog ለሚለው ቃል ዋና ትርጓሜው
የሞቀ የጋለ ያላበው ውሻ ነው።
እንዲያው ቅጥ የማጣት የመቅበጥ ካልሆነ
ትርጉም በስያሜ ጠፍቶ ካልመከነ
ቋንቋ አድኅበታል በሚባለው አገር
Hot Dog ምን አመጣው ለሚበላ ነገር?
እንዲት ታህል ዳቦ ሆድ የማትፈጋ
የቡችላ ብልት በምታህል ስጋ
በርበሬ ዕርድ መሳይ ጨፍልቀው ጨምረው
በታጠፈ ናፕኪን አበባ አስመስለው
አሰራሩ መልካም ዓይነተ፡ አስጎምጂ
ስመ ክፉ አድርገው አጣጣሉት እንጂ።
መልካሙ ተግባሩን ካልሆነ ማርከሻ
እንዲያው ከሆድ አልፎ ለራብ ማስታገሻ
ምኑ ይመሳሰላል ከሚያልበው ውሻ።
በዕርግጥ በህቅ ነገር ስጋውን አትኩሮ
በደንብ ላስተዋለ
ውሻን እንኳን ተዉት ባይሆን ሌላ ነገር
የሚመስለው አለ።

ዳኛቸው ፋንታ — Washington, D.C

## ለሰላምታው እንኳ

ምላሴ ተሳሰሮ
ባንተው ላይ አደመ
ቃሉም አጠረብኝ
ትንፋሼም ደከመ
እጄም ስራ ፈታ
ብዕሩም አቆመ
ነጩ ወረቀትም
ሳልነካው ታመመ
እንዲያ ሆኜ ነበር
እንዲህ ሆንኩልህ
ሡበብ እየፈጠርኩ
ብዬም አልዋሽህ

ስነሳ ከእንቅልፌ
ካንገቴ አቀርቅሬ
የትናንትን ሳስብ
ለዛሬው መኖሬ
ራሴን ታዘብኩት
እኔው በእኔ አፍሬ
መሆን ስላቃተኝ
የቃል ኪዳን ፍሬ

ከግርማ ዘገየ


በኮምፒውተር የአማርኛና
የእንግሊዝኛ የጽሑፍ ሥራዎች
በተቀላጠፈ ሁኔታ

መጽሐፍት፤ መጽሔቶችና
የተለያዩ የአማርኛና
የእንግሊዝኛ ጽሑፎችን
ጥራት ባለው ሁኔታ
ለማሠራት ከፈለጉ ደውለው
ገነትን ያነጋግሩ።

ስልክ — (404)508–4657
ፋክስ — (404)508–2447

# ዜና ቤተክርስቲያን

## የአትላንታ ሳህሊተ ምህረት ቅድስተ ማርያም
## አዲስ ቤተክርስቲያን ህንፃ ሊሰራ ነው።

*«…ባዶ ቦታ ገዝተን ጥንታዊውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅርጽ የያዘና አሁን ያለንበት ህንፃ ከመጥበቡ ባሻገር የሚጉድሉትን እንደህፃናት ትምህርት፣ ሁለገብ አዳራሽ፣ የመኪና ማቆሚያና የመሳሰሉትን መሠረታዊ አስፈላጊ ነገሮችን አሟልቶ የሚይዝ ቤተክርስቲያን እንስራ!»*


ይህ በአትላንታ የምትገኘው የሰአሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አባል ምዕመናን የጋራ ውሳኔ ነው።

የዛሬ 10 ዓመት ገደማ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑና በአትላንታ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖች ከየቦታው ተጠራርተው «የጋራ ፀሎት የምናደርግበት፣ ባህላችንንና እምነታችንን ለልጆቻችን እያስተማርን የምናሳድግበት፣ ጥንታዊውን የቤተክርስቲያናችንን ስርዓት ጠብቀን የምናቆይበት አንድ ቤተክርስቲያን እናቋቁም» ብለው በመነሳት በትንሽ የኪራይ ቤት የጀመሩት መሰባሰብ አድጉና ጉልብቶ ከ3 ዓመት በፊት የራሳችን የሆነ ቤተክርስቲያን ገዝተን እንድንገባ አስችሉን ነበር።

በዚህ የራሳችን ንብረት በሆነ ቤተክርስቲያን እየተገለገልን በቆየንበት የ3 ዓመት ጊዜ ውስጥ የምዕመናኑ ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት እጅግ ፈጣን በሆነ መልኩ እየጨመረ በመምጣቱ እንደልደት፣ ትንሳኤ፣ የእመቤታችን መታሰቢያ በዓለ ንግስና በመሳሰሉት በዓላት ወቅት ብቻ ይጠበን የነበረው ቤተክርስቲያን ዛሬ በአዘቦቱ እሁድ ቀን እንኳ እጅግ እየተጨናነቀ መጥቷል።

ይህንን ጉዳይ አንስቶ በሰፊው የተወያየው የቤተክርስቲያኗ አባል ምዕመናን ዓመታዊ ጉባኤ ከላይ በአርዕስቱ ላይ የተቀመጠውን «… አዲስ ቤተክርስቲያን እንስራ!» የሚለውን ውሳኔ በአንድ ድምፅ አሳልፏል።

ይህ በጥንታዊው የቤተክርስቲያናችን ስርአት መከበርና ለትውልድ የሚቆይ ቅርፅ ለመገንባት ላይ የተመሰረተ የወገን ትብብር ጥሪ ባለፈው የትንሳኤ በዓል ላይ ለተገኘው ምዕመን፤ በደብሩ አለቃ ካህን በመላከ ፀሀይ ገብረማርያም አያሌው፣በቦርዱ ፕሬዚዳንት በአቶ አባተ ዘውዴና፣ በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ም/ሊቀመንበር በአቶ አየለ ገብሩ ተደጋጋፊ መግለጫዎች ታክሎበት የአዲሱን ቤተክርስቲያን የፊት ለፊት ገጽታ የሚያሳየው ንድፍ በይፋ ሲገለጽ በበዓሉ ላይ የተገኙት ምዕመናን በዕልልታና በጭብጨባ ድጋፋቸውን ከማሳየታቸውም በላይ በግለሰብ ደረጃ ከ100 እስከ 5000 (ከመቶ እስከ አምስት ሺህ ብር) የደረሰ አስተዋጽኦ ለማድረግ ቃል የገቡ ሲሆን በየኪሳቸውና በየቦርሳቸው የያዙትም በግንባር በመስጠት ጅምሩ በሙሉ ስሜት እንዲቀጥል ፍላጉታቸውን አሳይተዋል።



ይህ የምስራች ከተነገረበት ጊዜ ጀምሮ በተከታታይ ባለፉት እሁዶች ምዕመናኑ የዓላማውን ስፋትና የፕሮጀክቱን ጥልቀት በመገንዘብ የአንድ ጊዜ ስጦታ ብቻ ሳይሆን ቤተክርስቲያኑ ተሰርቶ አልቆ በደመቀ ስነስርዓት አዲስ ህንፃ እስክንገባ ድረስ «በወር… ይህንን ያህል ገንዘብ እንሰጣለን» «…ይህንን እንደርጋለን» በማለት ቋሚ ችሮታቸውን በማስመዝገብና ክፍያውንም በመክፈል ላይ ይገኛሉ።

የሳህሊተ ምህረት ቅድስተ ማርያም ቤተክርስቲያን ካህናትና አስተዳደር ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ እውን መሆን በየትኛውም ስፍራ የሚገኙ ወገኖችን የተባበረ እርዳታና ድጋፍ ይጠይቃሉ።

የእግዚአብሔር ረድኤትና ቸርነት አይለያችሁ!
ድጋፋችሁንና እርዳታችሁን ለመስጠት አድራሻችን—

**Sealite Mihiret Kidist Mariam**
**Ethiopian Orthodox Tewahido Church**
**P.O.Box 1412, Decatur, GA 30031**
**Tel. (404) 377-2238**

# እንደው ለምክር ያህል

## በመኪና አደጋ ወቅት ምን መደረግ እንዳለበት የሚገልፅ መመሪያ

መኪናዎን እያሽከረከሩ ሳሉ ከተጋጩ ወይም ሌላ አደጋ ሲሆን ካዩ የሚከተሉት መመሪያዎች ሊረዱዎት ይችላሉ።

<u>መኪና እያሽከረከሩ ሳለ ከሌላ መኪና ጋር ቢጋጩ ምን ማድረግ አለብዎት</u>?

– የአደጋውን ቦታ ጥለው እንዳይሸሹ ወይም እንዳይሔዱ።

– በእርስዎም ሆነ በሌላ መኪና ከባድ ግጭት ከደረሰ ወይም የአካል ጉዳት ከደረሰ ወዲያውኑ ፖሊስ ይጥሩ።

– አስተርጓሚ ከፈለጉ ይህንንም ለፖሊስ ወዲያውኑ ያስታውቁ። ፖሊሱ ተርጓሚው እስከሚመጣ ካልጠበቀ የፖሊሱን ስምና የስልክ ቁጥር በኋላ ከተርጓሚው ጋር አብሮ ለመገናኘት ይጠይቁ። ይህም ግኑኝነት ከአደጋው በኋላ በ2 ቀን ውስጥ መሆን አለበት።

– <u>የአካል ጉዳትን ያረጋግጡ</u>፦ እርስዎም ሆኑ ሌላ ሰው ከተጐዳ ያረጋግጡ። ሰው ከተጐዳ ሳይንቀሳቀሱ አምቡላንስ እስከሚመጣ ወይም ርዳታ የሚያደርግ ሰው እስከሚደርስ ይጠብቁ። አስጊ ጉዳቶች ወዲያውኑ ላይታዩ ይችላሉ። ስለሆነም የተጐዳ ግለሰብን ሲያንቀሳቅሱ ይጠንቀቁ። ሰው ካልተጐዳ ሰላም ከሆነ ከመኪናዎ ወዲያውኑ ይውጡ። ዕርዳታ ከፈለጉ በመንገዱ ላይ አይረማመዱ።

– <u>መኪናዎን ማንቀሳቀስ</u>፦ በትራፊክ መንገድ እስከተቻለ አይንቀሳቀሱ። መኪናዎን በጐን ከመንገድ ውጪ ያቁሙ። የኢንሹራንስ ወኪሎች ደንበኞቻቸው መኪናውን ፖሊስ ሳይመጣ እንዳያንቀሳቅሱ ይመክራሉ። የፖሊስ መኰንን መኪናዎች ከተንቀሳቀሱ በዚህ እንቅስቃሴ ላይ ተመርኩዞ ዘገባ አያቀርብም። ዘገባው የሚያተኩረው አሽከርካሪዎችና አደጋውን ያዩ ምስክሮች ላይ ነው።

<u>ጠቃሚ መረጃዎችን ስለመለዋወጥ</u>፦

ብዙ ስቴቶች የመኪና አደጋ በደረሰ ጊዜ የሚከተሉት መረጃዎች እንዲቀርቡ ይፈልጋሉ፦

* ስም፣ አድራሻ፣ የቴሌፎን ቁጥር፣ የመንጃ ፈቃድ ቁጥር፣ የመኪና ሠሌዳ ቁጥር፣ መኪናው የተሠራበት ዓ/ም፣ የመኪናው ዓይነትና ቀለም፦ (ምሳሌ፣ ፎርድ–ቶረስ–ሰማያዊ)፣ አደጋው የደረሰበት ቀንና ሰዓት፣ የኢንሹራንስ ኩባንያው ስም – እነዚህን መረጃዎች ከሁሉም ነጂዎች ይውሰዱ።

<u>ፖሊስ መቼ ይጠራል</u>?

– ከነጂዎቹ አንዱ ኢንሹራንስ ከሌለው ወይም

– ሌላው ነጂ (አሽከርካሪ) እውነቱን ያልተናገረ(ች) ከመሰሉት።

<u>የምስክር ቃል</u>

– ማንኛውም ሰው ከተጠየቀ የምስክርነት ቃሉን መስጠት አለበት። ስለሆነም አደጋውን ያየውን የምሥክር አድራሻና የስልክ ቁጥር ይውሰዱ።

<u>የኢንሹራንስ ኩባንያዎን ይገናኙ</u>።

– ኢንሹራንሱን በመገናኘት ስለአደጋው ያስረዱ።

<u>በሌላ ሰው የመኪና አደጋ ሲሆን ካዩ ምን ማድረግ አለብዎት</u>?

– መኪናዎን ከመንገዱ ዳር ያቁሙ።

– በተቻለ መጠን ዳር ይዘው ይቁሙ። ሌላውን የተጐዳ ግለሰብ ከመርዳትዎ በፊትና የተጐዳውን መኪና ከመቅረብዎ በፊት ሰላም ተረጋግቶ እንደሆን ያረጋግጡ። መኪናው ይቃጠል እንደሆነ፣ ወይም ነዳጅ ያፈስ እንደሆነ ከመቅረብዎ በፊት ወዲያውኑ ፖሊስ ይጥሩ።

– መኪናዎ ናፍጣ መሰል ነገር ካፈሰሰ ወይም ፈሳሽ ነገር ካለው እንዳይነዱ። ከጪስ መውጫው ላይ ያለው ግለት መኪናዎን ሊያጋየውና ሊያቀጣጥለው ይችላል። ከጋዞሊን ሌላ ሌሎችም ፈሳሾች ጉማዎችን በማዳለጥና በማንሸራተት አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ።

– በአደጋው ወቅት ለተሽከርካሪዎች አቅጣጫ በማሳየት ለመምራት አይሞክሩ።

– የአካል ጉዳትን ያረጋግጡ።

– አሽከርካሪዎችና ተሳፋሪዎች ተጐድተው እንደሆነና አምቡላንስ ያስፈልጋቸው እንደሆነ ይጠይቁ። እነርሱ ተጐድቻለሁ ካላሉ አምቡላንስ አይጥሩ።

<u>የምስክርነት መረጃ</u>

– ፖሊስ ከጠየቅዎትና የሌላው መኪና ሾፌር ከፈለገ አድራሻዎንና ስልክ ቁጥርዎን ይስጡ።

* በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ለአምቡላንስ፣ ለእሳት አደጋ መከላከያና ለፖሊስ ግልጋሎት 911 ደውሉ።

(ከሴንትሉዊስ ኢንተርናሽናል ኢንስቲቲዩት የተወሰደ)

# ከአበው

## ታሪክና ምሳሌ

(ከመጋቢ አእላፍ መክብብ አጥናው)

«ሙዚቃ የነፍስ ምግብ ነው» የሚሉ አሉ። እንደእውነቱ ከሆነ ግን ሥጋዊ ስሜትን የሚያዝናና እንጂ ነፍስን የሚያጽናና መንፈሳዊ ምግብነትስ የለውም። ባጭር አገላለጥ የዓለማዊ ፍላጐትን መቀስቀሻ ሞተር ነው ማለቱ ይሻላል። ሄዶ ሄዶ እንደ ዝንጀሮ መንገድ ከዝሙት ዋሻ ሳያደርስ አይመለስምና!

ስለዚህም ያለመጠን ገደብየለሽ የሆነ የሙዚቃና ዳንስ ፍላጐት እየበረታ ሲመጣ እንደሚያስከሩ ዕፀዋት ሁሉ አደገኛ ሱስ ይፈጠርና አእምሮን የሚያናውዝ፣ ስሜትንም የሚበዘብዝ፣ አጥንትን የሚያነቅዝ፣ መንፈስን የሚያደነዝዝ፣ ለሌላው መልካም ፍላጐት ግን አፍዝ አደንግዝ ከመሆን ደረጃ ለማድረስ መቻሉን በሙዚቃ ስሜት ልባቸው ከነሆለለ አንዳንድ ሰዎች መረዳት ይቻላል።

«ዳንስ ህይወቴ ነው» የሚሉም አሉ። ምን ዓይነት ህይወት? ሲደንሱ አድሮ በመጨረሻ ተዝለፍልፎ (faint ሆኖ) በየመንገዱ አረፋ ሲደፍቅ የምናገኘውን አንዳንድ ገደብየለሽ ዳንሰኛ ጥሩ የሙዚቃ ስሜት ያለው ነው ማለት አይቻልም። መቼም ለሁሉ ነገር መጠን ልክና ወሰን አለው። ለሚያሰክር አደገኛ መጠጥ ጥቃቅን መለኪያዎች የተበጁለት ሰው ሁሉ መጠኑን አውቆ እንዲጠቀም ነበር። ነገር ግን እያንዳንዱጋ መለኪያ በልጅ እግሩዋ ትመላለስ እያሉ ከደጋገሙዋት ጠርሙሱ ባጭር ጊዜ ውስጥ ተጋብቶ ሌላ ጠርሙስ ሊያስፈልግ ነው።

ዋጥ፣ ስልቅጥ ነው ጂን አይላመጥም

ጉበት ዘመድ ላይሆን አልለማመጥም። እያሉ በራስ ላይ የሞት ቅጣት መፍረድን ያስከትላል።

በአንድ ወቅት በሀገራችን የነበረው የማርክሲስቱ መንግሥት የተቃውሞ ድምፅ የሚያሰሙበትን የብዙ እልፍ አእላፍ ወጣቶችን ብርቱ መንፈስ ለማደንዘዝና ትግላቸውን ለማዘናጋት ገደብየለሽ ኪነትን እንደጥሩ መሣሪያ አድርጉ በየቀበሌውና በየከፍተኛው የኪነት ቡድን በማቋቋም «አንድ ሰውና አንድ ከበሮ እስኪቀር ድረስ እንዋጋለን» የሚል ግንፍል መፈክር ማንገብ ተጀምሮ ነበር። ታዲያ ያንን ስውር ደባ ያለበትን አደገኛ ዕቅድ ለመቃወም መምከር ለቀይ ሽብር የሚዳርግ ስለነበር በወቅቱ መጠነኛ ትምህርት በመስጠት የኅብረተሰቡን አመለካከት ለማስለወጥ የተጠቀምንባቸው አንዳንድ ታሪክና ምሳሌዎች ነበሩ። የእነዚያም አጫጭር ታሪክና ምሳሌዎች አፃፃፍ ውስጠ ወይራ (ብረት ለበስ) ከመሆኑ የተነሣ ከጭራ የቀጠነውን የሳንሱር (censorship) ኬላ ያለ ምንም ችግር በቀላሉ ለማለፍ ችለው ነበር። ታሪክና ምሳሌዎች ምስጢርን ለማጉላት ወይም ሰወር አድርጉ ለማቅረብ ይጠቅማሉና።

እንግዲህ ለማስረጃ ያህል አሁንም ከዚህ የሚከተለውን ታሪክና ምሳሌ ለማቅረብ የፈለግንበትን ዋናው ምክንያት በስደት አህጉር ተበታትኖ ከሚኖረውም ኅብረተሰብ መካከል ብዙ ሰው የቀለም (የአካዳሚክ) ዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሙያ የሚያዳብርባቸውን መጻህፍትና መጽሔቶችን፣ ጋዜጦችን የማንበብ ልምዱ እየመነመነና እየተዳከመ በመሄዱ ብዙው ሰው በየመኪናውም ሆነ በየቤቱ የመጻህፍት መደርደሪያ ላይ ተከምረውና ጠረጴዛውን ሞልተው የሚታዩት የሙዚቃና የአደገኛ ፊልም ካሴቶች ከመሆናቸው አልፎ የጆሮን ጅማትና የስሜትን አውታሮች ሁሉ በጣጥሶ የሚያወድም የከበሮ ምት እስከመጨረሻው ተለቆ ሲያጓዋርባቸው ጐረቤት ይታወከብናል፣ ሰው ይታዘበናል ብለው የማሰብ ደንታ የሌላቸው አንዳንድ ወገናቻችን ለጉርብትና እንኳ ከማይፈለጉበት ደረጃ እንዳይደርሱ ለመጠቆም ያህል ነው።

### ቁጥር 1 ከጆሊ ጃኪዝም ተጠብቆ የመኖር ጥበብ በታሪክና ምሳሌ ሲቀርብ

ሊዎናርዶ የሚባል የስዕል ሳይንቲስት
አዲስ ሳይንሳዊ ጥበብ ተገልጦለት
አዳዲስ መርከቦች በተሻለ ሞዴል
በመፍጠር ችሎታው መስራት እንደሚችል
አስመስክሮ ነበር ተዘጋጅቶ በውል።
ቢያስፈልግ ደምላሽ ባሕር ሠርጓጅ መርከብ
ያየር በራሪ ጀት በክንፍ የሚያንሣብብ
ታንክ ሮኬት ሚሳይል የእሳት ነበልባል ቦምብ
ሌላም ብዙ ዓይነት የመሣሪያ ጥበብ
ሁሉን ለመፈልሰፍ እንደሚችል ታውቆ
ዝናው አስተጋባ እስከ ጽንፍ ዘልቆ።
ልዩ ፕላን ነድፎ በሥራ ላይ ሊያውለው
ተዘጋጅቶ ሳለ ችሎታ ሳያንሰው
ገንዘብ በማጣቱ እስከመጨረሻው
የሚረዳው አጥቶ የሚተባበረው
ሲባክን መኖሩን ሰምቶ የተረዳው
የሚላኑ መስፍን ወደ አገሩ አስጠራው።
ታዲያ ያ ሰዓሊ ሊዎናርዶ ፈላስፋው
ለሚላን አገር ሕዝብ እጅግ ለሚወደው
ብዙ ስራ እያለ ቅድሚያ የሚሰጠው
ሌላው ጥበብ ቀርቶ ለሕዝብ የሚጠቅመው
ለዳንስ ውዝዋዜ ዳንኪራ መርገጫ
መድረክ እንዲሰራ ባለመወጣጫ
ያ መናኛ መስፍን ሊዎናርዶን ጠየቀ
ሊዎናርዶም ታዝቦት በልቡ እየሳቀ
በመስፍኑ ድክመት እጅግ ተደነቀ።
«ተመልከት እንግዲህ ልብህ ይታዘበው
ስንት ስራ እያለ ቅድሚያ የሚሰጠው
ዳንኪራ ነበር ወይ ሕዝብ የሚጠብቀው?
በዳንስ ውዝዋዜ ጥላና ከለላ
ጆሊ ጃኪዝም ነው ክንድን የሚያላላ
መጠንቀቅ ጥበብ ነው እንዳይቆጭህ ኋላ።

ለምሳሌ ያህል ታላቁ ኢትዮጵያዊ ደራሲ አቶ ከበደ ሚካኤል ስለሙዚቃ ተመስጠ ሲገልጡ፦

«ቃናሽ ነፋስ ሆኖ ድምፅሽ ሰረገላ
ውሰጃት እባክሽ ነፍሲን ወደሌላ»

ሲሉ መጻፋቸው ይታወሳል። ታዲያ ያ ሌላ ቦታ ምን ዓይነት ይሆን? የምናኔ ቦታ? ወይስ ሌላ ያልታወቀ ዓለም? የገሃነም ሰመመንም ሊሆን ስለሚችል ጭልጥ ብሎ አፍቃሬ ሙዚቃ ብቻ በመሆን እንደ ወተት ዕቃ ሲናጡ መኖር የጤንነት አይመስለኝም። አንባቢዎችስ ይህን አባባል እንዴት ታዩታላችሁ?

(የዚህን ተከታይ ቁጥር 2
በሚቀጥለው እትም አቀርባለሁ)

# ሰንጠረዥ ፩

በሰይፉ ኣዳነች ብሻው

(መ) መብቱ የተጠበቀ ፲፱፻፹፱ ዓመት
SAEFU © Copyrighted 1997

ይህን የሰንጠረዥ ጨዋታ ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከቀኝ ወደ ግራ፣ ከላይ ወደ ታች፣ ከታች ወደ ላይና በሰያፍ በመከበብ የቀሩት ሆሂያት የሚያነቡትን በመፈለግ በጊዜዎት ይዝናኑ።

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | በ | ሳ | ጉ | አ | ው | ሉ | የ | ማ | ይ | ጨ | በ | ጥ | ዝ |
| ሳ | ጥ | ም | ራ | ቾ | ታ | ም | አ | የ | ር | በ | አ | የ | ር |
| ረ | ባ | ቋ | ቀ | ስ | ድ | መ | ዓ | ት | ፊ | ስ | ቅ | ጉ | መ |
| ኛ | ጭ | ባ | ወ | ኘ | ፀ | ወ | ስ | ላ | ታ | አ | ቦ | ተ | ው |
| ር | ራ | ጠ | ሰ | ኛ | ነ | የ | ሃ | ሚ | ተ | ኛ | ሶ | ቅ | ለ |
| ብ | ነ | ነ | ገ | ረ | ኛ | ት | ፋ | ክ | ከ | ዕ | በ | ደ | ደ |
| ሽ | ኛ | ው | በ | ጉ | መ | ላ | ና | ው | ጅ | ቅ | ን | ጠ | ሮ |
| ሪ | መ | ሽ | ረ | ኛ | ደ | ጠ | መ | ር | ጭ | ባ | ሌ | ባ | ጓ |
| ባ | ቂ | ብ | በ | ኛ | ለ | መ | ዐ | ቡ | ቅ | ባ | ና | ታ | ባ |
| ር | ጠ | ረ | ተ | ጣ | ር | ኪ | ሉ | ባ | ለ | ገ | አ | ወ | ም |
| በ | ተ | ራ | ባ | ገ | ጠ | ሲ | ን | ጌ | ጭ | ባ | ጣ | በ | አ |
| ጭ | ኩ | ጥ | ኛ | ጉ | ር | ኛ | ቀ | ተ | ል | ባ | ው | ል | ቅ |
| አ | በ | ገ | ቦ | ዞ | መ | ተ | ት | ዕ | ቢ | ት | ላ | ላ | ረ |
| ቀ | ወ | ቀ | ጣ | ፊ | ጥ | አ | ው | ሬ | ሬ | ጥ | በ | ቀ | ደ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሃሚተኛ | ስድ | በጥባጭ | አራቋጭ | ወገኛ | ጉራ |
| | | ባለጌ | አሳረኛ | ውሉ የማይጨበጥ | ጉቦ |
| ለቅሶኛ | ሽረኛ | | አበሳ | ወስላታ | ጉቦኛ |
| ሌባ | ሽብር | ተረበኛ | አበጣባጭ | ዐመለኛ | |
| ልባውልቅ | | ተንኮለኛ | አቦ ተው | ዕንባ | ጠላት |
| | | ትዕቢት | አወናባጅ | | ጠበኛ |
| መርዝ | ቀላል | | አውሬ | ዞር ሲሉ ቡጭቅ | ጠብ |
| መና | ቀላባጭ | ነውረኛ | አየር በአየር | | ጣር |
| መተት | ቀበጥ | ነገረኛ | አጥፊ | ደመኛ | ጣጠኛ |
| መዓት | ቀበጥባጣ | ንቀት | አጭበርባሪ | ደረቅ | ጦሰኛ |
| ምቀኝነት | ቀጣፊ | | | ደደበ | |
| | ቂመኛ | አመፀኛ | ከጅ | | ጭራ |
| ረበሽ | ቅሌታም | አምባጓሮ | ኩራተኛ | ገለባ | ጭባ |
| | ቅርናት | አምታች | ክፋት | ጉረኛ | |

ያለፈው የሰንጠረዥ ፩ መልስ ኢትዮጵያ ነው።
መልሱን በትክክል ያገኙ

1. አለምሸት አብዲ – ከሳንዲያጉ
2. ሰላማዊት መኰንን– ከሳን ሆዜ
3. ደረጀ አሰፋ – ከላስ ቬጋስ
4. ጋሻው ታፈረ – ከሎሳንጀለስ
5. ሀሰን ዑመር – ከቴክሳስ
6. እምሃ ዋለልኝ – ከዳላስ
7. ተዋበች ነጋሽ – ከዳላስ
8. እስናቀ አሰፋ — ሂውስተን

## ያለፈውን ሰንጠረዥ የመለሱ

1. ረታ ኃ/ማርያም – ከአትላንታ 3ኛ ጊዜ
2. አለምሸት አብዲ – ከሳንዲያጐ
3. ሰላማዊት መኰንን– ከሳን ሆዜ ለ2ኛ ጊዜ
4. ደረጀ አሰፋ – ከላስ ቬጋስ ለ3ኛ ጊዜ
5. ወርቅነሽ ተሻለ – ከሴንት ሉዊስ
6. የወንድወሰን ኃ/ስላሴ – ከሮም
7. ዋሌ አዲስ – ከካሊፎርኒያ
8. መለሠ ተከላ – ከኦክላንድ
9. መስፍን ወርቁ – ከሳንዲያጐ
10. ጋሻው ታፈረ – ከሎሳንጀለስ 2ኛ ጊዜ
11. ሀሰን ዑመር – ከቴክሳስ
12. አስናቀ አሰፋ — ሂውስተን 2ኛ ጊዜ

(ሳያቋርጡ 5 ሰንጠረዥ በትክክል ሞልተው ለሚልኩ ሶስት እትም በነፃ እንሸልማለን)

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቀ | ሎ | ማ | ከ | ኝ | ■ | ኸ | ተ | ጦ | ■ |
| ደ | ለ | ቷ | ■ | ደ | ማ | ■ | ሬ | ደ | ቾ |
| መ | ቷ | ■ | ማ | ር | ክ | ፎ | ክ | ፎ | ■ |
| ■ | ም | ፕ | ■ | ■ | ኽ | ር | ■ | ■ | ■ |
| ማ | ■ | ኗ | ጉ | ስ | ■ | ዷ | ባ | ቆ | ■ |
| ባ | ኗ | ዷ | ■ | ብ | ሳ | ■ | ቾ | ሌ | ቆ |
| በ | ባ | ■ | ኧ | ለ | ተ | ማ | ሁ | ■ | ሌ |
| ስ | ዷ | ኗ | ባ | ብ | ■ | ሌ | ■ | | ለ |
| በ | ■ | ጋ | ሁ | ■ | ኸ | በ | ኣ | ■ | ለ |
| ለ | ጋ | ቹ | ■ | ጦ | ከ | ለ | ቀ | ከ | ለ |

## ቃላት በሰንጠረዥ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | ■ | 4 | | 5 | 6 | ■ | 7 |
| 8 | | | 9 | | ■ | 10 | | 11 | |
| | ■ | 12 | | ■ | 13 | | | | |
| ■ | 14 | ■ | 15 | | | ■ | 16 | | |
| 17 | | 18 | | ■ | 19 | 20 | ■ | | ■ |
| 21 | | | ■ | 22 | | | 23 | ■ | 24 |
| 25 | | | | | ■ | 26 | | 27 | |
| | ■ | 28 | 29 | | | ■ | 30 | | |
| 31 | 32 | | | | ■ | 33 | | | ■ |
| ■ | | ■ | 34 | | | | | ■ | ■ |

### ወደጎን

1. ቅሌታም
4. ጠቦት (ትንሽ)
8. ውሃ ውሃ ያሰኛል
10. ጎበዝ
12. ለማዳ የቤት እንሰሳ
13. ዝሙተኛ
15. ኤርትራን ከእናት አገሩ የገነጠለ
16. በሌላው ብልፅግናና ዕድገት መብሸቅ
17. መጨመላለቅ
19. ትኩስ / አዲስ
21. ከንፈሯን በከንፈሩ ነካ
22. የአንድና የአንድ
25. በለፀግን
26. በሰማይ ሳይሆን በ______
28. ጠልቼአት
30. ለ365 ቀናት
33. ትኩሳት
34. አትሆንህምና ________።

### ወደታች

1. ዘረኛ መንግሥት (በኢትዮጵያ)
2. ቄንቅላት
3. ጨፈለቀው
4. ራስ
5. ተገናኘ
6. ልናጥላላ
7. ማዘን
9. ደላላ መሆን
11. የብር ማስቀመጫሽ
13. እመለከታለሁ
14. አወላወለ
17. መሳቂያ
18. አነስ አነስ ባሉ
20. በፈረስ ሄደ
22. የማይጨረስ
23. ትገዘታለህ ?
24. ውጤት
29. ቀይ መሆን
32. ተፈልቶ የሚጠጣ
33. ዓላማ

# የላንዳፍታ መጽሔት ማዘዣ ቅጽ

**የላንዳፍታ መጽሔት እንደታተመች ወዲያውኑ ካሉበት ቦታ እንዲደርሶት ይህንን ቅጽ በመሙላት ከነክፍያው ይላኩልን።**

☐ ☐
☐ ☐
☐ ☐
☐ ☐
☐ ☐

*(please, mark your choice above and send your payment in U.S. Dollars)*

*Subscriber's Name:* ______________________________

*Address:* ______________________________

*City:* ______________________________

*St.* __________ *Zip* __________________ *Phone: (     )* ____________________

==========================================================

*I would like to order for my friend as well. I have included both payments.*
*My friend's name and address are as follows.*

*Subscriber's Name:* ______________________________

*Address:* ______________________________

*City:* ______________________________

*St.* __________ *Zip* __________________ *Phone: (     )* ____________________

==========================================================

*TOTAL PAYMENT ENCLOSED:* $ ☐

*LANDAFTA, P.O.BOX 49301, Atlanta, GA 30359*




# ናዝሬት ምግብ ቤት

## NAZARETH RESTAURANT

*Authentic Ethiopian Cusine*

5291 Memorial Drive
Stone Mountain, GA 30083

በቅርቡ የተከፈተው
የናዝሬት የአገር ባህል ምግብ ቤት
የተሟላ የባር አገልግሎት አለው።
ዓርብና ቅዳሜና እሁድ ምሽቶች
የመዝናናኛ ፕሮግራሞች ይኖሩናል።



የአገርን ትዝታ የሚቀሰቅስ የባህል ምግብ ተመግቦ ምሽቱን
ከአገር ልጆች ጋር ለማሳለፍ የናዝሬት ምግብ ቤት አለላችሁ።

ና
ዝ
ሬ
ት

ብቅ ብላችሁ ጎብኙን!!
በመስተንግዷችን ትደሰታላችሁ!!
በምግባችን ጣዕምን ትረካላችሁ!!

Phone: (404) 294-0043

# ሀናና ብንያም ምግብ ቤት
## H & B Restaurant
## Ethiopian Cuisine & Bar



በቅርቡ ሥራውን የጀመረው ሀናና ብንያም ምግብ ቤት የውድ ደንበኞቹን ፍላጎት ለማርካት በልዩ ዝግጅትና መስተንግዶ የባህል ምግቦችን ያቀርባል።


በተጨማሪም ዘወትር ዓርብ፤ ቅዳሜና እሁድ የተለያዩ የምሽት የመዝናኛ ፕሮግራሞችን ያቀርብላችኋል።

**H & B Restaurant**

*Ethiopian Cuisine & Bar*

4600 A. E. Ponce DeLeon Ave.<br>
Clarkston, GA 30021<br>
Phone: (770)723-0502






መጥተው ይጎብኙን!!<br>
በመስተንግዶአችን ይኮራሉ።

በተጨማሪ በ431 N. Indian Creek, Suite E በሚገኘው ሀናና ብንያም በተሰኘው የኢትዮጵያ ሸቀጦች መደብራችን የበለጠ በማሻሻል እንጀራ፤ በርበሬና የመሳሰሉትን፤ እንዲሁም የአገር ልብስና ጌጣጌጦች በጥሩ ሁኔታ እናቀርባለን።

ጎብኙን!!

ስልክ ቁጥር (404) 296–2766